# ሁለቱ የእምነት ዓይነቶች

## The Two Kinds of Faith



ትርጉም ፦ የእግዚአብሔር ልጅ

እስክንድር ሐዲስ

መሸጋገሪያ ድልድይ ..... ERROR! BOOKMARK NOT DEFINED.
ሕያው የትውልድ አሻራ ..... 3
የተገለጠ ጉዳይ ..... 6
ምእራፍ አንድ ..... 7
የእምነት መሰረታዊ መርሕ ..... 7
አንድ መሰረት ..... 9
ምእራፍ ሁለት ..... 9
እምነት ማለት ..... 9
ምእራፍ ሦስት ..... 11
የእምነት ዓይነቶች ..... 11
እምነት በሐዋርያት ሥራ ላይ ..... 13
ምእራፍ አራት ..... 17
የተለያዩ የእምነት ደረጃዎች ..... 17
ፈጣሪ እምነት ..... 17
ገዢ እምነት ..... 18
ሐይማኖታዊ እምነት ..... 19
በልምድ ላይ የተመሰረተ እምነት ..... 19
ምእራፍ አምስት ..... 20
የመገለጥ እምነት ..... 20
ምእራፍ ስድስት ..... 24
ጥቂት የእምነት ጠላቶች ..... 24
ተስፋ ..... 24
አእምሮአዊ ስምምነት ..... 25
የስሜት እውቀት እምነት ..... 26
ምእራፍ ሰባት ..... 27
እምነት በራሳችሁ እምነት ላይ ..... 27

እምነት በሌሎች እምነት ላይ....29
ምእራፍ ስምንት....30
ተስማሚ ተግባራት....30
ምእራፍ ዘጠኝ....32
ሰው በልቡ ያምናል....32
ምእራፍ አስር....37
ቃሉን መተግበር....37
እምነትና ማመን....38
ስለማመን ጥቂት መረጃዎች....39
ምእራፍ አስራ አንድ....40
የእኛ የሆኑ ነገሮች....40
በክርስቶስ ውስጥ ባለን መብቶች መደሰት....42
ምእራፍ አስራ ሁለት....43
የእምነት እንቅፋቶች....43
የመረዳት ጉድለት....43
ሁለት አዋጆች....44
ትክክለኛ አዋጅ....45
ኢየሱስ ማንነቱን ያውቅ ነበር....47
የተሳሳተ አዋጅ....47
ምእራፍ አስራ ሦስት....50
ጸሎት....50
ጸሎት በብሉይ ኪዳን ስር....50
ጸሎት በአዲስ ኪዳን ስር....51
የያሕዌ አሳሳቢዎች....52
የስምምነት ጸሎት....52
እንዴት እንጸልይ....53
የአብ ፈቃድ ነው....54
ምእራፍ አስራ አራት....55

ማመን የሚገባን ጥቂት ነገሮች.....55
ማመን የማይገባን ጥቂት ነገሮች.....55
ምእራፍ አስራ አምስት.....57
መቀበል እንጂ መስጠት አይደለም.....57
ሁሉም በጸጋ ነው.....60
ምእራፍ አስራ ስድስት.....60
በስሜት የሚገዛ አእምሮ.....60
(ሮሜ 12፥1-2).....60
ምእራፍ አስራ ሰባት.....61
አዲሱ ትእዛዛትና ጽድቅ.....61
በደዌና በበሽታ ሕልውና ውስጥ የጽድቅ ተጽእኖ.....62
ጽድቅ ከእምነት ጋር ያለው ግንኙነት.....64
ለኃጢአት እውቅናን መስጠት በእምነት ላይ ያለው ተጽእኖ.....66
ልናደርጋቸው የሚገቡ ጥቂት ማረጋገጫዎች.....66
ምእራፍ አስራ ስምንት.....66
የእኔ ደረሰኝ.....66
የኃጢአትና የበሽታ ችግር ተፈትቷል.....67
ምእራፍ አስራ ዘጠኝ.....69
ኢየሱስ ስለ እምነት የተናገረው.....69
የሐዋርያው ጳውሎስ ትምህርት.....71
ማጠቃለያ.....72
አስተያየት.....73

# መሸጋገሪያ ድልድይ

ይህችን "ሁለቱ የእምነት ዓይነቶች" የተባለች ምጥን ሆኖም ግን እጅግ ብዙ ጥልቅ አሳቦችን የያዘች ወደ ፊት ለመጓዝ የሚያስችል ከጥርጥርና ካለማመን አዘቅት ነጥቃ የምታወጣ የእምነት ችግር ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የተፈታ መሆኑን ቅልጥጥ አድርጋ ወደ ብርሃን ያወጣች የታላቁን የእግዚአብሔር ሰው ዶክተር ኢሴክ ዊሊያም ኬኒዮንን መጽሐፍ ተርጉሜ እንዳቀርብ የረዳኝንና ለሕትመት ፍጻሜ ያበቃውን እስካጠናቅቀው ድረስም የገጠሙኝን የተለያዩ ተግዳሮቶች በእምነት እንድዘልቅ ትርጉሙንም ቀለል ባለ መልኩ እንዳቀርብ የመራኝን አባቴን እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን ከልቤ አመሰግናለሁ።

በመቀጠልም በዚህ ሁሉ ጊዜ ውስጥ ከአጠገቤ ሳትለይ ተግባራዊ በሆነ መንገድ ያገለገለችኝን እንዲሁም ያበረታታችኝን ባለቤቴን ይፍቱ ሥራ ነገደን ጌታ ይባርክሽ ስል በተለያየ መልክና መንገድ የደገፉኝን በጌታ ወንድሞቼ የሆኑትን ኤርምያስ ተፈራን ሚሊዮን ዘውዴን መላኩ ደነቀንና ባለቤቱን ፓስተር እሌኒ ተረፈን እጅግ አመሰገናለሁ። በተጨማሪ ሐዋርያው ምስጢረ ጌታቸውን ፓስተር ፍጹም ወ/አረጋይን ፓስተር ክንፈ ገብርኤል ማቴዎስንና ፓስተር ግርማ መታፈሪያን ሳላመሰግን በማለፍ ውለታቢስ መሆንን አልሻም።

እንግዲህ ማንም ክርስቶስ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኙ አድርጎ በመቀበል ዳግም የተወለደ ሁሉ "አማኝ" ተብሎ ተጠርቷል ምክንያቱ ደግሞ እምነት የሆነውን ክርስቶስን በመቀበሉና መለኮታዊ ባህሪውን በመካፈሉ ነው። ሁለተኛ ጴጥሮስ 1፥3 "በገዛ ክብሩና በበጎነቱ የጠራንን እርሱን በማወቅ ለሕይወትና ለእውነተኛ መንፈሳዊነት የሚያስፈልገንን ሁሉ የመለኮቱ ኃይል ሰጥቶናል።" ይላል።

"የሚያስፈልገንን ሁሉ" የሚለውን ልብ ካላችሁ በተለይም "ሁሉ" የሚለው ቃል ያላካተተው አንዳችም ነገር አለመኖሩን ከማስተዋል ልትነድሉ አትችሉም በሌላ አባባል አባታችን ይህ ስለሌለኝ ይህ ስለ ጎደለኝ እንዲህና እንዲህ ሆነ ብለን ልናመካኝ የማንችልበት የሕይወት ክበብ ውስጥ አስገብቶናል ማለት ነው።

"ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም።" ኤፌሶን 2፥8። ስለዚህ እምነት የጸጋ ስጦታ ነውና የእኛ ፋንታ መቀበልና ስለ ስጦታው ማመስገን ብቻ አንጂ መቼም ቢሆን ማንም ሰው ስለ ተሰጠው ስጦታ ክፍያ ሲከፍል ታይቶ አይታወቅም።

"እምነትም ሳይመጣ ሊገለጥ ላለው እምነት ተዘግተን ከሕግ በታች እንጠበቅ ነበር እንደዚህ በእምነት እንጸድቅ ዘንድ ሕግ ወደ ክርስቶስ የሚያመጣ ሞግዚታችን ሆኖአል እምነት ግን መጥቶአልና ከእንግዲህ ወዲህ ከሞግዚት በታች አይደለንም።" ገላትያ 3፥23-25

ይህ የእግዚአብሔር ቃል የሚያሳየን ክርስቶስና እምነት አንድ ናቸው በማለት ነው፡፡ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኙ አድርጎ የተቀበለ ሁሉ እምነት ተቀብሏል እያለ ነው፡፡ ምንም እንኳ ሕግ አይሁዶችን ወደ እምነት ወይም ወደ ክርስቶስ እንዲያመጣ የተሰጠ ሞግዚት የነበረ ቢሆንም እምነት ወይም ክርስቶስ መጥቷልና ከዚህ በኋላ አይሁዶችም ሆኑ ሕግ ያልነበራቸው አሕዛብ እምነት ተገልጧልና ሞግዚት አያስፈልጋቸውም፡፡ እምነትና ክርስቶስን በተለዋዋጭነት ለአንድ ዓላማ እንዴት እንደተጠቀመው ልብ በሉ፡፡ ሐዋርያው ይሁዳ ደግሞ ፡-

"ወዳጆች ሆይ አብረን ስለምንካፈለው ድነት ልጽፍላችሁ እጅግ ጓጉቼ ነበር ነገር ግን ለቅዱሳን አንዴና ለመጨረሻ ስለ ተሰጠው እምነት እንድትጋደሉ ለመምከር እጽፍላችሁ ዘንድ ግድ ሆነብኝ፡፡" ይሁዳ 3 ይላል፡፡ (አመት)

ማንም በክርስቶስ ከሆነ አዲስ ፍጥረት ሆኗል ስለዚህ እምነት የሆነውን ክርስቶስን ተቀብሏል ምክንያቱም የጸጋ ስጦታ ነውና፡፡ ይሁዳ ምንም እንኳ ሊጽፍ የፈለገው ስለ ተካፈልነው ድነት የነበረ ቢሆንም መንፈስ ቅዱስ ግን እምነት ለቅዱሳን ለአንዴና ለመጨረሻ መሰጠቱን እንዲጽፍ ግድ እንዳለው እናያለን፡፡ በእምነት ጉዳይ የተለያየ ውዥንበር አንዲመጣ አስቀድሞ አይቶ ብዥታውን በቅድሚያ ለማጥራት የተወሰደ ርምጃ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ይህን የጸጋ ስጦታ የሆነውን እምነት እንድንጋደልለት ሐዋርያው ጳውሎስ (ሁለተኛ ጢሞቴዎስ 6፥12) ላይ እንደ መከረ በመምከር እምነታችንን እንዴት እንደምናንጸውም ይሁዳ እንደሚከተለው ጽፎታል፡፡

"እናንተ ግን ወዳጆች ሆይ እጅግ ቅዱስ በሆነው እምነታችሁ ራሳችሁን ለማነጽ ትጉ በመንፈስ ቅዱስም ጸልዩ፡፡" መጽሐፍም ስለማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን እንደሚል ቅዱስነቱም ከእግዚአብሔር የተሰጠ ስጦታ በመሆኑ ይሁዳ ይህ የተሰጣችሁ እምነት ቅዱስ ስጦታ ነውና በሰጪው በመንፈስ ቅዱስ በመጸለይ አንጹት አለ፡፡

ስለሆነም መጽሐፉን ከዚህ አንጻር እንድታነብቡ ይሕቺን የመዳረሻ ድልድይ ስጽፍላችሁ እጅግ ልመክራችሁና ላሳስባችሁ የምፈልገው አንድ ነገር ቢኖር በመጽሐፍ ቅዱስ እያመሳከራችሁ እንድትዘልቁት ነው፡፡

ይህም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ለመሆኑ አንዳች ማሳያ ከአባታችን ቃል ላሳያችሁ ሐዋርያት ሥራ ምእራፍ አስራ ሰባት ከአንድ እስከ አስራ አራት በሁለት የተለያዩ ስፍራ ስለሚኖሩ ነገር ግን አንድ ዓይነት መልእክትን ከሐዋርያው ጳውሎስ ሰምተው የተለያየ ምላሽ ስለ ሰጡ አይሁዶች ይተርካል፡፡ የመጀመሪያዎቹ በተሰሎንቄ ይኖሩ የነበሩት አይሁዳውያን ሲሆኑ እነርሱም የሐዋርያው ጳውሎስን

እውነተኛ የወንጌል ስብከት ለሕጋቸው ለወጋቸውና ለሥርአታቸው ቀንተው በመቃወም በሐሰት እንደ ወነጀሉአቸውና እንዳሳሰሩአቸው እነ ጳውሎስ ግን በዋስ እንደ ተፈቱ የሚናገረው ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በቤሪያ የነበሩት አይሁድ ግን በተሰሎንቄ

ከሚኖሩት አይሁዶች ይልቅ ልበ ሰፊዎች እንደነበሩ ሆኖም ነገሩ እንደዚህ ይሆንን? በማለት ዕለት ዕለት መጻሕፍትን መርምረው ትክክል መሆኑን ሲረዱ በሙሉ ፈቃድ እንደ ተቀበሉት ያስረገጠው ነው፡፡ መልእክቱን እንዲቀበሉ ያደረጋቸው የጳውሎስ ታዋቂነትና ሐዋርያነት ሳይሆን ከብሉይ ኪዳን ትንቢት ጋር በማመሳከር የተጣጣመ ለመሆኑ መርምረው በማግኘታቸው ነበር፡፡

ማንኛችንም ብንሆን ስለ መጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍትን ማንበብ አለብን ብሎ የሚሞግት አለ ብዬ አላ ስብም፡፡ ነገር ግን ቀደም ሲል የተጻፉትን አሁንም እየተጻፉ ያሉትን ወደ ፊትም የሚጸፉትን መንፈሳዊ መጻሕፍት ሁሉ የመጻሕፍት የበላይ በሆነው በመጽሐፍ ቅዱሳችን መመዘኛነት ከእርሱ አንጻር እናነባቸዋለን፡፡ ትክክል የሆነውን እንደ ቤሪያ ሰዎች በቅን መንፈስ እንቀበላለን ትክክል ያልሆነውን ደግሞ አንገዋልለን በመለየት እንደፋዋለን፡፡

ከዚህ በታች የምታነብቡት የእግዚአብሔር ሰው የሕይወት ታሪክ በሬማ እምነት አገልግሎት ቤተ ክርስቲያን የ"ሬማ ድምፅ" ዋና አዘጋጅ በነበርኩበት በ1993 ዓ.ም "ምስክርነት" በሚለው አምድ ስር ያቀረብኩትን ነው፡፡

ራሳቸውን እግዚአብሔርን መምሰልን ያስለመዱ ሰዎች ስነ መለኮታዊ ትንታኔ ብቻ ከሚሰጡና ስለ እግዚአብሔር አስተያየት ከሚያቀርቡ ነገር ግን ምንም ዓይነት ድንቅ ምልከት ተአምራት ከማይከተላቸው ምሕረት ስር አይወድቁምና የእነዚህን የእግዚአብሔር ሰዎች መጻሕፍት ማንበብ እነርሱ እዚያ ለመድረስ የወጡት የወረዱትን ጊዜ የፈጁትን ጉልበት ሳንወጣና ሳንወርድ እነርሱ በደከሙበት ልንገባ ያስችለናል፡፡ (ዮሐንስ 4፥38)። ከዚህም ባሻገር የኑሮአቸውን ፍሬ ተመልክተን በእምነታቸው ልንመስላቸው ዕድልን ይሰጠናል፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ለዘላለም ያው ነውና፡፡ (ዕብራውያን 13፥7-8)፡፡ ይህንን ሁሉ ለማድረግ ግን መጽሐፉን ገዝተን ማንበብ ለወዳጆቻችንም በስጦታ መልክ በመስጠት እንግሊዘኛውን መጽሐፍ ላላነበቡና እንዲሁም እንግሊዘኛን ማንበብ የማይችሉ ወገኖቻችን እንዲህ ዓይነት መጻሕፍት ትርጉምን አግኝተው በመረዳት ባለ ጠግነት እንዲባረኩ ዕድል እንዲያገኙ በማድረግ እንተባበር፡፡ መልካም ንባብ!

ሕያው የትውልድ አሻራ

በ1867 በአሜሪካ አገር በኒው ኢንግላንድ ከተማ ከድሀ ቤተሰብ ተወለደ፡፡ አስራ ሰባት ዓመት ሲሆነውም በሜቶዲስት የጸሎት ጉባኤ ራሱን ለጌታ አስረከበ፡፡ ወዲያውም አስደናቂ በሆነ ፍጥነት ነፍሳትን ለጌታ መማረክ ሥራው አደረገ፡፡

ለጠፉ ነፍሳት የሚራራ ሕይወቱን የገዛ ስጦታ ከውስጡ ብቅ አለ፡፡ የወንጌላዊነት ሥራውም በፍሬ ይገለጥ ጀመር፡፡ የእግዚአብሔርን እውቀት ለሁሉ ለማዳረስ ለራሱ ቃል ገባ፡፡

በጊዜው ማንኛውም አዲስ የተወለደ ክርስቲያን “የሚደርስበት ችግር” ገጠመው፡፡ ይሁን እንጂ እንዲህ የመሰለውን ተስፋ አስቆራጭ የዲያብሎስ ጥቃት በጽናት የሚጋፈጥበትና የሚያልፍበት መሰረት አልነበረውም፡፡ በመሰረታዊ የእምነት አስተምሕሮ ደቀ መዝሙር እንዲሆን አልተደረገም ነበርና፡፡ በወቅቱ የነበሩ አገልጋዮች ደግሞ በጥርጣሬ መንፈስ በከሉት፡፡

ከዓመታት በኋላ ጌታን ባገኘበት የመጀመሪያዎቹ ጊዜያት መንፈስ ቅዱስን በመረዳት አለመቀበሉን በሃዘኔታ ሲገልጽ ተደምጧል፡፡ በመሆኑም ቀስ በቀስ ከጌታ እየሸሸ ሄደ፡፡ ለሁለት ዓመት ተኩልም ከጌታ ጋር የነበረውን ጎብረት አቋርጦ በጨለማ ተመላልሷል፡፡

በ1893 አዲስ ጎጆ ወጣ! ትዳር መሠረተ፡፡ እርሱና ባለቤቱም በቦስተን ከተማ በክላሬንዶን ጎዳና በሚገኝ መጥምቃውያን ቤተ ክርስቲያን መካፈል ሲያዘወትሩ በተከበረ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪ በነበረው ኢ.ጄ ጎርደን እግር ሥር ተቀምጦ የመማር እድል ገጠመው፡፡ በአገልግሎት መካከል የእግዚአብሔር መንፈስ በእርሱ ላይ በኃይል ወረደ፡፡ ከዚያን ጊዜ አንስቶ ራሱን ለዘላለም ለጌታ አሳልፎ ሰጠ፡፡ በተሀድሶ ወደ ጌታውና ጥሪው ከተመለሰም በኋላ እንደ ቀድሞው ነፍሳትን ለጌታ መማረክ ቀጠለ፡፡ በጥቂት ወራትም ውስጥ በነጻ ፈቃድ መጥምቃውያን ቤተ ክርስቲያን አንደኛው አጥቢያ በመጋቢነት እንዲያገለግል ተሾመ፡፡

በኒው ኢንግላንድ ከተማ ለጥቂት ዓመታት በብዙ ቤተ ክርስቲያናት በመጋቢነት ሲያገለግል በተጓዳኝ ደግሞ በግሉ መንቀሳቀስ ጀመረ፡፡ በተሳተፈበት ቤተ ክርስቲያን ሁሉ ገንዘብ የሚሰበስቡበት መንገድ ደስ ስላላሰኘው የሚያስፈልገውን ማንኛውንም የፋይናንስ ጥያቄ ለሚሚላት ሙሉ ለሙሉ በጠራው ጌታ በመታመን ለመቀበል ወስኖ ከነበረበት ቤተ ክርስቲያን ለቀቀ፡፡ በማንኛውም የሕይወት አቅጣጫ እግዚአብሔርን መደገፍ በጀመረው በጆርጅ ሙለር ጎዳና ለመጓዝ መንገዱን አቀና፡፡ በግል የማገልገል ርምጃውንም ባለማፈግፈግ ቀጠለበት፡፡

በዛ ያሉ ወጣቶች ስልጠና እንዲሰጣቸው በመቅረብ ይወተውቱት ጀመር፡፡ ይህም የመጽሐፍ ቅዱስ ትምሕርት ቤት ለመጀመር መነቃቂያ መንገድ ሆነው፡፡ ከቀደመው መራራ የሕይወት ተሞክሮው የተነሣ አዲስ አማኞችን በመሰረታዊ እምነት ትምሕርት በጽናት እንዲቆሙ ለማድረግ በሙሉ ልብ ተነሣ፡፡ የዚህ እውቀት ከሕይወቱ መጉደል የሁለት ዓመት ተኩል የጨለማ ጊዜ እንዲያሳልፍ ስላደረገው ሌሎች ይህ ሁኔታ እንዳይገጥማቸው ወሰነ፡፡ የምእተ ዓመቱ ማገባደጃ ግድም ላይ ቤቴል የመጽሐፍ ቅዱስ ተቋምን ከፈተ፡፡ የእግዚአብሔርን ቃልና የእምነት ሕይወትን በተግባር ለመማር ብዙ ወጣቶች ወደ እዚህ ትምሕርት ቤት መጉረፍ የማያቋርጥ ሆነ፡፡

ለሚሰጠው ትምሕርት ምንም ዓይነት ክፍያ አይጠይቅም ነበር። ከዚህም በላይ በወቅቱ ለአስተማሪዎቹም ቢሆን ደሞዝ አልነበራቸውም። በአጠቃላይ አገልግሎቱ በእምነት ላይ የተመሰረተ ሥራ ያከናውን ነበር።

በ1923 የምስራቅ ዳርቻን ለቅቆ ወደ ደቡብ ካሊፎርንያ ሄደ። በዚህ አካባቢ ለአያሌ የቤተ ክርስቲያን መጋቢዎች የእግዚአብሔርን ቃል አካፈለ በመልካምም ተቀበሉት። ተአምራዊ ፈውስ ስብከቱን ተከትሎ መገለጡ የተለመደ ሆነ። በሎስ አንጀለስ የመጋቢነት ተግባሩን ስያከናውን ወደ ሺህ የሚጠጉ አባላትን ሊያፈራ የቻለ ጉባኤ ለመሆን እንዲበቃ አስተዋጽኦ አደረገ። ወርሃዊ ጋዜጣ ማሳተም ከመጀመሩም ባሻገር ሁለት መጽሐፎችን ለንባብ አበቃ። በሳምንታዊ አገልግሎቱም አያሌ ሰዎች የጉባኤው ተካፋይ እየሆኑ መታደም ቀጠሉ።

አሁንም ለሦስተኛ ጊዜ አካባቢውን ትቶ ተጓዘ። ይህን ጊዜ ግን በሰሜናዊ ምዕራብ በሚገኝ ሲያትል ተብሎ በሚጠራ ከተማ ኑሮውን በቋሚነት መሰረተ። በሎስ አንጀለስ በነበረ ጊዜ የጀመረውን የእግዚአብሔር ቃል በሬዲዮ በአየር ሞገድ የማሰራጨት አገልግሎቱን ሳያቋርጥ ገፋበት። ትምሕርቱም ብዙ ነፍሳትን ደረሰ አያሌዎችንም ባረከ። ጉባኤውም ወደ ቤተ ክርስቲያንነት አደገ። የአዲስ ኪዳን መጥምቃውያን ቤተ ክርስቲያን ተብሎም ተሰየመ። ሲያትል የመጽሐፍ ቅዱስ ተቋም ትምሕርት ቤትም ሥራውን ቀጠለ በተጨማሪም "ዘ ሔራልድ ኦፍ ላይፍ" ጋዜጣ በሕዝቡ መካከል በስፋት እንዲዳረስ አደረገ።

የስነ ጽሑፍ አገልግሎቱ ማበብ የጀመረው በሰሜናዊ ደቡብ ቆይታው ነበር። በመጀመሪያ ያቀረባቸውን ሁለቱን መጽሐፎች እንደገና በአዲስ መልክ አሻሽሎ አቀረበ። በመቀጠልም ሌሎች መጽሐፎችን በተከታታይ አሳተመ።

ሴት ልጁ ሩት ለፍጻሜ የተቃረቡ ሁለት መጽሐፎቹን ከእርሱ ሕልፈተ ሕይወት በኋላ ቀሪውን አሟልታ ለሕትመት አብቅታለች። እነዚህ መጻሕፍቶች አማኙን በተሀድሶ ይዳስሱሉ ያበረታታሉ መረዳትን ያጎለብታሉ። ከዚህም ባሻገር ክርስቶስ በፈጸመው ሥራ የተከፈለልንን ዋጋ በማወቅ እንድንመላለስ መንገድን ያሳያሉ።

ይህ ሰው ወንጌላዊ መጋቢ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምሕርት ቤት ተቋሙ ፕሬዘዳንት ጸሐፊ መዝሙር ደራሲና ገጣሚ ነበር። አሁንም እጅግ ተፈላጊ በሆኑት አያሌ መጽሐፍቶቹ የታወቀ ነው።

ጽሁፎቹ ለሐዋርያው ጳውሎስ የተገለጠውን የከበሩ እውነቶች በሚያስገርም ቀላል አገላለጽ ፍንትው አድርጎ ያሳያል። የሚጽፈውም ከአእምሮ ይልቅ መንፈስ ለሆነው ለውስጠኛው የልብ ሰው ነው። የጽሑፉ ማዕከላዊ አሳብ የሚያጠነጥነው የእግዚአብሔርን የልብ አሳብ በክርስቶስ ያለውን ማንነት ስልጣንና መብት አማኙ በመረዳት እንዲራመድ ማሳወቅ ነው።

ያለማመንን ከሚያጠናክሩ ባሕላዊ ወግና ትብታብ እንዲወጣና በክርስቶስ ወደ ተዋጀበት ጥልቅ የግንዛቤ ባለጠግነት እንዲገባ ጥሪ ማቅረብ ነው፡፡ ይህንን በቀላል አቀራረብ የተጻፈ መጽሐፍ በማንበብ ብዙ ሕይወት ተለውጧል፡፡

የዚህን ታላቅ የእግዚአብሔር ሰው አገልግሎት ጥቂቶች ያኔም አሁንም ቢነቅፉትም ቢያጥላሉትም ቢያንጓጥጡትና በእውቀት አልባ ትችት ቢዘምቱበትም ትክክለኛ የነበረውን የእግዚአብሔር ልብ አሳብ በርግጠኝነት ተገንዝቦ በመግለጥ ትውልዱን ያገለገለና ዘመን ተሻጋሪ ሆኖ በመቀጠል የሚያገለግል ለመሆኑ ፍሬው አሁን እንኳ ሕያው ምስክር ሆኖ ይናገራል፡፡

ብዙ የጴንጤቆስጤአዊ እንቅስቃሴዎች እግዚአብሔር በእርሱ የገለጠውን መንገድ እንዲከተሉ እውነቱ አስገድዷቸው እንደ ነበር ተቃዋሚዎቹ እንኳ ሳይቀሩ ይመሰክሩለታል፡፡ የቀደሙ አገልግሎቶች ከዚህ ዕይታ አንጻር አካሄዳቸውን ቃኝተው አስተካክለዋል፡፡ አያሌ አገልግሎቶችም ተለውጠዋል፡፡ አዳዲሶችም ተነስተዋል፡፡

በአሁኑ ሰዓት በምድራችን ወርድና ስፋት እንደ አሸን የፈሉ የእምነት አገልግሎቶች በተለያየ የራሳቸው ምክንያት ወደ ኋላ ከተመለሱ ወይም ከተንሸራተቱትና በግብዝነት ሽምጥጥ አድርገው ከሚክዱት በቀር በእርሱ ለተገለጠው እውነት ዋቢነታቸው አያጠያይቅም፡፡ መነሻና መድረሻ የሆናቸው ግንዛቤ ሁሉ መንፈስ ቅዱስ በእርሱ አማካኝነት ያሳየው ምሪት ነውና፡፡

በተወለደ በሰማንያ አንድ ዓመቱ በ1948 እ.ኤ.አ ወደ ጌታው የሄደውና እንደ ደመና በዙሪያችን ካሉ ምስክሮችየተቀላቀለው ይህ ሰው ዶክተር ኢሴክ ዊሊያም ኬኒዮን ወይም ኢ . ደብልዩ . ኬኒዮን ይባላል፡፡

## የተገለጠ ጉዳይ

ያልተመለሱ ጸሎቶች በግለሰብ አማኝና በእምነት ሕይወት መካከል ቆሟል፡፡ ጥቂቶች ጭርሱኑ እምነታቸውን አጥተዋል፡፡ ብዙዎች ደግሞ ከጸሎት ሕይወታቸው ፉርሽ መሆን የተነሳ ወደ ፍልስፍናና ሜታፊዚካል አምልኮ ዞረዋል፡፡

እኛ ግለሰቡን በክርስትና አካሄዱ ላይ ትልቁ ችግሩ ምን እንደሆነ እንደሚያምን ብንጠይቀው ምንጊዜም መልሱ "እኔ በቂ እምነት የለኝም፡፡ የእግዚአብሔር ጥፋት እንዳልሆነ አውቃለሁ፡፡ ተስፋዎቹ በቃሉ ውስጥ እንዳሉም አውቃለሁ፡፡ እምነትን ከማግኘት ግን ጎድያለሁ፡፡ ሰለ ነገሩ ጸልያለሁ ጾሜአለሁ ነገር ግን እንዴት ማግኘት እንዳለብኝ አላውቅም፡፡" የሚል እንደሚሆን አምናለሁ፡፡

ቀጣዩ ጥቂት ውይይት በቁርስ ገበታ ላይ በባልና ሚስት መካከል የተደረገ ነው፡፡

"በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ያለኝን እምነት በጭራሽ አላጣሁም፡፡ ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን በታደምንባቸው ዓመታቶች ውስጥ አንድ ስፍራ መድረስ የነበረብን ይመስለኛል፡፡

"በቢሮ ውስጥ የእምነት ጥያቄ ተነሳና እኔ ምንም እምነት እንደ ሌለኝ አወቅሁ፡፡ ይኸውም በንግዴ ያለኝን እምነት ያህል በቃሉ ላይ አዎንታዊና ቁርጥ ያለ እምነት የለኝም ማለት ነው፡፡

"በምንሠራቸው ሥራዎች ላይ እምነት አለኝ፡፡ ያደርጋሉ ብለን የምናስተዋውቀውን ነገሮች እንደሚያደርጉ አውቃለሁ፡፡

"የእግዚአብሔር ቃል ያደርጋል ተብሎ የተነገረለትን ነገር ስለማድረጉ ግን አላውቅም፡፡ ችግሩ ደግሞ ምን ላይ እንደሆነ ማወቅ እፈልጋለሁ፡፡

"በቢሮአችን ችግር ሲያጋጥመን እንፈታዋለን በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ሲሆን ግን እንሸፍነዋለን፡፡ ነገሩን ችላ እንለዋለን፡፡ የምችለውን ያህል ችላ ብዬዋለሁ፡፡ አሁን ግን የግድ ማወቅ አለብኝ፡፡

ለዚህ መጽሐፍ መነሻ ምክንያቱ ይህ ነው፡፡ በእንዲህ ዓይነት ጎዳና ላይ ላሉ ወንዶችና ሴቶች የእምነትን ጥያቄ ለመመለስ ጽፈናል፡፡

ምእራፍ አንድ

የእምነት መሰረታዊ መርሕ

ባለፈው ቀን አንድ ወጣት "ይህ የእምነት ጉዳይ አስቸገረኝ፡፡" አለ፡፡

መጋቢው እሁድ ዕለት በእምነት ላይ ሰበከ፡፡ እንዴት እምነት እንደማገኝ ግን አላስረዳኝም፡፡ ሆኖም ግን አስፈላጊነቱንና ምን ማድረግ እንደሚችል ነገረኝ፡፡

" ‘ለሚያምን ሁሉ ይቻለዋል’ ‘የሰናፍጭ ቅንጣት የሚያክል እምነት ቢኖራችሁ…’ የሚሉትን ከጌታ አፍ የወጡ አስገራሚ አረፍተ ነገሮችን ጠቀሰ፡፡”

"እኔም ለማግኘት ጣርኩ፡፡ የማውቀውን ማንኛውንም ነገር ሁሉ ወይም ማንም የነገረኝን ሁሉ አደረግሁ ነገር ግን የማይጨበጥ ሆነብኝ፡፡ ችግሩ ምን ላይ እንደ ሆነ ልትነግረኝ ትችላለህን?" አለኝ፡፡

ግልጽና ቅን ነበረና ወደድኩት፡፡ በዓይኖቹ ውስጥ ያለው ጭንቀትም ተፈታተነኝ፡፡ እኔም እርሱን "እምነት የሚመጣው ከእግዚአብሔር ቃል ነው፡፡" አልኩት፡፡

"በምትሠራለት ሰው ላይ እምነት አለህና የደሞዝ ጭማሪ ቃል ቢገባልህ ጥያቄ አታነሳም፡፡

"ንግድህን በምታካሂድበት ባንክ ላይ እምነት ስላለህ ከተቀማጭህ በላይ አውጥተሃል ቢሉህ ጥያቄ አታነሳም፡፡

"አንተና ቃልህ አንድ እንደሆናችሁም ታውቃለህ፡፡ አንተ የቃልህ ጠባቂ ነህና እያንዳንዱን የገባኸውን የተስፋ ቃል ለመፈጸም ትተጋለህ፡፡

"እግዚአብሔርና ቃሉ አንድ ናቸውና እግዚአብሔርም ተስፋ የገባውን እያንዳንዱን ቃል ይፈጽማል፡፡ የቃሉ ፈጻሚ እርሱ ብቻ አይደለም ነገር ግን የእርሱ ሥልጣን የእርሱን ቃል ይፈጽማል፡፡

"እርሱ 'እፈጽመው ዘንድ በቃሌ እተጋለሁ፡፡ ብሏልና"

"እርሱ ሠራተኛ ነው፡፡ ቃሉ የማንኛውም ነገር መሰረት እንደ ሆነ ያውቃልና ቃሉን ለመፈጸም ይተጋል፡፡

"ኢየሱስ 'ሰማይና ምድር ያልፋሉ ቃሌ ግን አያልፍም' አለ፡፡

"እንግዲህ እምነትን የሚሰጠው ይህ ነው ... እርሱም የቃሉ ሐቀኛነት ነው፡፡"

"እምነት ቃሉን በመስማትና በመረዳት ይመጣል የእኛም አንዱ በሕሪ ይሆናል፡፡

"እንግዲህ ጠንከር ያለ ነገር ልናገር ነው፡፡ አንተም እንደምትረዳኝ ርግጠኛ ነኝ፡፡ ሐሰት ማታለልና ከታማኝነት መጉደል የዓለም መለያ ናቸው አይደል?

"ሆኖም እነኚህን መለያዎች በዓለም አቀፍ ግንኙነት በሃገራት መካከል እያየነው ነው፡፡

"በየትኛውም ስፍራ የሚያነፈንፉ የደኅንነት አገልግሎት ሰዎች አሏቸው፡፡ የትም ስፍራ ደኅንነት የሚባል ነገር እሰከማይኖር ድረስ ርቀው ሄደው አንዳቸው ከሌላው የጦር መርከብ ንድፎችን ይሰርቃሉ ሌላም ሌላም ወዘተ ...

"ላለማመናችን አንዱ ምክንያትም ይህ ነው፡፡ አየሩ ይህንን አርግዟል፡፡ ወደ እማይዋሸውና መገዳደር ከማንችለው የእግዚአብሔር ቃል ጋር ስንገጣጠም በአንድም ይሁን በሌላ ልንቀበለው ዝግጁ አይደለንም፡፡

"ሰይጣን ውሸታም ነው እርሱም የእዚህ ዓለም ገዢ ነው፡፡

"ኢየሱስ የእውነት መገለጥ ሆኖ መጥቷል፡፡ እውነትን ለመናገር ሲነሱ ሊያጋጥማቸው የሚችለውን ለመቀበል በራሳቸው ተወራርደው ሊሆን እንደሚገባ ሰዎች ታማኝ እንዲሆኑ አድርጎ የሠራቸው እርሱ ብቻ ነው፡፡

"እዚህ ላይ የእምነትን መሰረት እናያለን፡፡ ኢየሱስን ለማወቅ የምትችለው በቃሉ ብቻ ነው፡፡ እርሱ ደግሞ ከአብ ጋር ያስተዋውቅሃል፡፡

"ከዚያም ቃሉን እንዳለ ለመፈተን ቃሉን መተግበር ትጀምራለህ፡፡

"ከጥቂት ጊዜ በኋላ ኢየሱስ ባለው ወይም አብ ባለው ላይ ስትቆም የምትሠራለት ሰውዬ ቃል ላይ እንደምትቆመው ሁሉ ግላዊ ባሕሪህ ይሆናል።" አልኩት።

እርሱም በጥንቃቄ ካሰበ በኋላ "አመሰግናለሁ ከዚህ በፊት አይቼ የማላውቀውን ተምሬአለሁ ብዬ አምናለሁ።" አለ።

አንድ መሰረት

ለእምነት መሰረት የሚሆን አንድ ነገር ብቻ አለ እርሱም ሕያው የሆነው የእግዚአብሔር ቃል ነው። በተግባራችን ከቃሉ ጋር አንድ ስንሆን ያን ጊዜ እምነት የሕይወት እውነታ ይሆንልናል። እንዲህ ሲሆን በፍጹም ስለ እምነታችሁ አታስቡም የምታስቡት ስለ ፍላጎታችሁና እርሱም ይህንን ሊያሟላላችሁ ብቃት እንዳለው ብቻ ይሆናል።

እምነት እንዲያድግ ጤናማና ጠንካራ እንዲሆን ከፈለጋችሁ ከሥራችሁ ጋር አንድ እንደ ሆናችሁ ከሚሰማችሁ ውስጣዊ ስሜት ጋር አንድ እስኪ ሆን ድረስ በቃሉ ረስርሱ ቃሉን ተመገቡት አሰላስሉት።

በክርስቶስ ማን እንደ ሆናችሁ ልዩ ጥቅማችሁና መብታችሁ ምን እንደ ሆነ እርሱ ስለ እናንተ ምን እንደሚያስብ ስለ እናንተ ምን እንዳለ ፈልጋችሁ አግኙ። ይህንንም ሁሉ በቃሉ ውስጥ ታገኛላችሁ።

ምእራፍ ሁለት

እምነት ማለት

"እምነትም ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ ነው።"

እምነት እውን ያልሆኑትን ተስፋዎች እውን ወደ ሆነው ዓለም ማምጣትና መያዝ ነው። እምነት በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ያድጋል። እምነት በጉጉት ተስፋ የምታደርጉት ነገር መጨረሻ ላይ የእናንተ እንደሚሆን ማረጋገጫ ዋስትና ነው። እርሱ "የማናየውን የሚያስረዳ ነው።"

ግድ የሚላችሁን ጉዳይ ለማሟላት ፋይናንስን ተስፋ ታደርጋላችሁ እምነትም በሚያስፈልጋችሁ ጊዜ ገንዘቡን እንደምታገኙ ዋስትና ይሰጣችኋል።

መሥራት ያለባችሁን ሥራ ለመሥራት አካላዊ ብቃትን ለማግኘት ተስፋ ታደርጋላችሁ። እምነትም "እግዚአብሔር የሕይወቴ መታመኛ (ኃይል) ነው። የሚያስፈራኝ ማነው?" ይላል።

የስሜት እውቀት ከእምነት ጋር በእጅጉ ስለሚመሳሰል ሰይጣን ብዙዎች ሊለዩት ያልቻሉትን የአእምሮ ስምምነትን ለቤተ ክርስቲያን ሰጥቷታል። የአእምሮ ስምምነት የሚያይ የሚያደንቅና "እውነት ነው ነገር ግን በእኔ ጉዳይ ላይ አልሠራም።" የሚል ነው።

የአእምሮ ስምምነት መጽሐፍ ቅዱስ መገለጥ መሆኑን እርሱም ከእግዚአብሔር እንደ መጣ እያንዳንዱ ቃልም እውነት እንደ ሆነ ይስማማል ሆኖም ችግር ሲመጣ ግን አይተገብርም፡፡ እንዲያው ብቻ ለዚያ አስገራሚ መጽሐፍ እውነትነት እውቅናን ይሰጣል ነገር ግን ተግባራዊ አያደርግም፡፡

ተስፋ "አንድ ቀን አገኘዋለሁ" ይላል፡፡

እምነት ደግሞ "አሁን አለኝ" ይላል፡፡

የአእምሮ ስምምነት ደግሞ "ቆንጆ ነው፡፡ ሊኖረኝ እንደሚገባ አውቃለሁ ሆኖም በአንዳች ምክንያት አላገኘሁትም፡፡ ለምን እንደ ሆነ ሊገባኝ አልቻለም፡፡" ይላል፡፡

የስሜት እውቀት እምነት ደግሞ "ሳየው ስዳስሰው ያን ጊዜ እንዳለኝ አውቃለሁ፡፡" ይላል፡፡

እውነተኛ የቃሉ እውቀት ደግሞ "እግዚአብሔር እውነት ነው ካለ እውነት ነው፡፡ እርሱ 'በመገረፉ ቁስል ተፈወሳችሁ፡፡' ካለ ተፈውሻለሁ፡፡ እግዚአብሔር የሚያስፈልገኝን ሁሉ አቀርብልሃለሁ ካለኝ ያደርገዋል፡፡ እግዚአብሔር የሕይወትህ *መታመኛ ኃይሏ* ነኝ ካለ ሆኗል ማለት ነው፡፡ ስለዚህ በሰላም ሥራዬን ወደ ማከናወን እሄዳለሁ ምክንያቱም እርሱ ያለውን እርሱኑ ነው እኔም እርሱ ነህ ያለኝን ነኝና፡፡" ይላል፡፡

"እርሱ አንተ ብርቱ ነህ ካለኝ ብርቱ ነኝ፡፡ እርሱ ተፈውሰሃል ካለኝ ተፈውሻለሁኝ፡፡ እርሱ ስለ አንተ አስባለሁ ካለ እንዳደረገው አውቃለሁ፡፡ ስለዚህ ስሜቶችን ከሚያረካ መረጃዎች ባሻገር በሰላም በቃሉ ላይ አርፋለሁ፡፡"

እውነተኛ እምነት በቃሉ ላይ ይገነባል፡፡ እርሱም በስሜት እውቀት ያልደበዘዘ ነው፡፡ ልክ ሕጻን ልጅ በእናቱ ላይ ያለውን እምነት ዓይነት ለራሱ ተራ ተፈጥሮአዊ ስሜት ንቁ አይደለም፡፡ ሕጻን ልጅ በጭራሽ "እናቴ አሁን ቃልሽን አመንኩ፡፡ ቁራሽ ዳቦ ብጠይቅሽ ለእኔ እንደምትሰጪኝ አወቅሁ፡፡" አይልም፡፡ እንዲህ ቢል እናትየውን ያስደነግጣታል፡፡ ልጇን ምን ነካው ብላም ትገረማለች፡፡

እኛ በእምነት ዙሪያ የተለያዩ እንግዳ የሆኑ የቃላት ቋጥኞች እንደ ተወሳሰበ የእሾህ ሽቦ አጥር አጥረናል፡፡ ወንዶችና ሴቶች "ጌታ ሆይ አምናለሁ አለማመኔን እርዳው፡፡" እያሉ ሲያለቅሱ እምነትን ለማግኘትም ሲጸልዩ ትሰማላችሁ፡፡ ወንዶችም ለእግዚአብሔር እርሱ ያለው ነገር እውነት እንደ ሆነ እያንዳንዱ የተናገረው ቃልም እውነት መሆኑን ሲነግሩት ትሰማላችሁ፡፡ እነኚህ ሁሉ የስሜት እውቀት መንፈሳቸውን እንደ ገዛው እንዲሁም እስከ አሁን ቃሉ በሕይወታቸው የበላይነቱን ስፍራ አለመያዙን የሚጠቁሙ ናቸው፡፡

እምነት የቃሉ በውስጣችን ማደር ውጤት ነው፡፡ ቃሉ የራሳችን የአካል ክፍል እስኪሆን ድረስ የምንኖረውና የምንተገብረው መሆን አለበት ማለቴ ነው፡፡ እናሰላስለዋለን፡፡

በጥልቀት እናስበዋለን፡፡ sssእንመገበዋለን፡፡ ቃሉም የራሳችን ማንነት ይሆናል፡፡ ይህ የእምነት ቃል በውስጣችን መተማመንንና ዋስትናን ይገነባል፡፡

የስሜት እውቀት በሚታይ በሚዳሰስና በሚሰማ ነገሮች ዓለም ውስጥ ይዞ ሊያስቀረን በመንገዳችን ላይ እያንዳንዷን ርምጃ ይዋጋናል፡፡ ነገር ግን እኛ ቃሉ እውን ነውና የማንነታችን ክፍል እስኪሆን ድረስ በጽናት ራሳችንን በቃሉ ውስጥ እናሰጥማለን፡፡

ምእራፍ ሦስት

የእምነት ዓይነቶች

እኔ አዲስ ፍጥረትነትን አስመልክቶ የእግዚአብሔር ቃል ማረጋገጫን ሳልሰጥ ደቀ መዛሙርቱ እስከ ጴንጤ ቆስጤ ቀን ድረስ ዳግም ያልተወለዱ መሆናቸውን ድነትም በኢየሱስ የምትከነት ወይም የመለኮታዊ ልውውጥ ሥራ እምነት ውጤት ነው ስል ገለጻ አደረኩ፡፡

ከጉባኤው በኋላ አንድ ሰው "ማርታ አልዳነችም ማለት ነውን? እርሷ በኢየሱስ አምናለች፡፡ የጴጥሮስስ አዋጅ ድነትን ካመጣልን አንዱ አይደለምን? " አለኝ፡፡

ኢየሱስ ሞቶ ከመነሳቱ በፊት ሰዎች በኢየሱስ ላይ የነበራቸው እምነት ምን ዓይነት ነበር?

ዮሐንስ 20፥9 "ከሙታን ይነሳ ዘንድ እንዲገባው የሚለውን ቃል ገና አላወቁም ነበርና፡፡" ይላል፡፡

ይህ ከጌታ ኢየሱስ ትንሳኤ ጋር የተያያዘ ታሪካዊ ትዕይንት ክፍል ነው፡፡

እኛ ድነት በኢየሱስ የምትከነት ሥራ መለኮታዊ ልውውጥ ይኸውም እርሱ ስለ ኃጢአታችን እንደ ሞተ ደግሞም እኛን ለማጽደቅ እንደ ተነሳ ማመናችን ላይ የተደገፈ እንደ ሆነ እናውቃለን፡፡

ስለዚህ ማርታ በኢየሱስ ላይ የነበራት እምነት በዮሐንስ ፲፥27 ላይ ተገልጿል፡፡ "እርስዋም ፦ አዎን ጌታ ሆይ አንተ ወደ ዓለም የሚመጣው ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆንክ አምናለሁ፡፡" አለችው፡፡ እርሷ ተስፋ እንደ ተገባው የትንቢት ቃል የእግዚአብሔር ልጅ መሲሁ ለመሆኑ በእርሱ ላይ እምነት ነበራት እንጂ የእርሷ የግል ምትከና አዳኝ ሆኖ እንደ ሞተና እንደ ተነሳ በኢየሱስ ላይ እምነት አልነበራትም፡፡

ጴጥሮስ ኢየሱስን በተመለከተ በማቴዎስ ፲፮፥16 ላይ የተመዘገበ ለየት ያለ አዋጅ አድርጓል፡፡ ስምኦን ጴጥሮስም መለሰ እንዲህም አለ "አንተ ክርስቶስ ሕያው የእግዚአብሔር ልጅ ነህ አለ፡፡" ይህም ክርስቶስ ለእርሱ ኃጢአት እንደ ሞተና እርሱንም ለማጽደቅ ከሞት እንደ ተነሳ የሚመሰክር አዋጅ ሳይሆን መሲህነቱንና የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ብቻ ያወጀና የመሰከረ ነው፡፡

በአራቱ ወንጌላት ላይ ክርስቶስን አስመልክቶ ሌላ ለየት ያለ አስደናቂ አዋጅ ወይም ምስክርነት አለ፡፡

ዮሐንስ 6፥30 "እንግዲህ ፡- እንኪያ አይተን እንድናምንህ አንተ ምን ምልክት ታደርጋለህ? ምንስ ትሠራለህ?" "እንኪያ አይተን እንድናምንህ..." የሚለውን አገላለጽ ልብ በሉ፡፡

ምናልባትም ወደ ዮሐንስ 20፥25 ተመልሰን የቶማስን አዋጅ ብናነብ ይሻላል፡፡ ኢየሱስ ከትንሳኤው በኋላ ቶማስ ባልነበረበት ጊዜ ለደቀ መዛሙርቱ ተገለጠላቸው፡፡ የሆነውንም ነገር ደቀ መዛሙርቱ ለቶማስ ነገሩት፡፡ እርሱም "የችንካሩን ምልክት በእጆቹ ካላየሁ ጣቴንም በችንካሩ ምልክት ካላገባሁ አላምንም አላቸው፡፡" ምልክቶቹን ካየ ግን ለማመን ፈቃደኛ ነበረ፡፡

ኢየሱስም መጥቶ አገኘውና "ቶማስን፡- ጣትህን ወደዚህ አምጣና እጆቼን እይ እጅህንም አምጣና በጎኔ አግባው ያመንህ እንጂ ያላመንህ አትሁን አለው፡፡ ቶማስም፡- ጌታዬ አምላኬም ብሎ መለሰለት፡፡ ኢየሱስም፡- ስለ አየኸኝ አምነሃል ሳያዩ የሚያምኑ ብፁዓን ናቸው አለው፡፡"

እዚህ ላይ በተነጻጻሪነት ሁለት የተለያዩ የእምነት ዓይነቶች እኒሁላችሁ፡፡

አንደኛው የስሜት እውቀት እምነት ሲሆን እርሱም ፍጥረታዊውን ሕግ መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ይኸውም ካየን እንቀበላለን ከሰማን እናምናለን የሚል ነው፡፡

ኢየሱስ ደግሞ ከዚህ ለየት ስላለ እምነት እርሱም ሳያዩ ሳይዳስሱ ሳይሰማቸው ስለሚያምኑ ወገኖች ይናገራል፡፡

ኢየሱስ በምድር ላይ በአካል ሲመላለስ በነበረበት ጊዜ ሰዎች በእርሱ ላይ የነበራቸው እምነት የስሜት እውቀት እምነት ነበር፡፡ ይህ አከራካሪና አወዛጋቢ ጉዳዮችን ያጠራል፡፡

አብዛኛው የቤተ ክርስቲያን አካላት እግዚአብሔር ከሰጠን የመገለጥ እምነት ይልቅ የስሜት እውቀት እምነት አላቸው፡፡

ክርስቶስ በምድር በተመላለሰበት ወቅት አይሁዶች በቀደመው ኪዳን ስር ማለትም በብሉይ ኪዳን ስር ነበሩ፡፡ እነርሱ በኮርማዎችና በፍየል ደም ስርዓት ስር ነበሩ፡፡

እነርሱ ክርስቶስ ሞቶ እስኪነሳ ድረስ የዘላለም ሕይወት አልነበራቸውም ምክንያቱም አንዳቸውም ክርስቶስን አዳኛቸው አድርገው አልተቀበሉም፡፡ የእርሱን የተተኪነት ሥራ መለኮታዊ ልውውጥ አላመኑም፡፡ ስለዚህ ጉዳይ ምንም የሚያውቁት ነገር አልነበረም፡፡

ከጌታ ኢየሱስ ትንሳኤ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ ስለ ነበራቸው ሁኔታ ሉቃስ 24፥ ከ10-53 ግልጽ ያለ ስዕል ያቀርባል፡፡

ኢየሱስ ለማርያምና ለሌሎች ተገለጠ። እነርሱም ደቀ መዛሙርቱ ተሰብስበው ወደ ነበሩበት ፈጥነው ሄዱ። "ይህንንም ለሐዋርያት የነገሩአቸው መግደላዊት ማርያምና ዮሐና የያዕቆብም እናት ማርያም ከእነርሱም ጋር የነበሩት ሌሎች ነበሩ። ይህም ቅዠት መሰሎ ታያቸውና አላመኑአቸውም።" ሉቃስ 24፥10

በወቅቱ በደቀ መዛሙርቱ በኩል ለድነት የሚሆን እምነት አልነበረም። እንደ አዳኛቸው አድርገው አልተቀበሉትም። በእርሱ መገለጥ ተምታተውና ተደነጋግረው ነበር። የስቅላቱ መረጃ የሆነውን ምልክት በሰውነቱ ላይ ስላዩ ለዩትና እርሱ መሆኑን አወቁ። ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስ መሲህና የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑ ላይ እምነት ነበራቸው እንጂ እንደ ምትካቸውና ከኃጢአታቸው እንዳዳናቸው አላመኑም። ከሮማውያን እጅ ነጻ እንደሚያወጣቸው አድርገው ይመለከቱት ነበርና።

እግዚአብሔር ለጳውሎስ መገለጥን እስኪ ሰጠው ድረስ የክርስቶስ የምትክነት ሥራ መለኮታዊ ልውውጡ ግልጽ ሆኖ ወደ እነርሱ አልመጣም። ይህንንም በጳውሎስ የመልእክት መገለጥ ላይ እናገኘዋለን።

## እምነት በሐዋርያት ሥራ ላይ

ጳውሎሳዊ መገለጥ ከመታወቁ በፊት በሐዋርያት ሥራ እስከ ምእራፍ አስራ አምስት ድረስ የተመዘገበውን የደቀ መዛሙርቱን እምነት ልብ ብለን እናስተውል።

ሐዋርያት ሥራ 1፡- ደቀ መዛሙርት ከጌታ ጋር ተገናኙ። ዳሰሱት። አብረው በሉ። ድምጹን ሰሙ። ስለዚህ በርሱ ላይ የነበራቸው እምነት በስሜት መረጃ ላይ የተመሰረተ ነበር። ይህ እናንተ ያላችሁ ዓይነት እምነት አይደለም። እናንተ ኢየሱስን በአካል አላያችሁትም። ድምጹን በጭራሽ አልሰማችሁትም። ሰውነቱን አልዳሰሳችሁትም ይሁን እንጂ ከሙታን እንደ ተነሣ አመናችሁ።

እነርሱ ከመሞቱ በፊት አብረው ኖረዋል። ከትንሳኤውም በኋላ ለአርባ ቀን ከእርሱ ጋር ኖረዋል።

ሐዋርያት ሥራ 2፥1-4ን በጥንቃቄ አንብቡ።

"በዓለ ኀምሳ የተባለውም ቀን በደረሰ ጊዜ ሁሉም በአንድ ልብ ሆነው አብረው ሳሉ ድንገት እንደሚነጥቅ ዓውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምፅ መጣ ተቀምጠው የነበሩበትንም ቤት ሁሉ ሞላው። እንደ እሳትም የተከፋፈሉ ልሳኖች ታዩአቸው በያንዳንዳቸውም ላይ ተቀመጡባቸው። በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው መንፈስም እንደ ሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር።"

እንደሚነጥቅ ዓውሎ ነፋስ የሆነ ድምፅ ሰሙ። እንደ እሳትም የተከፋፈሉ ልሳኖች በእያንዳንዳቸው ላይ ሲቀመጡ አዩ። በልሳን ሲናገሩና እግዚአብሔርን ሲያከብሩ

ሰሚቸው፡፡ ይህ ቅልጥጥ ያለ የስሜት እውቀት እምነት እንጂ የመገለጥ እምነት አልነበረም፡፡ በልሳን በመናገር ያመኑት ስለ ሰሙት ነበር፡፡ ማረጋገጫዎቹን ስላዩ መንፈስን አመኑ፡፡

ይህን የተከተሉት በሐዋርያት ሥራ አምስት ላይ የተመዘገቡት ታላላቅ ተአምራት ለአያሌዎች በጌታ ኢየሱስ ትንሣኤ ላይ ታላቅ እምነትን ሰጣቸው፡፡ ይህ እምነት ዛሬ እናንተ ያላችሁ ዓይነት እምነት አይደለም ምክንያቱም እናንተ በኢየሩሳሌም እንደ ነበሩት አካላዊ ማስረጃ አላገኛችሁም፡፡

አንደኛ ዮሐንስ ፩፥፩-4

"ስለ ሕይወት ቃል ከመጀመሪያው የነበረውንና የሰማነውን በዓይኖቻችንም ያየነውን የተመለከትነውንም እጆቻችንም የዳሰሱትን እናወራለን ሕይወትም ተገለጠ አይተንማል እንመሰክርማለን ከአብ ዘንድ የነበረውንም ለእኛም የተገለጠውን የዘላለምን ሕይወት እናወራላችኋለን እናንተ ደግሞ ከእኛ ጋር ኅብረት እንዲኖራችሁ ያየነውንና የሰማነውን ለእናንተ ደግሞ እናወራላችኋለን፡፡ ኅብረታችንም ከአባት ጋር ከልጁም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ነው፡፡ ደስታችሁም እንዲፈጸም ይህን እንጽፍላችኋለን፡፡"

ከትንሣኤ በኋላ ኢየሱስን በዓይናቸው ያዩ በእጃቸውም የዳሰሱ ጴጥሮስና ሌሎችም ነበሩ፡፡ ኢየሱስም በስሙ እጃቸውን በድውያን ላይ እንዲጭኑ በስሙ የመጠቀምን ስልጣን ሰጣቸው፡፡ ይህንንም ስልጣን በተግባር ገለጡት፡፡

በሐዋርያት 3፥6 ላይ ጴጥሮስና ዮሐንስ ስሙን በመጠቀም መልካም በሚሉአት በቤተ መቅደስ ደጅ የነበረውን አንካሳ የሆነ ሰው ፈወሱት፡፡ ሕዝቡም ያውቁት የነበረው አቅመ ቢስ አንካሳ በዓይናቸው ፊት ሲፈወስ ለማየት ቻሉ፡፡ የካህናት አለቆችም እነርሱን ከመያዝ በስተቀር ምንም ሊሉ አልተቻላቸውም፡፡ ሐዋርያት ሥራ 4፥14 "የተፈወሰውንም ሰው ከእነርሱ ጋር ቆሞ ሲያዩ የሚመልሱትን አጡ፡፡" ይህ ነገር የካህናት አለቆችን አፋቸውን አዘጋቸው፡፡

በበዓለ ኀምሳ ቀን ሰዎቹ "ጴጥሮስንና ሌሎችንም ሐዋርያት፡- ወንድሞች ሆይ ምን እናድርግ?" ባሉአቸው ጊዜ ጴጥሮስ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ማመን አለባችሁ አላላቸውም፡፡ በቀላሉ "ንስሐ ግቡ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፡፡" ነው ያላቸው፡፡ የእምነት መገለጥ ገና አልመጣምና እግዚአብሔር እነርሱን እንደ ሕጻናት እያገለገላቸው ነበር፡፡ የማያዩት የማይሰሙትና የማይዳስሱትን አንዳችም ነገር እንዲያምኑ አልጠየቃቸውም፡፡

ብዙ ጊዜ አማኞች "እኛ ቤተ ክርስቲያን በተወለደች ጥቂት ዓመታት ውስጥ የነበራትን ዓይነት ክርስትና እንሻለን፡፡" ብለው ለእኛ መናገራቸው እጅግ አስገራሚ ነገር ነው፡፡ ያንን

ዓይነት ክርስትና ለማግኘት መሻታቸው ትክክለኛውን እምነትና ቃሉን መቃወማቸው እንደ ሆነ አልገባቸውም።

እነርሱ፡- ውጪአዊ መገለጥ ካልታየ (እንደ ሐዋርያት ሥራ 2፥1-4 ማለት ነው) በስተቀር ማንም መንፈስ ቅዱስን ሊቀበል አይችልም ሲሉ ያውጃሉ። ስሜታዊ መረጃዎች እስከ ሌሉ ድረስ እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል አለ ብለው አያምኑም። ይህ በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሰረተ እምነት አይደለም። በስሜት (በአምስቱ አካላዊ የስሜት ሕዋሳት) ላይ የተመሰረተ እምነት ነው። እኔ "አይቼዋለሁ" እኔ "ሰምቼዋለሁ" እኔ "ዳስሼዋለሁ" ስለዚህም እንዳለኝ አምናለሁ የሚል ነው።

"ይህን ብቻ ከእናንተ እንድማር እወዳለሁ በሕግ ሥራ ወይም ከእምነት ጋር በሆነ መስማት መንፈስን ተቀበላችሁን? እንዲህን የማታስተውሉ ናችሁ? በመንፈስ ጀምራችሁ አሁን በሥጋ ትፈጸማላችሁን?" (በስሜት) ገላትያ 3፥2-3

እኛ ከጊዜው የተነሳ ማደግና በእምነት እንጂ በማየት አለመመላለስን መማር ሲገባን ሳለ ባልቻልን ጊዜ እግዚአብሔር በታላቅ ጸጋ እንደ ሕጻናት እንዳገዘን ማየት ትችላላችሁ።

የሐዋርያት ሥራን የመጀመሪያዎቹን አስራ አምስት ምእራፍ በጥንቃቄ ብታጠኑ አንዳቸውም የኢየሱስን የምትክነት ወይም መለኮታዊ ልውውጥን ሥራ ስለ መረዳታቸው ቅንጣት መረጃ እንደ ሌለ ታስተውላላችሁ።

ስለ ጽድቅ ታላቁ ትምሕርት አንድም ፍንጭ የለም። እነርሱ አዲስ ውልደት ምን ማለት እንደ ሆነ ስለ መረዳታቸው የሚጠቁም አንድም ነገር የለም። በርግጥ እነርሱ ደስ ተሰኝተውበታል በነገሩ በሙላት ተመላልሰውበታል ሆኖም በጭራሽ አልተረዱትም። ይህ በኋላ ላይ አብ ለሐዋርያው ጳውሎስ በሰጠው መገለጥ የመጣ ነበረ።

መቼም እኛ ከሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ስለ መዋጀት ወይም ስለ መቤዠት ስለ ምትክነት ወይም መለኮታዊ ልውውጥ ሥራ ሰለ አዲስ ፍጥረት ኢየሱስ በአብ ቀኝ ስላለው አገልግሎት ድንቅ ርእሶች መግቢያ የሚሆን ነገር እንጠብቃለን ነገር ግን ስለ እነዚህ ጉዳዮች አንዲትም ነገር የለም። ከእነዚህ ርእስ ጋር የሚቀራረብ ነገር ከመጽሐፉ የምናገኘው በሐዋርያት ሥራ 15፥10-11 በኢየሩሳሌም በሐዋርያትና ሽማግሌዎች ስብሰባ ላይ ነው። እርሱም ጳውሎስ የሰበከውን መልእክት በሐዋርያቱ ፊት አቀረበላቸው። ከዚያም ጴጥሮስ ተነስቶ "እንግዲህ አባቶቻችንና እኛ ልንሸከመው ያልቻልነውን ቀንበር በደቀ መዛሙርት ጫንቃ ላይ በመጫን እግዚአብሔርን ስለ ምን ትፈታተናላችሁ? ነገር ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ እንደ እነርሱ ደግሞ እንድን ዘንድ እናምናለን።" አለ። ሐዋርያት ሥራ 15፥10-11

እርሱ በቀደመው ኪዳን ስር ሕጉን ስለ መጠበቅ የሆነው ማጣቀሻ አለው፡፡ የመጨረሻው መግለጫ ግን አሕዛብ አማኞችን አስመልክቶ ነው፡፡ የመገለጥ እምነትን ከማንሳታችን በፊት ዛሬ ሰዎች በኢየሱስ ላይ ስላላቸው የተለያዩ የእምነት ዓይነቶች ልብ ልንል ይገባል፡፡

የዛሬ ክርስቲያን ሳይንስ አንድነትና ሌሎች የሜታፊዚክስና የፍልስፍና አስተማሪዎች እግዚአብሔር መንፈሳዊ አካል እንዳለው አያምኑም፡፡ እርሱ ፍጹም ጎሊና መሆኑን ይነግሯችኋል፡፡ በእያንዳንዱ ግለ ሰብ ውስጥ የሚገኝ ታላቅ የኒቨርሳል ጎሊና ነው ሆኖም አድራሻ የለውም ይላሉ፡፡ አካል አልባ አእምሮ የሌለው ጎሊና ነው ይላሉ፡፡ ጳውሎስ በተሰጠው መገለጥ አማካኝነት ስለ ኃጢአት የሚያስተምረውን አይቀበሉም፡፡ ሰማዕት ሆኖ እንደ ሞተ እንጂ ኢየሱስ ስለ ኃጢአታችን መስዋእት ሆኖ እንደ ሞተ አያምኑም፡፡ እነርሱ በአካል ትንሳኤ እንደ ተነሳ አያምኑም፡፡ ነገር ግን አንዱ እንዳስቀመጠው "ሜታ ፊዚካላዊ ትንሳኤ" (ምን ለማለት እንደ ተፈለገ ባይታወቅም) ነው በማለት ያምናሉ፡፡

እግዚአብሔር ሕልው ካልሆነ ወይም ሕልውና አልባ ከሆነ ኢየሱስ ኃጢአትን አላስወገደም ማለት ነው፡፡ ታዲያ ኢየሱስ ማን ነው? ደግሞስ በእርሱ ላይ ያለን እምነት ዋጋስ ምንድን ነው?

ከእነርሱ አንዱ ኢየሱስን "መንገድ - አሳዩ" ሲል ጠራው፡፡ እርሱ ግን መንገድ አሳዩ አይደለም፡፡ እርሱ ራሱ መንገድ ነው እንጂ!

እነርሱ በኢየሱስና በእግዚአብሔር ላይ ያላቸው እምነት በራሳቸውና በተፈጥሮ በውስጣቸው ባለው ማንነታቸው ላይ ነው፡፡ በእነርሱ ላይ ታላቅ ለውጥን አምጥቶላቸዋል ነገር ግን አዲስ ፍጥረትነትን አላፈራላቸውም ደግሞም ከእግዚአብሔር አብ ጋር እውነተኛ ኅብረት አላመጣላቸውም ጽድቅንም አልሰጣቸውም፡፡

የዛሬ ጊዜ "ዘመናውያን" ያላቸው እምነት ምንድን ነው? ሰዎች ስለ ኢየሱስ ራሳቸው ባመነጩት ጽንሰ አሳብ ላይ ያላቸው እምነት ነው፡፡ እርሱም አዲስ ፍጥረትነትን አያፈራላቸውም፡፡ የጠፉትንም አያድንም፡፡

ሰዉ በሳይንስ ላይ እምነት አለውና ሳይንስን የዘመኑ ሰብዓዊ ፍጡር አምላክ መሆኑን በታላቅ ድምፅ እየጮኸ ያውጃል፡፡ ነገር ግን ሳይንስ በታላቁ ዩኒቨርስ አካል ከተደበቀው እውነት ውስጥ ሰው የሰበሰበው ፍርፋሪ የእውቀት ቅንጣት ብቻ ነው፡፡ እነዚህንም እውቀቶች ያገኘው በአምስት የስሜት ሕዋሳቱ አማካኝነት ነው፡፡ እነዚህ አምስቱ የስሜት ሕዋሳት ፍጥረት ለምን እንደ ተፈጠረ ለፍጥረት መፈጠር ምክንያቱ ምን እንደሆነ ማግኘት አላስቻሉም፡፡

እነርሱ የሕይወትን ምንጭ ወይም የእንቅስቃሴን ወይም የሥልጣንን ወይም ዩኒቨርሱን በአንድነት ደግፎ የያዘውን ኃይል ፈልገው ማግኘት አልተቻላቸውም፡፡ ሰው ለምን እንደ

ተፈጠረ መጨረሻውም ምን እንደሚሆን አያውቁም፡፡ የስሜት እውቀት ውሱን ነው ስለሆነም የስሜት እውቀት እምነትም ውሱን ነው፡፡

## ምእራፍ አራት

## የተለያዩ የእምነት ደረጃዎች

ምንም እንኳ እምነት ለሰዎች ሁሉንም ታላላቅ ስኬቶች የወለደ ቢሆንም በቤተ ክርስቲያን ግን እምነት "የረባ ስፍራ" አላገኘም፡፡

ዉልወርዝ በአምስትና አስር ሳንቲም ላይ እምነት ነበረውና ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ $60,000,000 እና በየመንገዱ መታጠፊያ ላይ ብዙ ሱቆች ትቶ አለፈ፡፡

ፎርድ ማንም ሰው ሊገዛው የሚችል አነስተኛ ዋጋ ባለው አውቶሞቢል ላይ እምነት አለው፡፡

እምነት ለስልጣኔ መነልበት ታላቁ መሰረታዊ ነገር ነው፡፡ እንግዲህ በፍጥረታዊው ዓለም የሰብአዊ ፍጡር እምነት እንዲህ ዓይነት ስኬቶች ከወለደ አማኞች በአብና በቃሉ ላይ የሚኖራቸው እምነት ለንጽጽር ሊቀርብ የማይችል መንፈሳዊ ስኬቶችን ይወልዳል፡፡

በሚያቀርበው መልእክት ላይ እምነት ያለው ሰባኪ በሚሰሙት ሰዎች ልብ ውስጥ ቃሉ የእምነት ውጤት ፍሬ ሲያፈራ ያያል፡፡ እግዚአብሔር እንዳለበትና ለመፈጸምም እንደሚተጋ በቃሉ ላይ እምነት አለው፡፡ ለሚሰጣቸውም ቃል ምላሽ እንደሚሰጡ በሰዎቹ ላይ እምነት አለው፡፡ እርሱ ፍቅርን በተመለከተ የኢየሱስ ዓይነት ፍቅር ላይ እምነት አለው፡፡ ፍቅር የማንኛውም ሰብአዊ ፍጡር ችግር መፍትሔ ነው ደግሞም ፍቅርን የሚለማመድ ቤተሰብ ታላቁን ዓይነት የክርስቲያን ባሕሪ ያፈራል ብሎ ያምናል፡፡

እግዚአብሔር የእምነት አምላክ መሆኑን ያወቅኩበት ዕለት በሕይወቴ ታላቁ ቀን ነው፡፡ የፍቅር አምላክ መሆኑን አውቃለሁ፡፡ እርሱ የጽድቅ አምላክ ሁሉን ቻይ ሁሉን አዋቂ አምላክ መሆኑንም አውቃለሁ ሆኖም በይበልጥ የእምነት አምላክ መሆኑን ባየሁ ጊዜ እኛም የእርሱ ልጆች እንደ መሆናችን መጠን በእምነት መመላለስ ሳንጨናነቅ የምንኖረው ባሕሪያችን መሆኑን አየሁ፡፡

## ፈጣሪ እምነት

"ዓለሞች በእግዚአብሔር ቃል እንደ ተዘጋጁ ስለዚህም የሚታየው ነገር ከሚታዩት እንዳልሆነ በእምነት እናስተውላለን፡፡" ዕብ ፲፩፥3

ይህም ከነተበ ዓለም በመታደስ የተገኘ ሳይሆን ትኩስና አዲስ ፈጠራ ነበር፡፡ እርሱም በቃላት የሚታዘዝ መሆኑንም አስተዋልኩ "እርሱም የከብሩ መንጸባረቅና የባሕርዩ ምሳሌ

ሆኖ ሁሉን በሥልጣኑ ቃል እየደገፈ ኃጢአታችንን በራሱ ካነጻ በኋላ በሰማያት በግርማው ቀኝ ተቀመጠ::" ዕብ 1፥3

በመጀመሪያው የአሪት ዘፍጥረት ምእራፍ ላይ በተደጋጋሚ የሚገኙ ሦስት ቃላት አሉ እነርሱም "ይሁን አለ" የሚሉት ናቸው:: (በአማርኛ ሁለት ብቻ ናቸው ("let there be") በእንግሊዘኛ ግን እንደምታዩት ሦስት ናቸው::) በቅንፍ ውስጥ ያሉት ለማብራሪያ የተጨመሩ ናቸው::

እምነትን የተሞሉ ቃሎች ዩኒቨርሱን ወደ መኖር አመጡት ዛሬም እምነትን የተሞሉ ቃሎች ዩኒቨርሱን እየገዙት ነው:: ኢየሱስ ጥቂት የፈጠራ እምነት ማነጻጸሪያዎችን ሰጥቶናል:: ማቴዎስ 15፥30-31 አካለ ስንኩላን ተፈወሱ (ምሉዕ) ሆኑ በማለት መዝግቦታል::

"ብዙ ሕዝብም አንካሶችን ዕውሮችንም ዲዳዎችንም ጉንድሾችንም ሌሎችንም ብዙ ይዘው ወደ እርሱ ቀረቡ በኢየሱስም እግር አጠገብ ጣሉአቸው ፈወሳቸውም ስለዚህም ሕዝቡ ዲዳዎች ሲናገሩ ጉንድሾችም ሲድኑ አንካሶችም ሲሄዱ ዕውሮችም ሲያዩ አይተው ተደነቁ የእስራኤልንም አምላክ አከበሩ::"

እኔ ብልቶቻቸው በኦፕራሲዮን በዶክተሮች የተወገደላቸው ሆኖም በሚፈጥር እምነት ብልቶቻቸው ተመልሰው የተተኩላቸው አያሌ ሴቶችን አውቃለሁ:: የሚፈጥር እምነት ኢየሱስ በአካል በገሊላ ሲመላለስ የነበረውን ያህል ዛሬም እውን ነው::

## ገዢ እምነት

ይህ ሁኔታዎችን የሚያዝዝና የሚገዛ እምነት ነው:: በዕብራውያን 1፥3 የኢየሱስን ሥዕል እናያለን:: "እርሱም የክብሩ መንጸባረቅና የባሕርዩ ምሳሌ ሆኖ ሁሉን በሥልጣኑ ቃል እየደገፈ ኃጢአታችንን በራሱ ካነጻ በኋላ በሰማያት በግርማው ቀኝ ተቀመጠ::"

እዚህ ላይ እርሱ ፈጣሪ ብቻ አይደለም ነገር ግን የፈጠረውንም የሚገዛ ጭምር ነው እንጂ:: ዩኒቨርሱን በቃሉ ኃይል ሥልጣን ይመራል ይገዛል:: ቀጣዩ ጥቅስ የፍጥረትን ኃይል እንደሚገዛ አንድ ማሳያ ነው::

"እርሱም ... ተነሥቶ ነፋሱንና ባሕሩን ገሠጸ ታላቅ ጸጥታም ሆነ::" ማቴ 8፥26:: ኢየሱስ ነፋሱንና በሕሩን በቃሉ ጸጥ አሰኘ ገዛ:: የእርሱን ሥልጣን ገዢነት የተመለከቱትን በጣም አስደነቃቸው:: "ሰዎቹም :- ነፋሳትና በሕርስ ስንኳ የሚታዘዙለት ይህ እንዴት ያለ ሰው ነው? እያሉ ተደነቁ::" ማቴ 8፥27:: በሉቃስ 5፥1-11 የባሕር ዓሣዎችን ሲገዛ (ሲያዝ) እናየዋለን:: የጴጥሮስን ጀልባ ለጊዜው እንደ ምስባከ ወለል ተጠቅሞ ሲያበቃ ለተጠቀመበት ከፈለ:: እርሱም "ትላንት ምሽት አንዳች አጠመዳችሁን?" አለ:: ጴጥሮስም "ጌታ ሆይ በፍጹም" አለ:: ኢየሱስም "ወደ ጥልቁ ፈቀቅ በል መረቦቻችሁንም ለማጥመድ ጣሉ አለው::" ጴጥሮስም "አቤቱ ሌሊቱን ሁሉ አድረን ስንደክም ምንም አልያዝንም ነገር ግን በቃልህ መረቦቹን እጥላለሁ አለው::"

መረቦቹም በቅጽበት በዓሦች ተሞሉ፡፡ ገዢ እምነት ማለት ይህ ነው፡፡

"ፀሐይም ገብቶ በመሸ ጊዜ የታመሙትንና አጋንንት ያደረባቸውን ሁሉ ወደ እርሱ አመጡ ከተማይቱም ሁሉ በደጅ ተሰብስባ ነበር፡፡ በልዩ ልዩ ደዌ የታመሙትን ብዙዎችን ፈወሰ ብዙዎችንም አጋንንት አወጣ አጋንንትም ክርስቶስ መሆኑን አውቀው ነበርና ሊናገሩ አልፈቀደላቸውም፡፡" ማር ፩፥32-34

ኢየሱስ አጋንንትን አዘዛቸው እነርሱም በእነርሱ ላይ ያለውን ሥልጣን ተገነዘቡ፡፡ በዮሐንስ ፲፩፥39-44 አልዓዛር ሲነሳ እርሱ በሞት ላይ ጌትነቱ ተገልጧል፡፡ እርሱም "ድንጋዩን አንሱ አለ" ከዚያም አልዓዛርን ወደ ውጭ ና ብሎ አዘዘው፡፡

ኢየሱስ ገዢ እምነት አለው፡፡ የአጋንንታዊ ኃይልን ይገዛል፡፡ የዲያብሎስን ሥራ ይገዛል፡፡ እርሱ ጌታ ነበር፡፡ የበለሲቱ ዛፍ እንድትደርቅ አዘዛት ከስሯ አንስታ ደረቀች፡፡ ዩኒቨርሱን በሚገዛው ሕግ ላይ እርሱ ፍጹም ገዢ ንጉስ ነው፡፡

## ሐይማኖታዊ እምነት

ዛሬ ሐይማኖታዊ እምነት ምን ያሕል ግዙፍ ኃይል እንደ ሆነ ጥቂቶቻችን እንገነዘባለን፡፡ ሰዎች በቀኖና ላይ በድርጅቶች ላይ በቤተ ክርስቲያናቸው ላይ በመድኃኒት ላይ በዶክተሮች ላይ በሜዲካል ሳይንስና ቀዶ ጥገና ላይ በመልካም ሥራ ላይ በርህራሄ ድርጊት ላይ ገንዘብ በመስጠት በንስሃና ራሳቸውን በመቅጣት ያምናሉ፡፡ በአመዛኙ ሰው እርሱ ወይም ሌላ ሰው ሊያደርገው በሚችለው ነገር ላይ ያለው እምነት አስገራሚ ነው፡፡

## በልምድ ላይ የተመሰረተ እምነት

ከተለያዩ የእምነት ዓይነቶች መካከል ምናልባትም እጅግ አሳሳቹ እምነት በልምድ ላይ የተመሰረተ እምነት ነው፡፡ ሰዎች የተሰማቸውን ስሜት የሰሙትን ወይም ያዩትን ይናገራሉ፡፡ በቅርብ ቀን አንዱ "አልተፈወስኩም ስለዚህ እምነቴን መግለጥ አልቻልኩም፡፡" አለኝ፡፡ እንዲህ ያሉ ሰዎች ያላቸው የስሜት እውቀት እምነት ነው፡፡ እንደ እነዚህ ዓይነቶቹ አካላዊ መረጃ ማግኘት አለባቸው አለበለዚያ ግን አያምኑም፡፡

"ዘመናዊቷ"ን ቤተ ክርስቲያንን ከያዛት ከዚህ አሳሳች ጉዳይ የበለጠ አደገኛ ነገር የለም፡፡ ጥቂቶች አካላዊ መገለጫ እስካላገኙ ድረስ መንፈስ ቅዱስን መቀበላቸውን አያምኑም፡፡ ሕመሙ ሰውነታቸውን ለቅቆ እስካልሄደ ድረስ መፈወሳቸውን አይቀበሉም፡፡ አካላዊ መረጃ በዓይናቸው እስካላዩ ድረስ እግዚአብሔር ጸሎታቸውን እንደ ሰማ አያምኑም፡፡ ይህን የመሰለ ዓይነት እምነት ውስጥ የስሜት እውቀትና የስሜት መረጃ የእግዚአብሔር ቃል ሊይዘው የተገባውን ስፍራ ይዞ እናገኘዋለን፡፡

በመገለጥ እምነት ውስጥ ቃሉ ዋነኛውን የመጀመሪያ ስፍራ ይይዛል፡፡ በአካላዊ መረጃ ላይ የተደገፈ አይደለም፡፡ የመገለጥ እምነት ከእግዚአብሔር አፍ የወጣ ቃል ኃይል አልባ

እንዳልሆነ በማመን እግዚአብሔር በተናገረው ውስጥ በፍጹም መታመን ያርፋል። ከማንኛውም መረጃ ውጪ ቃሉን የመጨረሻ ወሳኝ አድርጎ ይቀበላል።

ቃሉ ካወጀው ያ በቂ ነው። አንድ የታመመ ሰው "በእውነት እርሱ ደዌዬን ተሸከመ ሕመሜንም ተቀበለ።" ብሎ ያነብብና በደስታ "ተፈውሻለሁና አባት ሆይ አመሰግንሃለሁ።" ይላል። ይህ አዲስ ኪዳን ወይም የመገለጥ እምነት ነው።

ምእራፍ አምስት

የመገለጥ እምነት

የጳውሎስ መገለጥ የተመሰረተበት ሦስት ታላላቅ የእግዚአብሔር ቃሎች በብሉይ ኪዳን ውስጥ አሉ። የመጀመሪያው "አብራምም በእግዚአብሔር አመነ ጽድቅም ሆኖ ተቆጠረለት።" ዘፍ 15፥6። ይህም "የማያወላውል ውሳኔን" ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ ማለት ሲሆን እርሱም ጽድቅ አድርጎ ቆጠረለት።

ይህ "የማያወላውል ውሳኔ" በሮሜ 10፥9-11 ጋር ተመሳሳይ ነው። "ኢየሱስ ጌታ እንደ ሆነ በአፍህ ብትመሰክር እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳነሣው በልብህ ብታመን ትድናለህና ሰው በልቡ አምኖ ይጸድቃልና በአፉም መስክሮ ይድናልና። መጽሐፍ ፦ በእርሱ የሚያምን ሁሉ አያፍርም ይላልና።"

ለጳውሎስ የተሰጠው የመገለጥ እምነት የኢየሱስን ጌትነት በአፋችን እንድንመሰክር ወይም እንድናውጅ ግድ የሚል ነው። ይህም ቃሉ በአካል የሌለውን የክርስቶስን ስፍራ ስለተካ "የማያወላውል ውሳኔ"ን ቃሉን ታምኖ መወሰንና ተግባራዊ ማድረግ ማለት ነው።

ሁለተኛው ቃል በኢሳይያስ 28፥16 "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ እነሆ በጽዮን ድንጋይን ለመሠረት አስቀምጣለሁ የተፈተነውን የከበረውን መሠረቱ የጸናውን የማእዘን ድንጋይ የሚያምንም አያፍርም።" የሚለው ነው። ሁለት ዓይነት ትርጉሞች አሉ አንደኛው "በእርሱ የሚያምን በመጨነቅ ሌላ መሰረትን ፍለጋ አይቅበዘበዝም።" የሚለው ሲሆን ሌላው ደግሞ "በእርሱ የሚያምን ሁሉ አያፍርም።" የሚለው ነው። ይህን የሚያደርግ ሁሉ አያፍርም ሲል ከሁኔታዎች ከመገለጫዎች ወይም ከስሜት መረጃዎች ባሻገር በፍጹም መታመን በቃሉ ላይ ያርፋል ማለቱ ነው።

ሦስተኛው ቃል "ጻድቅ ግን በእምነቱ በሕይወት ይኖራል።" ዕንባቆም 2፥4 የሚለው ነው። ይህ አንድ ርምጃ ወደ ፊት ይወስደናል። "ጻድቅ" የሚለው ቃል አዲስ ፍጥረት በመሆን ጽድቅ የሆነውን ሰው የሚገልጽ ነው። እርሱም በማየት በስሜት መመላለስ የለበትም ይልቅስ መመላለስ ያለበት በእምነት ነው። በሌላ አባባል መመላለስ ያለበት በቃሉ ነው ማለት ነው። ሁለተኛ ቆሮ 5፥7 "...በእምነት እንጂ በማየት አንመላለስምና..." ይላል።

"የእኔ ጻድቅ በእምነት ይኖራል ወደ ኋላም ቢያፈግፍግ ነፍሴ በእርሱ ደስ አይላትም።" (አምፕሊፋይድ እትም) ዕብ 10፥38። በእነዚህ በእያንዳንዱ የእግዚአብሔር ቃሎች ውስጥ መታመናችንን የሚገዳደር ነገር እንዳለ አስተዋላችሁ። እናንተ የእርሱ ጽድቅ ናችሁ። እናንተ በእምነት በሕይወት መኖር አለባችሁ።

እነዚህ ታላላቅ የእግዚአብሔር ቃሎች በጳውሎሳዊ መልእክቶች ውስጥ እንዴት በቃሉ ላይ በሆነ እምነት የጽድቅ መገለጥ መሰረት ሆነው እንደ ተገኙ ማየት ትችላላችሁ። ጳውሎስ በሮሜ ሰዎች መልእክቱ መጀመሪያ ላይ ላቀረበው ታላቁ ሙግት የአብርሃምን እምነት እንደ ምሳሌ አድርጎ መጠቀሙንም ታገኛላችሁ።

"መጽሐፍስ ምን አለ? አብርሃምም እግዚአብሔርን አመነ ጽድቅም ሆኖ ተቆጠረለት። ለሚሠራ ደመወዝ እንደ ዕዳ ነው እንጂ እንደ ጸጋ አይቆጠርለትም ነገር ግን ለማይሠራ ኃጢአተኛውንም በሚያጸድቅ ለሚያምን ሰው እምነቱ ጽድቅ ሆኖ ይቆጠርለታል።" ሮሜ 4፥3-5

ጽድቅ ማለት በእግዚአብሔር ሕልውና ፊት ካለ ኃጢአት ስሜት ኩነኔ ወይም የበታችነት ስሜት መቆም መቻል ማለት ነው። አብርሃም እግዚአብሔር እምነቱን ጽድቅ አድርጎ ከቆጠረለት በኋላ ለሰዶምና ገሞራ መዳን እንደ ማለደ ታስተውላላችሁ። ዘፍጥረት አስራ ስምንትን በጥንቃቄ አንብቡና የአብርሃምን ፍርሃት አልባ እምነት ተመልከቱ። እኛ ጻድቅ የሆነውን ያህል ጻድቅ አልነበረም። እርሱ ጻድቅ እንደ ሆነ ብቻ ነበር የተቆጠረለት። እንዲህ ሲባልም በአካውንቱ ውስጥ ተካተተለት። በእግዚአብሔርም ዘንድ ጽድቅ ሆኖ ተቆጠረለት ማለት ነው።

በሮሜ አራት ላይ ያነበብነው ቃል ጽድቅ በሥራ አማካኝነት እንደማይቆጠር ነግሮናል። የዚህ ጽድቅ ዋስትና እምነት ነው። ሰው ከእግዚአብሔር የጽድቅ ስጦታን ይቀበላል እንጂ ስለ ጽድቅ አይሠራም። “ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም።" ኤፌ 2፥8-9

ድነት፤ መዋጀት ወይም መቤዠት፤ የዘላለም ሕይወት፤ አዲስ ፍጥረትነት፤ የመንፈስ ቅዱስ ሕልውና ማደሪያ መሆን፤ የኢየሱስን ስም የመጠቀም ሕጋዊ መብት፤ የእግዚአብሔር ወንድና ሴቶች ልጆች በመሆናችን ያለን ልዩ ጥቅም ሁሉ መሰረት የሚያደርጉት በጸጋ የሆነውን እምነት ነው።

ማንም በጥረት ግረት አያገኘውም። አንዱም ከሌላው የተሻለ ስፍራ የለውም። ማንኛውም ግለ ሰብ ተመሳሳይ ጽድቅ ተመሳሳይ ልዩ ጥቅም በእግዚአብሔር ፊት የመቆም ተመሳሳይ መብት አለው ምክንያቱም ሁሉም ነገር ከጸጋው ነውና።

የአብርሃም እምነት በሮሜ ላይ እንዲህ ተብሎ ተገልጿል "ዘርህ እንዲህ ሊሆን ነው እንደተባለ ተስፋ ባልሆነው ጊዜ የብዙ አሕዛብ አባት እንዲሆን ተስፋን ይዞ አመነ።" ሮሜ

4፥18፡፡ ይህ አስደናቂ መግለጫ ነው፡፡ እምነት ከተስፋ ጋር ውጊያ ነበረው ሆኖም እምነት አሸነፈ፡፡ ተስፋ አብርሃምን ወንድ ልጅን ሊዘርፈው ነበር ነገር ግን እምነት ከተስፋ ጋር ተዋግቶ ድል በመንሳት ሽልማቱ የሆነውን ይስሃቅን ተቀበለ፡፡

ሮሜ 4፥19-21 "(የመቶ ዓመትም ሽማግሌ) ስለ ሆነ እንደ ምውት የሆነውን የራሱን ሥጋና የሳራ ማኅጸን ምውት መሆኑን በእምነቱ ሳይደክም ተመለከተ ለእግዚአብሔርም ክብር እየሰጠ የሰጠውንም ተስፋ ደግሞ ሊፈጽም እንዲችል አጥብቆ እየተረዳ በእምነት በረታ እንጂ በአለማመን ምክንያት በእግዚአብሔር ተስፋ ቃል አልተጠራጠረም፡፡"

ይህ የእምነት ቆንጆ ስዕል ነው፡፡ አብርሃም ከመለአኩ ቃል በስተቀር እርፍ ሊል የሚያስችለው ሌላ ምንም ነገር አልነበረውም፡፡ ይሁን እንጂ ቃሉን አምኖ ሰውነቱን ተመለከተና ለራሱ "እኔ ዘጠና ዘጠኝ ዓመቴ ነውና የልጅ አባት መሆን ከሚያስችለኝ ዕድሜ አልፌአለሁ፡፡" አለ፡፡ ዘጠና ዓመት የሆናትን ሳራንም አሰበና ልጅ ለመውለድ የማትችል እጅግ ያረጀች እንደ ሆነች አወቀ፡፡ ሆኖም ከስሜት ሕዋሳቶቹ መረጃዎች ዘወር አለና እግዚአብሔር በመለአኩ በኩል የተናገረውን ቃል ተመለከተ፡፡ ለእግዚአብሔርም ክብርን እየሰጠ በእምነቱ በረታ፡፡ ሳይጠራጠርና ሳይፈራ "እግዚአብሔር የሰጠኝን የተስፋ ቃል ይፈጽማል፡፡" ብሏልና፡፡ ይህ የስሜት እውቀት እምነት አይደለም፡፡ የመገለጥ እምነት እንጂ፡፡ ጳውሎስም በመገለጥ የሰጠን ይህን ዓይነቱን እምነት ነው፡፡ ቁጥር 22ን አስተውሉ "ስለዚህ ደግሞ ጽድቅ ሆኖ ተቆጠረለት፡፡" አብርሃም ጽድቅ ሆኖ ተቆጠረለት እንጂ እኛ ያለን ዓይነት ጽድቅ አልነበረውም፡፡

ሮሜ 4፥23-25 "ነገር ግን፡- ተቆጠረለት የሚለው ቃል ስለ እርሱ ብቻ የተነገረ አይደለም ስለ እኛም ነው እንጂ ስለ በደላችን አልፎ የተሰጠውን እኛን ስለ ማጽደቅም የተነሣውን ጌታችንን ኢየሱስን ከሙታን ባስነሣው ለምናምን ለእኛ ይቆጠርልን ዘንድ አለው፡፡"

የጳውሎስ መገለጥ እግዚአብሔር በክርስቶስ የሠራውን ፍጹም የሆነና የተጠናቀቀ የመዋጀት ወይም የመቤዠት ሥራ ያሳያል፡፡ "እርሱ ከጨለማ ሥልጣን አዳነን ቤዛነቱንም እርሱንም የኃጢአትን ስርየት ወዳገኘንበት ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግስት አፈለሰን፡፡" ቆላ 1፥13-14፡፡ "በውድ ልጁም እንደ ጸጋው ባለ ጠግነት መጠን በደሙ የተደረገ ቤዛነታችንን አገኘን እርሱም የበደላችን ስርየት፡፡" ኤፌ 1፥7፡፡ "ራሱም ጻድቅ እንዲሆን በኢየሱስም የሚያምነውን እንዲያጸድቅ አሁን በዚህ ዘመን ጽድቁን ያሳይ ዘንድ ነው፡፡" ሮሜ 3፥26

ይህ ቤዛነት ከሰይጣን አገዛዝ መዋጀት ነው፡፡ ደግሞም ከኩነኔና ከኃጢአት ቅጣት መዋጀት ነው፡፡ በክርስቶስ ኢየሱስ መፈጠር የአዲስ ፍጥረትነት መገለጥም ነው፡፡ ይህም ክርስቶስን አዳኛችን አድርገን ስንቀበልና ጌታችን መሆኑን ስናውጅ የሕይወታችን እውነታ ሆኗል፡፡ እግዚአብሔር ለፍጥረታዊው ሰው ሕይወቱንና ባሕርዩን ሰጥቶታል፡፡

"ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው አሮጌው ነገር አልፎአል እነሆ ሁሉም አዲስ ሆኖአል፡፡ ነገር ግን የሆነው ሁሉ በክርስቶስ ከራሱ ጋር ካስታረቀን

የማስታረቅም አገልግሎት ከሰጠን ከእግዚአብሔር ነው።።" ሁለተኛ ቆሮ 5፥17። "አሮጌውን ሰው አስወግዱ በአእምሮአችሁም መንፈስ ታደሱ ለእውነትም በሚሆኑ ጽድቅና ቅድስና እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረውን አዲሱን ሰው ልበሱ።።" ኤፌ 4፥23-24።

ይህ የአዲስ ፍጥረትነት መገለጥ እጅግ አስገራሚው የእግዚአብሔር ጸጋ እውነታ ማረጋገጫ ነው። እግዚአብሔር በሰይጣን የሚገዛን "ኃጢአት" ተብሎ የተጠራን ሰው (ምክንያቱም ከሰይጣን ጋር በመተባበር አንድ ስለ ሆነ የሰይጣን ልጅ ነው።) ሊዋጀው ወይም ሊቤዠው ደግሞም ከዚህ ሁኔታ ውስጥ አውጥቶ የራሱን ባሕርይ በማካፈል የራሱ ልጅ ሊያደርገው ይችላል።

አንደኛ ዮሐንስ 5፥12-13 ምንን እንደ ተቀበልን ይነግረናል። "ልጁ ያለው ሕይወት አለው የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ሕይወት የለውም። የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታውቁ ዘንድ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ለምታምኑ ይህን ጽፌላችኋለሁ።" "በእኔ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው።" ዮሐንስ 6፥47። አማኝነት ባለቤትነት ነው። ያለ ባለቤትነት አማኝነት የለም።

እኔ እግዚአብሔር ኃጢአቶቼን በኢየሱስ ላይ እንዳደረገና ኢየሱስም የእኔ ምትክ እንደ ሆነ በእኔም ፋንታ እንደ ሞተ ከሞት የተነሣበትም ምክንያት ኃጢአቴን በማስወገዱና ለእኔ ጽድቅን ስላስገኘልኝ መሆኑን ባመንኩበት ቅጽበት እኔ የዘላለምን ሕይወት በመቀበል የእግዚአብሔር ልጅ ሆንኩ ማለት ነው። ማመን ባለቤት መሆን ማለት ነው። (በክርስቶስ ለተከፈለለት ዋጋ ባለቤት መሆን ነው።) ቀጥሎ ጽድቅን ለእኛ ሰጠን። ይህም በኢየሱስ ላይ እምነት ላለው ሰው እንዲገኝ ሆኖ የቀረበ የእግዚአብሔር ጽድቅ መገለጥ ነው። (ሮሜ 3፥21-26)። እግዚአብሔር ኢየሱስን እንደ ግል አዳኙ አድርጎ ለሚወስድ ደግሞም የሕይወቱ ጌታና ሙሽራ ለሚያደርግ ሰው ጽድቅ ሆኖለታል።

"እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን ስለ እኛ ኃጢአት አደረገው።" ሁለተኛ ቆሮ 5፥21። እርሱ የእኛ ጽድቅ ብቻ አልሆነም ነገር ግን የባሕርዩ ተካፋይ አድርጎናልና እኛም የእርሱ ጽድቅ ወንዶችና ሴቶች ልጆቹ ሆነናል። "የእኔ ጻድቅ በእምነቱ በሕይወት ይኖራል።" ዕብ 10፥38 (አምፕሊፋይድ)። እኛ የእርሱ ጽድቅ ተብለንም ተጠርተናል።

ልብ በሉ እኛ የእግዚአብሔር ጽድቅ ብቻ አይደለንም ነገር ግን የእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆችም ሆነናል። እግዚአብሔር ለጳውሎስ የሰጠው የመጨረሻ ከፍተኛ ደረጃ መገለጥ በሮሜ 8፥14-17 ላይ የተመዘገበው ሲሆን ይህንን ጥርት አድርጎ ይገልጸዋል።

"በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ ሁሉ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና። አባ አባት ብለን የምንጮኽበትን የልጅነትን መንፈስ ተቀበላችሁ እንጂ እንደ ገና ለፍርሃት የባርነትን መንፈስ አልተቀበላችሁም። የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ

ከመንፈሳችን ጋር ይመሰክራል። ልጆች ከሆንን ወራሾች ደግሞ ነን ማለት የእግዚአብሔር ወራሾች ነን… ከክርስቶስ ጋር አብረን ወራሾች ነን።" ይህ ከከበረው አጠቃላይ ልዩ ጥቅማችን ጋር ልጅነታችንን ጥርት አድርጎ የሚያሳይ ነው።

ጳውሎስ እዚህ ላይ ብቻ አላቆመም። እነኚህ ወንዶችና ሴቶች ልጆች የእግዚአብሔር ባህርይ ተካፋዮች ብቻ ሳይሆኑ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት እግዚአብሔርን የወረሱ ናቸው በማለት ይቀጥላል።

"ነገር ግን ኢየሱስን ከሙታን ያስነሳው የእርሱ መንፈስ በእናንተ ዘንድ ቢኖር ክርስቶስ ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው እርሱ በእናንተ በሚኖረው በመንፈሱ ለሚሞተው ሰውነታችሁ ደግሞ ሕይወትን ይሰጠዋል።" ሮሜ 8፥11። "ወይስ ሥጋችሁ (ሰውነታችሁ) ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደ ሆነ አታውቁምን?" አንደኛ ቆሮ 6፥19።

ይህ ሁሉ ወደ አማኙ የሚመጣው በእምነት ነው። ምንም ዓይነት የእውቀት ስሜት እምነት አስፈላጊ አይደለም። ዳግም ለመወለዳችሁ ምንም ዓይነት የአምሰቱ ሐዋሳት ማረጋገጫ ስሜት አያስፈልጋችሁም። የሚያስፈልጋችሁ የእግዚአብሔር ቃል ብቻ ነው። "ኢየሱስ ጌታ እንደ ሆነ በአፍህ ብትመሰክር (ብታውጅ) እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህና።" ሮሜ 10፥9።

መንፈስ ቅዱስን ለመቀበላችሁም ምንም ዓይነት የስሜት እውቀት ማረጋገጫ አያስፈልጋችሁም። "በሰማይ ያለው አባት ለሚጠይቁት እንዴት አብልጦ መንፈስ ቅዱስን ይሰጣቸው?" ሉቃስ 11፥13። የእናንተ መተማመኛ ቀለል ብሎ የቀረበላችሁ ቅን የእግዚአብሔር ቃል እንጂ አካላዊ መገለጥ ወይም አካላዊ መረጃ አይደለም። "ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና።" (ሊፈጽመው ችሎታ አለው) ሉቃስ 1፥37። እነዚህ ኃይለኛ ቃሎች ለእምነት መሰረት ይሰጡታል። እኛ በክርስቶስ ማን እንደ ሆንን ስናውቅ እንተማመናለን።

እግዚአብሔር በክርስቶስ ያደረገልኝን ባየሁ ጊዜ ሁለንተናዬ ፈነጠዘ እምነትም ሳልጨናነቅ የምኖረው በመሆኑ እርሱ የእኔ ነበር ይህንንም ያደረገው ለእኔ ስለ ነበር እኔ "አባት ሆይ ተመስገን" በማለት በክርስቶስ ባለኝ መብት ሃሴት ማድረግ ጀመርኩ።

ምእራፍ ስድስት

ጥቂት የእምነት ጠላቶች

ውብ የሆኑ ጥቂት የእምነት ጠላቶችን ካልገለጥኩላችሁ በስተቀር ይህ መጽሐፍ ሙሉ አይሆንም። ቀዳሚው ጠላት ደግሞ "ተስፋ" ነው።

ተስፋ

ተስፋ ሁልጊዜ የወደፊት ወይም የመጪ ጊዜ አመላካች ነው፡፡ "እንደምፈወስ ተስፋ አደርጋለሁ" "ልከፍለው የምችለው ገንዘብ እንደማገኝ ተስፋ አደርጋለሁ" "ሥራዬን ለመሥራት የሚያስችል ኃይል እንደማገኝ ተስፋ አደርጋለሁ" እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉ ቃሎች የእምነት ውብ ጠላቶች ናቸው፡፡ እነዚህ በእምነት መንገድ ላይ የተጋረጡ ደንቃራዎች ናቸው፡፡

እኔ "ስጸልይልህ ትፈወሳለህን?" ስል እናንተ "ተስፋ አደርጋለሁ" ብላችሁ ከመለሳችሁ አትፈወሱም ማለት ነው፡፡ በተስፋ ውስጥ ፈውስ የለም፡፡ እምነትን በተመለከተ ተስፋ ከንቱ ቅዠት ነው፡፡ እምነት ሁሌም የአሁን ጊዜ ነው፡፡ ተስፋ ደግሞ የወደፊት የመጪው ጊዜ አመላካች ነው፡፡ ስለዚህ ተስፋ የእምነት እንቅፋት ነው፡፡ በርግጥ እኛ የመንግስተ ሰማይ ተስፋ አለን፡፡ መንግስተ ሰማይ ከደረስን በኋላ ግን ተስፋ ማድረግ እናቆማለን ማለት ነው፡፡

## አእምሮአዊ ስምምነት

አእምሮአዊ ስምምነት ሌላው ሙልጭ ያለ አጭበርባሪ አደገኛ የእምነት ጠላት ነው፡፡ አእምሮአዊ ስምምነት ሙሉ ለሙሉ መጽሐፍ ቅዱስ እውነት መሆኑን ይቀበላል፡፡ በአእምሮ ስምምነት ስር ያሉ ሁሉ ቃሉን በሙሉ እናምናለን ይላሉ ነገር ግን ቃሉን ታምነው አይቆሙም ወይም አይተገብሩም፡፡ እነርሱ እንዲያው ቃሉ እውነት ስለ መሆኑ ብቻ ይስማማሉ፡፡

ካንሰር ላለባት አንዲት ሴት እንድጸልይ ተጠራሁ፡፡ ሁለቱም ማለትም እርሷና ባለቤቷ ለዓመታት  ታዋቂ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪዎች ነበሩ፡፡ በአልጋዋ አጠገብ ተቀምጬ ቃሉን ስገልጥ በማከታተል "ይህንን ምንጊዜም አምናለሁ፡፡ ይህንን ቃል ደግሞ ከልጅነቴ ጀምሮ የማውቀው ነው፡፡" ትላለች፡፡ እኔም ግራ በመጋባትና በሸንፈት ከቤቱ ወጥቼ ሄድኩ፡፡ ችግሩ የትጋ እንዳለ ለማወቅ አልቻልኩም፡፡

እቤት እንደ ደረስኩ ክፍሌ ውስጥ ወዲያና ወዲህ እየተንቆራጠጥኩ "ጌታ ሆይ እርሷ ስለ ምን አልተፈወሰችም? መልካም ሴት ናት፡፡ ቃልህን አምናለሁ ብላለች ደግሞም ለዓመታት የቃልህ አስተማሪ ነበረች፡፡" አልኩት፡፡ ከዚያም መንፈስ ቅዱስ እርሷ ከቃሉ ጋር አእምሮአዊ ስምምነት ብቻ እንዳደረገች እንዳይ አደረገኝ፡፡ እርሷ ቃሉን አላመነችም! ማመን በቃሉ ላይ መቆም ወይም ቃሉን ተግባራዊ ማድረግ ነው፡፡ ለፈውሷ በቃሉ ላይ በመቆም ተግባራዊ ርምጃ አልወሰደችም፡፡ ከጥቂት ቀን በኋላ ወደ ቤቷ ሄደኩኝ፡፡ በእዚህ ጊዜ ግን ችግሯን ተረድቻለሁ፡፡

እኔ ልክ ቃሉን መግለጥ ስጀምር "ይህንንማ ሕይወቴን በሙሉ ሳምን ነው የኖርኩት፡፡" አለች፡፡ እኔም "የለም በፍጹም አላመንሽም፡፡ አምነሽ ቢሆንማ ኖሮ ከአልጋ ተላቅቀሽ ሥራሽን እየሠራሽ በተገኘሽ ነበር፡፡ አንቺ ከቃሉ ጋር የተስማማሽው በአእምሮ ብቻ ነው፡፡" ብዬ ነገርኳት፡፡ ከዚያ በድጋሚ ቃሉን መግለጥ ጀመርኩ፡፡ እርሷም "በርግጥ

እውነት ነው፡፡ ቃሉን አላመንኩትም፡፡ እንዴት እንዳላመንኩትም አሁን ማየት ቻልኩ፡፡ ምንጊዜም ከቃሉ ጋር በአእምሮዬ ብቻ እየተስማማሁ ነበር ማለት ነው፡፡" አለች፡፡ በአብዛኛው የብዙ አማኝ ወንዶችና ሴቶች ጉዳይ ከእምነት ይልቅ አእምሮአዊ ስምምነት ሆኖ ታገኙታላችሁ፡፡ የራሳቸው የሆነ እምነት ወይም ቀኖና የቃሉን እውነት ስፍራ ተክቶታል፡፡

## የስሜት እውቀት እምነት

የስሜት እውቀት እምነት የአምስቱ ስሜት ሕዋሳትን መረጃ ይፈልጋል፡፡ በዮሐንስ 20፥25 ላይ ቶማስ "የችንካሩን ምልከት በእጆቹ ካላየሁ ጣቴንም በችንካሩ ካላገባሁ አላምንም፡፡" ባለ ጊዜ የነበረው እምነት እንዲህ ዓይነት ነበር፡፡ ሆኖም ኢየሱስ ድንገት ተገለጠና "ከዚያም በኋላ ቶማስን፡- ጣትህን ወደዚህ አምጣና እጆቼን እይ እጅህንም አምጣና በጎኔ አግባው ያመንህ ሁን እንጂ ያላመንህ አትሁን አለው፡፡" ዮሐ 20፥27፡፡

እዚህ ላይ እነዚህን ሁለት የእምነት ዓይነቶች በተነጻጻሪነት እናያለን፡፡ ኢየሱስ በምድር ላይ በአካል በተመላለሰበት ጊዜ ማርታና ማርያም እንዲሁም ሌሎችን ጨምሮ የነበራቸው የስሜት እውቀት እምነት ነበር፡፡ በኢየሱስ ያመኑበትም ምክንያት ያደርገው የነበረውን ተአምራት በማየት ነበር፡፡ አይሁዶች "እንግዲህ፡- እንኪያ አይተን እንድናምንህ አንተ ምን ምልክት ታደርጋለህ? ምንስ ትሠራለህ?" ዮሐ 6፥30 አሉ፡፡

ይህ የስሜት እውቀት እምነት እውነተኛውን እምነት ጥቂት እስኪቀረው ድረስ ከቤተ ክርስቲያን ሙልጭ አድርጎ ጨርሶ አስወጥቷል፡፡ ይህ ዓይነት እምነት ትክክለኛውን ስፍራ ለቃሉ አይሰጥም፡፡ ሰዎች ቃሉን ይዘው ወደ ቤተ ክርስቲያን ይሄዳሉ ነገር ግን አይታመኑትም፡፡ በሚዳስሱት በአእምሮአዊ ስሜታቸው ሊያዩት ሊሰሙት ሊቀምሱት ወይም ሊያሸትቱት በሚችሉት ነገሮች ላይ ይታመናሉ፡፡ እውነተኛ እምነት ስሜታዊ ማረጋገጫን ሳይደገፍ በቃሉ ላይ በመቆም መተግበር ነው፡፡

ሁለት ዓይነት አለማመኖች አሉ፡፡

ቀዳሚው እውቀት ከማጣት የተነሳ የሚመጣ ነው፡፡ ሰው ስለ ቃሉ ምንም ባለማወቁ ምክንያት አያምንም፡፡ ስለዚህ ለእርሱ የመጣውን የአብ መገለጥ አያምንም፡፡ እጅግ ብዙ ቁጥር ያላቸው አላማኞች ማመን የተገባቸውን አያውቁም፡፡ አያውቁም እናም ሊያምኑ አይችሉም፡፡

ሁለተኛው የአለማማን ዓይነት በዕብራውያን 4፥11 መሰረት "ዳተኛነት" ነው፡፡ "እንግዲህ እንደዚያ እንደ አለመታዘዝ ምሳሌ ማንም እንዳይወድቅ ወደዚያ ዕረፍት ለመግባት እንትጋ፡፡" (በኪንግ ጄምስ ትርጉም የግሪኩ ቃል "አለማመን" ተብሎ ተተርጉሟል፡፡ በአምፕሊፋይድ "አለመታዘዝ" ተብሎ ተተርጉሟል፡፡ ይህም "ዳተኝነት" ነው)

ይህም ሰውዬው ቃሉ እንዲገዛው ፈቃደኛ አይደለም ማለት ነው፡፡ በእውቀት ለመቆም እምቢተኛ መሆን ነው፡፡ ቃሉ ምን እንደሚያስተምር ያውቃል ነገር ግን ለመቆምና ተግባራዊ ለማድረግ አሻፈረኝ ባይ ነው፡፡

ማመን በፈቃደኝነት የሚደረግ ተግባራዊ አቋም ነው፡፡ ሰው ፈቃደኛ ከሆነ ብቻ ተግባራዊ ያደርገዋል፡፡ "ማመን" ቃሉን ለማድረግ "ፈቃደኝነት ነው፡፡" አለመታዘዝ ለቃሉ ዳተኛ የመሆን ዝንባሌ ነው፡፡ ስለሆነም አለማመን የቃሉ እውቀት ጉድለት ወይም ቃሉን ተግባራዊ ያለማድረግ ዳተኝነት ነው፡፡

## ምእራፍ ሰባት

## እምነት በራሳችሁ እምነት ላይ

በራሳችሁ ውስጥ ባለው እምነት ላይ መታመን በመንፈሳዊው ዓለም ውስጥ የስኬት ሕግ ነው፡፡ ይኸውም እናንተ በቃሉ ትኖራላችሁ ቃሉም በእናንተ ውስጥ ይኖራል፡፡ የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነው፡፡ ቃሉን በውስጣችሁ ስትለቅቁት በውስጣችሁ እግዚአብሔርን እንደ መልቅቅ ነው፡፡ ቃሉን ተግባራዊ ለመድረግ ስትነሱ ቃሉን ስትናገሩና ስታውጁ እግዚአብሔር በምትናገሩትና በምታውጁት ቃሎች ውስጥ ይገኛል ይገለጣል፡፡

ቃሉ በሕይወታችሁ የበላይነትን ባገኘ ጊዜ ሳትጨናነቁ እርሱን ልታምኑ የምትችሉበት እምነት ይኖራችኋል፡፡ ፈጽማችሁ ትታመኑታላችሁ ስለሆነም ወሰን አልባ የቃሉ ጥግ ድረስ ትሄዳላችሁ፡፡ ሰው ራሱን ቃሉ ላይ በመጣል በፍጹም ነጻነት ሲመላለስና "በዓለም ካለው ይልቅ በእናንተ ያለው ታላቅ ነውና" የሚለው ቃል በሕይወቱ እውነተኛ ሃሴት እስኪሆን ድረስ እግዚአብሔርን በውስጡ ሲለቅቀው እጅግ ያማረና ውብ ነው፡፡

አንደኛ ቆርንቶስ 2፥12 ከእግዚአብሔር እንዲያው በነጻ የተሰጠንን እንድናውቅ ከእግዚአብሔር መንፈስ እንደ ተቀበልን ይነግረናል፡፡ "እኛ ግን ከእግዚአብሔር እንዲያው የተሰጠንን እናውቅ ዘንድ ከእግዚአብሔር የሆነውን መንፈስ እንጂ የዓለምን መንፈስ አልተቀበልንም፡፡"

የእናንተ የሆነውን ስፍራችሁን መብቶቻችሁን ልዩ ጥቅሞቻችሁንና ሥልጣናችሁን እወቁ፡፡ ከዚያ በኋላ የእምነት ችግር የሚባል አይኖርም፡፡ እምነት ችግር የሚሆነው ጌታን ሳናውቅ ስንቀርና ቃሉን በመረዳት ባለጠግነት ሳንረዳ ስንመላለስ ብቻ ነው፡፡ በውስጣችሁ ላለው እግዚአብሔር ተገቢውን ስፍራ ስጡት፡፡ እግዚአብሔር በወስጣችሁ እንዳለ ቁጠሩ አስቡ እወቁ፡፡

ማለዳ ከእንቅልፋችሁ እንደ ነቃችሁ "ይህንና ያንን ማድረግ እችላለሁ ምክንያቱም እርሱ በውስጤ አለና፡፡ ከሰዎች ጋር እንድገናኝ ያስችለኛል፡፡ ቃሉን እንድናገር ያስችለኛል፡፡ በፍቅር እንድመላለስ ያደርገኛል ምክንያቱም በውስጤ ያለው ፍቅር በዙሪያዬ ካለው ቅናትና ጥላቻ እጅግ ይበልጣልና፡፡" በሉ፡፡ በውስጣችሁ ያለውን እግዚአብሔር ቁጠሩ

አስቡ እወቁ ተደገፉ፡፡ በውስጣችሁ ያለው የእርሱ ችሎታ ሊፈጽመው እንደሚችል በንቁ ኅሊና በማወቅ ሥራችሁን አቅዱ፡፡

እርሱ ሕያው እውነታ ሆኖአል፡፡ እርሱ በውስጣችሁ አለ፡፡ የሚገባችሁን እስክትጠይቁ ድረስ እየጠበቃችሁ ነው፡፡ ፍላጎታችሁ የሚሻውን ለመሙላት እርሱ ራሱን ይገልጣል፡፡ ቃሉን ለጥቂት ደቂቃ ባሰባችሁ ቁጥር በውስጣችሁ ያለው ብርሃን ቃሉን በመክፈት ሕያው እንደሚያደርገው አውቃችኋልና እናንተ እርሱ ወደ እውነቶች ሁሉ እንዲመራችሁ ትጠባበቁታላችሁ፡፡

የዮሐንስ 16፥13ን ፍጹም እውነትነት ታውቃላችሁ፡፡ "ግን እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል፡፡" እርሱ የአብ የሆነውን ሁሉ አምጥቶ ለእናንተ ይገልጥላችኋል፡፡ እናንተ በአፋችሁ ስሙን ስታውጁ ያልተጨናነቀ መታመን አላችሁ ማለት ነው፡፡ እናንተ "በኢየሱስ ስም አንተ አጋንንት ከዚህ ሰውዬ ወይም ሴት ውጣ" ስትሉ እንደሚወጣ አውቃችኋል፡፡

አንድን ደዌ ሕልውናው እንዲያበቃ ስታዝዙት እንደሚቆም አውቃችኋል፡፡ ፋይናንስን አስመልክቶ የኢየሱስ ክርስቶስን ስም አንስታችሁ አብ በዙፋኑ ላይ ለመሆኑ የተረጋገጠውን ያህል ግዴታችሁን እንድትወጡ ይመጣል፡፡ በእናንተ አንደበት ያለው ቃል የጠፉትን እንደሚያድን በሽተኞችን እንደሚፈውስ ለደከሙ መበርታትንና ኃይልን ለተሸነፉ ድልን እንደሚሰጥ አውቃችኋል፡፡

ይህ ቃል ከዕለታት አንድ ቀን በኢየሱስ አንደበት የነበረ የእግዚአብሔር ቃል ነበረ፡፡ አሁን ግን በእናንተ አንደበት ያለ የእግዚአብሔር ቃል ነው፡፡ ኢየሱስ በአንደበቱ የነበረውን የእግዚእብሔርን ቃል ያምን ነበር፡፡ እናንተ በቃሉ ላይ ያላችሁ መታመን በአንደበታችሁ ላይ ሕያው እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ ቃሉ በልባችሁ የበላይነቱን ስፍራ ሲይዝ ሕይወት እንዴት ወድ ያማረና ውብ ነው፡፡

እምነታችሁ ነገሮችን እንደሚፈጽም ደግሞም የፍቅርን ጆሮ ለመድረስ እንደምትችሉ በውስጣችሁ ባለው ችሎታ ስታምኑ ለእናንተ ታላቅ ቀን ይሆናል፡፡ ጸሎታችሁ እንደ ተመለሰ እግዚአብሔር እንደሰማችሁ ስታውቁ የራሳችሁ እምነት አላችሁና በሌሎች ሰዎች እምነት ላይ መደገፋችሁ ያበቃል፡፡ እየደጋገማችሁ "በመጨረሻ በራሴ እምነት ላይ እምነት አለኝ፡፡ እንደ ማንኛውም አማኝ እግዚአብሔርን ላገኝ እችላለሁ" በሉ፡፡

አንድ ወዳጃችሁ ድንገት በሆነ ነገር ከተያዘ ያለ ምንም ፍራቻ መብታችሁን ተጠቅማችሁ ከጠላት ትታደጉታላችሁ ጸሎታችሁ ዘልቆ ያልፋል እምነታችሁም ያሸንፋል፡፡ አሁን እንደ ማንኛውም አማኝ የኢየሱስን ስም መጠቀም ትችላላችሁ፡፡ በመጨረሻ ያ ስም "ከሙሉ ሥልጣኑ" ጋር የእናንተ ሆኗልና የራሳችሁ አድርጋችሁ ለመጠቀም ድፈሩ፡፡ እርሱ እንድትጠቀሙበት ሰጥቷችኋልና እናንተ በልበ ሙሉነት ተገልገሉበት፡፡

እውቀትን እንዴት አድርጋችሁ መጠቀም እንዳለባችሁ እስካላወቃችሁ ድረስ ዋጋ አልባ ነው፡፡ እናንተ ግን በአብ ዘንድ ያላችሁን የመቆም መብት ያላችሁንም ልዩ ጥቅም አውቃችኋል ስለሆነም አሁኑኑ ተግባራዊ አድርጉት፡፡

## እምነት በሌሎች እምነት ላይ

የብዙሃን የተባበረ እምነትና ቅባት ባለበት በታላላቅ ጉባኤ ላይ የተፈወሱ አብዛኛዎቹ ሰዎች ፈውሳቸውን በደንብ ተንከባክበው ማቀየት በፍጹም አልቻሉም፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ግልጽ ነው፡፡ በግላዊ እምነታቸው ላይ ስላልተደገፉና ልባቸው በሌሎች ሰዎች እምነት ላይ የተንጠለጠለ ስለሆነ ነው፡፡

ወደ ሎስ አንጀለስ ባደረግነው የመጨረሻ ጉዞ ላይ ጌታ በእጅጉ የሚጠቀምበት ክርስቲያን ሠራተኛ "ለዘመናት ወዳጆቼ ለነበሩ ሰዎች የጸለይኩት ጸሎት ለምን እንዳልተሰማ አልገባኝም፡፡ ቀደም ሲል ለእነርሱ በጸለይኩላቸው ቁጥር ይፈወሱ ነበር፡፡" አለኝ፡፡ እኔም "ችግሩ በርግጥ ያለው እነኚህ የታመሙ ወገኖች ራሳቸው ከጊዜው የተነሳ ለታመሙ መጸለይ ሲገባቸው እነርሱ ለራሳቸው የሚጸልይላቸው መሻታቸው ነው፡፡" አልኩት፡፡

ልክ በዕብራውያን 5፥12 ላይ መንፈስ እንዲህ ሲል እንደሚናገረው ማለት ነው፡፡ "ከጊዜው የተነሳ አስተማሪዎች ልትሆኑ ሲገባችሁ አንድ ሰው ስለ እግዚአብሔር ቃላት መጀመሪያ ያለውን የሕፃንነትን ትምሕርት እንዲያስተምራችሁ እንደገና ያስፈልጋችኋልና የሚያስፈልጋችሁም ወተት ነው እንጂ ጠንካራ ምግብ አይደለም፡፡"

ማንኛውም ወተት የሚጋት ሁሉ በስሜት ዓለም ውስጥ ይኖራል ከቃሉም ይልቅ በስሜት ሕዋሳት መረጃ ላይ ይደገፋል የጽድቅ ቃል ልምምድ የለውምና አሁንም ጨቅላ ሕጻን ነው፡፡ ይህ ምን ማለት ነው? እግዚአብሔር ለዓመታት በሌላ ሰው እምነት የተፈወሱ እነዚያ ሰዎች እነርሱ የራሳቸው እምነት እንዲኖራቸው የሚሻበት ጊዜ ላይ ደርሰዋል ማለት ነው፡፡

እነርሱ ቃሉን ለማጥናት አሻፈረኝ ካሉ የእምነት ሕይወታቸውን ለማሳደግም እምቢተኛ ከሆኑ ወደ "ሥጋ ለባሽ ክንድ" ይመለሳሉ እርሱን ተከትሎ የሚመጣውም ችግር ይደርስባቸዋል፡፡ እግዚአብሔር እያንዳንዳችን የጽድቅ ቃል ልምምድ እንዲኖረን ይጠብቅብናል፡፡ በሌላ አባባል እኛ ለታመሙ ወገኖች የመጸለይ ልምድ ቃሉን የማወጅ ሰዎችን ወደ ክርስቶስ መምራትና ቃሉን መግለጥን ይጠብቅብናል ማለት ነው፡፡

ይህ ለሁሉ አማኝ የተሰጠ ነው፡፡ "በቅዱሳንም ርስት በብርሃን እንድንካፈል ያበቃንን አብን እያመሰገናችሁ" ቆላ 1፥12፡፡ ከዚህ የተሻለው ትርጉም "ከቅዱሳን ጋር በብርሃን የርስታችንን ድርሻ እንድንካፈል ብቃት የሰጠንን አብን እያመሰገንን" ይላል፡፡ እርሱ ከጨለማ ሥልጣን አድኖአችኋል፡፡ እርሱ መንፈሳችሁን ፈጥሯል፡፡

አሁን ደግሞ እርሱ በክርስቶስ ያላችሁን ልዩ ጥቅሞችና መብታችሁን እንድትረዱ አእምሮአችሁን ለማደስ ዝግጁ ነው። አሁን የራሳቸሁ እምነት አላችሁና በሌላ ሰው እምነት ከመደገፍ ይልቅ ተደሰቱበት። ይህን መጽሐፍ የሚያነቡ "በእግዚአብሔር ጸጋ የራሴ እምነት አለኝ" በለው ቢያውጁ ምን ዓይነት ጊዜ በሆነ! የእናንተ ነውና ከእርሱ መብት አላችሁ።

እናንተ የእኔ ዓይነት ተመሳሳይ መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስ የነበረው ዓይነት መንፈስ ቅዱስ ሐዋርያቱ የነበራቸው ዓይነት መንፈስ ቅዱስ አላችሁ። ተመሳሳይ የዘላለም ሕይወት ተመሳሳይ ጽድቅ ተመሳሳይ ችሎታ አላችሁ። አብ በለጥ አድርጎ የሚያዳላለት ማንም የለውም። ይህ ሁሉ የእያንዳንዳችን ስለ ሆነ መካንና ፍሬ አልባ መሆን የለብንም።

"እግዚአብሔር ሁልጊዜ በነገር ሁሉ ብቃትን ሁሉ አግኝታችሁ ለበጎ ሥራ ሁሉ ትበዙ ዘንድ ጸጋን ሊያበዛላችሁ ይችላል።" ሁለተኛ ቆሮ 9፥8። በቁጥር 10 ላይ ደግሞ "ለዘሪ ዘርን ለመብላትም እንጀራን በብዙ የሚሰጥ እርሱም የምትዘሩትን ዘር ይሰጣችኋል የጽድቃችሁንም ፍሬ ያሳድጋል" ይላል።

እናንተ በአዲስ ውልደት የአብን ጽድቅ ባሕርይ ተካፍላችኋል ስለሆነም ይህን በክርስቶስ ዙፋን ፊት የመቆም ዕድል ተጠቅማችሁ ለታመሙና ለተቸገሩ መጸለይ ጀምሩ። እናንተ ጳውሎስ በእግዚአብሔር ፊት ለመቆም ያለው ሕጋዊ መብትና እርሱ ያለው ተመሳሳይ ጽድቅ አላችሁ ስለዚህ መብራታችሁን ለመደበቅ ምንም ዓይነት ምክንያት የላችሁም። በክርስቶስ ውስጥ ያላችሁን ማንነት መመስከር ጀምሩ።

ምእራፍ ስምንት

ተስማሚ ተግባራት

የዊማውዝ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ያዕቆብ 2፥14ን በአስደናቂ ሁኔታ እንዲህ በማለት ይገልጽልናል "ወንድሞች ሆይ አንድ ሰው እምነት እንዳለው ቢናገርና ሆኖም ግን ተስማሚ ተግባር ከሌለው ምን መልካምነት አለው።" በቁጥር 18 ላይ ደግሞ "የእርሱ እምነት ከተግባሩ ጋር እንደ ተባበረ በዚህ ተግባሩም እምነቱ ፍጹም እንደ ሆነ ታስተውላላችሁ።"

ብዙ አማኞች የሚፈጽሙት ትልቁ ስህተት በቃሉ ላይ ያላቸውን እምነት ማወጃቸውና በተመሳሳይ ጊዜም አዋጃቸውን በተሳሳተ ተግባር መቃረናቸው ነው። አንዲት ሴት "መጽሐፍ ቅዱስ እውነት እንደ ሆነ አውቃለሁ። እኔ ጸለይኩ ጸለይኩ ነገር ግን ለምን እንዳልተፈወስኩ መረዳት አልቻልኩም።" አለች። እኔም "አሁንም መድኃኒት እየወሰድሽ ነውን?" ስል ጠየቅኳት። "አዎን።" አለች። ስለዚህ ቀደም ሲል የጠቀስኩትን ቃል አነበብኩላት። ተግባሯ ከአዋጇ ጋር የተስማማ አይደለም። ጌታን እታመነዋለሁ ትላለች ሆኖም የታመነችው መድኃኒቱን እንጂ የእርሱን ቃል አልነበረም።

እኛ ስለ ፋይናንስ መሻታችን አብን እንታመናለን እንላለን ሆኖም በተመሳሳይ ቅጽበታዊ ጊዜ ክፍያውን ከየት አምጥተን እንከፍላለን ብለን እንጨነቃለን እንሰጋለን፡፡ በአንደኛው ደቂቃ ከእግዚአብሔር የወጣ ቃል በፍጹም ሊሻር አይችልም እርሱ ለእኛ የገባውን ቃል ይጠብቃል እንዲህ አንደሚያደርግም እናውቃለን በማለት እናውጃለን በቀጣዩ ደቂቃ ደግሞ ያወጅነውን ሁሉ በማይስማማ ተግባር እንክደዋለን፡፡

ያዕቆብ የግድ ተስማሚ ተግባር ሊኖረን እንደሚገባ ነግሮናል፡፡ "ቃሉን የምታደርጉ ሁኑ እንጂ ራሳችሁን እያሳታችሁ የምትሰሙ ብቻ አትሁኑ፡፡" ያዕ 1፥22፡፡ የ"ቃሉን አድራጊ" ተግባር ከአዋጁ ጋር አብሮ ይሄዳል ወይም ይስማማል፡፡ ኢየሱስ በማቴዎስ 7፥24-27 ላይ እንዲህ አለ "ስለዚህ ይህን ቃሌን ሰምቶ የሚያደርገው ሁሉ ቤቱን በዓለት ላይ የሠራ ልባም ሰውን ይመስላል፡፡ ዝናብም ወረደ ጐርፍም መጣ ነፋስም ነፈሰ ያንም ቤት ገፋው በዓለት ላይም ስለ ተመሰረተ አልወደቀም፡፡" ቁጥር 24-25፡፡ "ይህንም ቃሌን ሰምቶ የማያደርገው ሰው ሁሉ ቤቱን በአሸዋ ላይ የሠራ ሰነፍ ሰውን የመስላል፡፡ ዝናብም ወረደ ጐርፍም መጣ ነፋስም ነፈሰ ያንም ቤት መታው ወደቀም አወዳደቁም ታላቅ ሆነ፡፡" ቁጥር 26-27፡፡

ክርስቶስን እናውቃለን ከዘፍጥረት እስከ ራዕይ ድረስ ያለውን ቃል እናምናለን የሚሉና የሚያውጁ ራሳቸውን እጅግ የሚያጋንኑ ብዙዎች ቃሉን አድራጊዎች ሳይሆኑ ቃሉ እውነት መሆኑን በአእምሮ የተስማሙ ብቻ ናቸው፡፡ የራሳቸው እያደረጉት አይደለምና ይህ ምንም አይጠቅማቸውም፡፡

እኔ በሙሉ ልቤ ቃሉን ስታመንና በስሜታዊ ምክንያት መደገፌን ለአርነትም ሰዎችን መፈለጌን ሳቆም ያኔ ከቃሉ ጋር የተስማማ ተግባር አለኝ፡፡ ተግባራቴም ከአዋጄ ጋር ፍጹም የሆነ ጎብረት አለው፡፡ ጥቂቶቻችን ከአዋጆቻችን ጋር የሚጣጣም ተግባር ሊኖረን ረዘም ያለ ጊዜ ወስዶብናል፡፡ የሚጣጣም ተግባር እስከ ሌለን ጊዜ ድረስም የማያቋርጥ ወድቀት ያጋጥመናል፡፡

እኔ የፈለኩትን ያህል እየጮኹክ እግዚአብሔር የሕይወቴ መታመኛ ኃይል ነው በማለት ላውጅ እችላለሁ ሆኖም በተመሳሳይ ጊዜ ስለ ድካሜ ስለ አለመቻሌና ስለ እምነት ማጣቴ ከተናገርኩ በዚህ አካሄዴ ውስጥ ምንም ዓይነት ተስማሚ ተግባር የለም ማለት ነው፡፡ በጌታ ላይ ሙሉ ለሙሉ ከመታመን ይልቅ ዘለቄታ በሌለው ፍጥረታዊው ስው ዘዴና ጥበብ እየተዝናናሁ ሲሆን ይህም ለመንፈሴ ብዥታንና ውዥንበርን ለሕይወቴ ድካምና ውድቀትን ሄዶ የማምጣት ያህል ነው፡፡

ወደ ቆራጡ አንደኛ ጴጥሮስ 5፥7 እንሂድ "እርሱ ስለ እናንተ ያስባልና የሚያስጨንቃችሁን ሁሉ በእርሱ ላይ ጣሉት፡፡" ይላል፡፡ ሁኔታን ግምት ውስጥ ሳናካትት የእኛን ተሰሚነትና አግባቢነት ግምት ውስጥ ሳናስገባ ችግሮቻችንን በሙሉ ለእርሱ እናስረክበው፡፡ የእናንተ

ክፉ ጠላት ራሳችሁ ናችሁ። ችግሩ ደግሞ በራሳችሁ ብቃት እንድትወሰኑ ለማድረግ በስሜት አውቀት እንድትደገፉ ወደ እናንተ የመጣው እምነት ነው።

የስሜት ቋንቋ "አልችልም፤ ብቃት የለኝም፤ ኃይል የለኝም፤ ምቹ አጋጣሚ አልተፈጠረልኝም፤ የተማርኩ አይደለሁም፤ ውሱን ነኝ።" የሚል እንደዚህ የመሳሰሉ ስሜታዊ ምክንያቶችን የሚደረድር ነው።

የእምነት ቋንቋ ደግሞ "ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ።" ነው። ኃይልን የሚሰጠኝ ማነው? አባቴ እግዚአብሔር ነው። ስለዚህ በእርሱ ሁሉን ማድረግ እችላለሁና ልረታ ወይም ልሸነፍ አልችልም። በእኔ ውስጥ ያለውን እርሱን ሊያሸንፍ የሚችል በቂ ኃይል በመላው ዓለም ዙሪያ የለም ይላል።

ከእግዚአብሔር መወለድና የባሕርዩ እንዲሁም የሕይወቱ ተካፋይ የሆንኩኝ ብቻ ሳልሆን እግዚአብሔር በውስጤ ይኖራልና ኢየሱስን ከሙታን ያስነሳው መንፈስ በውስጤ አለኝ። እኔ የእግዚአብሔር ጥበብ የእግዚአብሔር ኃይል የእግዚአብሔር ብቃት አለኝ። እኔ እርሱ አእምሮዬን እንዲገዛ በእኔ እንዲያስብ አንደበቴን እንዲጠቀምበት እንዴት እንደምፈቅድለት ተምሬአለሁ። ስለሆነም እኔ ከአርሱ ቀጥዬ የእርሱን አሳብ ለማሰብ ደፍሬአለሁ።

እኔ በእኔ ውስጥ የሚሠራው እግዚአብሔር መሆኑንና ስለ በጎ ፈቃዱ መፈለግንም ማድረግንም የሚሠራ እርሱ እንደሆነ ለማመን ደፍሬአለሁ። በጥንት ጠላቶቼ በውድቀት፤ ድካም፤ እጦት፤ ዕድል ማጣት፤ እውቀት አልባነት፤ የእውነተኛ ወዳጆች እጥረትና እንዲሁም ሌሎች ሺህ ነገሮች ሕልውና ፊት "እግዚአብሔር ብቃቴ ነው" ለማለት ደፋር ሆኛለሁ። እግዚአብሔር ከጠላቶቼ በላይ አድርጎኛል።

እግዚአብሔር በድካም በብቃት የለሽነትና ፍርሃት አንገት ላይ እንድጫማና በእርሱ የሚያምን ሁሉ አያፍርም በማለት እንዳውጅ አድርጎኛል። እኔ አላፍርም። ድካሜ ተነቅሏል። የእግዚአብሔር ኃይል የእኔ ነው። የእግዚአብሔር ብቃት ምርኮኛ አድርጎ ይዞኛልና በምርኮኛነቴ እቦርቃለሁ። ይህ እውነተኛ ተስማሚ ተግባር የእምነት ንግግር ነው።

ምእራፍ ዘጠኝ

ሰው በልቡ ያምናል

ለዓመታት በሮሜ ፲፥፲ "ሰው በልቡ አምኖ ይጸድቃል" ስለሚለው ቃል አመርቂ ማብራሪያ ለማግኘት በጉጉት ስመረምር ነበር። "ልብ" የሚለውን ቃል በማሳያነት እንደ ተጠቀመበት ትረዳላችሁ ምክንያቱም ልብ አካላዊው ሰውነት እንዲኖር ደም የሚያቀርብ ታላቅ መርጪያ ጣቢያ ስለ ሆነ የሰው ሕይወት ማዕከል ነው። እኛም እግዚአብሔር ስለ ልብ ሲናገር ስለ ሰው መንፈስ እንደ ሆነ አውቀናል። ሰውም መንፈስ እንደ ሆነ ነፍስ

እንዳለው በሰውነት ውስጥ እንደሚያድር እናውቃለን፡፡ ሰው ከእግዚአብሔር መደብ ነው፡፡

እኛ እግዚአብሔር መንፈስ እንደ ሆነና የሰው አካልን ተላብሶ ሰው ሆኖ እንደ መጣም እናውቃለን፡፡ ይህንንም ባደረገ ጊዜ የሰውን አካል ከመልበሱ በፊት ከነበረው ያነሰ እግዚአብሔር አልነበረም፡፡ እኛ ሰው ሲሞት አካላዊ ሰውነቱን ለቅቆ እንደሚሄድ ሆኖም አካላዊ ሰውነት ከነበረው ያነሰ ሰው እንዳልሆነም እናውቃለን፡፡ ሰውም እግዚአብሔርን በስሜት እውቀት ማወቅ እንደማይችልም ተረድተናል፡፡

እግዚአብሔር ለሰው የሚገለጠው በመንፈሱ ብቻ ነው፡፡ እግዚአብሔርንም የሚገናኘው የሰው መንፈስ ነው፡፡ እኛ መንፈሳዊ ነገሮች ልክ እንደ ቁሳዊ ነገሮች ሁሉ እውን እንደ ሆኑ እናውቃለን፡፡ እግዚአብሔር አካል እንዳለው ግለሰብ ያህል እውን ነው፡፡ በመንግስተ ሰማያት በአካል ያለው ኢየሱስ ከመንፈስ ቅዱስ ወይም ከአብ የበለጠ እውን አይደለም፡፡

በአንደኛ ጴጥሮስ 3፥4 ላይ የእኛ መንፈስ "ስውር የልብ ሰው" ተብሎ ተጠርቷል፡፡ በሮሜ 7፥22 ላይ ደግሞ "የውስጥ ሰውነት" ተብሎ ተጠርቷል፡፡ ይህ "የውስጥ ሰውነት"ና "የተሰወረ የልብ ሰው" እግዚአብሔር ስለ ሰው መንፈስ ያለውን ትርጉም ይሰጡናል፡፡ እውነተኛው ሰው መንፈስ ነው፡፡ እርሱም ነፍስና ሰውነት ወይም አካል አለው፡፡

ነፍስ የእውቀቱን ዓለም፤ ሰውነት ቁሳዊውን አካላዊ ዓለም፤ መንፈስ ደግሞ መንፈሳዊውን ዓለም ይገናኛሉ፡፡ "ለፍጥረታዊ ሰው የእግዚአብሔር መንፈስ ነገር ሞኝነት ነውና አይቀበለውም በመንፈስም የሚመረመር ስለ ሆነ ሊያውቀው አይችልም፡፡" አንደኛ ቆሮንቶስ 2፥12፡፡ ይህ እንዴት እንደ ሆነ ይገልጻል፡፡ የአንደኛ ቆሮንቶስ ሁለት ምእራፎች በስሜት እውቀትና በመንፈሳዊ እውቀት ወይም በስሜቶችና በመንፈስ መካከል ያነጻጽራል፡፡

ከመገለጥ እውቀት ውጪ ያለው ማንኛውም እውቀት ሁሉ ወደ ሰው የመጡት በአምስቱ ሕዋሳቱ በአእምሮው በኩል ነው፡፡ እነርሱ በቁሳዊ ነገሮችና በስሜት እውቀት መካከል ያሉ የመገናኛ መንገዶች ናቸው፡፡ አእምሮ ነገሮችን በአምስቱ ሕዋሳቶቹ አማካኝነት ካላገኘ በስተቀር አንዳችም ሊቀበል አይችልም፡፡ እነኚህ አምስቱ ሕዋሳቶች ቢደመሰሱ ሰው እውቀትን ሊቀበል የሚችልበት መንገድ አይኖረውም፡፡ እራሱንና ቁሳዊውን ዓለም እንኳ ለይቶ ማወቅ አይችልም፡፡

ሁለተኛ ቆሮንቶስ 4፥16 "ስለዚህም አንታክትም ነገር ግን የውጭው ሰውነታችን ቢጠፋ እንኳ የውስጡ ሰውነታችን ዕለት ዕለት ይታደሳል፡፡" ይላል፡፡ ኤፌሶን 3፥16 "በመንፈሱ በውስጥ ሰውነታችሁ በኃይል እንድትጠነክሩ ክርስቶስ በልባችሁ በእምነት እንዲኖር እንደ ክብሩ ባለጠግነት መጠን ይስጣችሁ፡፡" ይላል፡፡

ሰው ዳግም ሲወለድ ለዚህ ለውስጠኛው ሰው ለመንፈሱ የዘላለምን ሕይወት ይካፈላል። መንፈስ ቅዱስ ወደ ሰውነቱ ሲመጣ የመጣው በመንፈሱ ውስጥ ለመኖር ነው። መንፈስ ቅዱስ በቀጥታ አእምሮአችንን አይገናኝም ነገር ግን የእውቀት ሂደታችንን መድረስና መለወጥ ከሚችለው መንፈሳችን ጋር የግድ መገናኘት ይኖርበታል። መንፈሳችንም ድምፅ አለው እርሱንም ጎሊና ቀልብ ወይም መሪ ብለን እንጠራዋለን። (እኔ "ቀልብ" የሚለውን ቃል አልወድደውም ነገር ግን በስፋት በጥቅም ላይ የዋለ ነው።)

እኛ ሁላችን የውስጥ ድምጻችንን ተከትለን ብንሄድ ኖሮ ገንዘብ የከሰርንባቸውን አንዳንድ ኢንቨስትመንቶችን በፍጹም እንደማናደርግ የተወሰኑ ሰዎችንም ለባልንጀራነት በፍጹም አንደ ማንመርጥ ከአንዳንዶችም ጋር አብረን ለመሥራት እንደማንነሳ እናውቃለን። ያ የውስጥ ድምፅ ለአእምሮአችን መመሪያን ሊሰጠው ይሻል። እኛም መንፈሳችንን ማዳመጥ ብንማር ኖሮ ብዙ ስህተቶችን በጭራሽ ባልፈጸምን ነበር።

በእውቀት ባህላችን ውስጥ የተፈተመ አንዱና ዋነኛ ትልቅ ስህተት ቢኖር መንፈስን ችላ ማለት ነው። የአእምሮ እውቀታችን ዙፋኑን ያዘና መንፈሳችን እስር ቤት ውስጥ ተቆለፈበት። ስለዚህ ሊመራን የተገባው መንፈሳችን እንዲሠራ አልተፈቀደለትምና እኛ በተከታታይ ስህተት መስራታችንን ቀጠልንበት።

እውቀት በማንበብ በመጻዝና በመስማት በስሜት ሕዋሳችን አማካይነት የምናገኘው ነው። ጥበብ ደግሞ እውቀትን በመጠቀም ለጥቅም የማዋል ችሎታ ነው። ጥበብም በስሜት ሕዋሶቻችን በኩል አይመጣም። ጥበብ ከመንፈሳችን የሚመጣ ነው። ያዕቆብ ከላይ ይመጣል ይላል። የእግዚአብሔርን ጥበብ ተካፍለናል እርሱም መለኮታዊ ጥበብ ነው።

መንፈሱን የሚዘጋና እስረኛ የሚያደርግ እርሱንም የማይሰማ የማይታዘዝ ሰው ስንኩል ይሆንና ለራስ ወዳድ ስግብግቦችና ለዚህ ዓለም ሸፍጠኞች ወጥመድ አልፎ ይሰጣል። መንፈስ እንዲነሳሳና የበላይነቱን እንዲቀዳጅ በማንኛውም ቀወስ ጊዜ እንዲረዳው የሚፈቅድ ሰው ግን ወጥቶ በላይኛው ስፍራ ይቀመጣል።

"በልብ ማመን ማለት" ምን ማለት ነው? በመንፈስ ማመን ማለት ነው። በአእምሮአችን ልናምን አንችልም ይህ ምንም ዓይነት ሙግት አያስፈልገውም። እምነት የመንፈስ ውጤት ነው። ማረጋገጫ ተብሎ የተጠራው የውስጥ ምስክርነት የመንፈስ ልጅ ነው። ለምን እንዳወቅን አናውቅም ወይም ልንገልጸውም አንችልም ሆኖም ግን እናውቃለን።

አንድ ቀን በጣም የሚያሰቃይ ሕመም ለነበረባት ሴት ቃሉን እየገለጥኩላት ነበር። ቃሉን ደረጃ በደረጃ ሳስረዳት ሴቲቱም "አየሁት በመገረፉ ቁስል ተፈውሻለሁ" አለች። እኔም "መፈወስሽን እንዴት አወቅሽ" አልኳት እርሷም "ምክንያቱ ቃሉ የእኔን መፈወስ ስላወጀ ነው።" አለች። የስሜት እውቀት "ቁስሉ በሰውነትህ ላይ አለ አሁንም ሕመሙ ይሰማሃል።" ይላል። እርሷ ግን ከስሜት እውቀት ከስሜታዊ መረጃ በላይ አልፋ መፈወሷን አወጀች። ለእርሷ እየጸለይኩላት ሳለ እምነቷ ደዌውን ጨርሶ አስወገደው።

ለእርሷ ሞት የነበረው ደዌ ለቅቆ ሄደ። ለምን? ቢባል ምክንያቱ የእግዚአብሔርን ቃል በልቡዋ ስላመነች ወይም በመንፈሷ ስላመነችው ነው።

አእምሮአችን ሊይዘው ያልቻለውን እምነት መንፈሳችን እንዴት አገኘ ለሚለው ጥያቄ መልሱ ከቃሉ የሚል ይሆናል። ኢየሱስ "ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም።" አለ። ማቴ 4፥4። እዚህ ላይ ኢየሱስ ስለ መንፈሳዊ ምግብ እየተናገረ ስሜታዊ እውቀትን በመጠቀም መንፈሳዊ እውነትን እያስተላለፈ ነው። ቃሉን ስናሰላስል መንፈሳችን በመታመን ይሞላል።

ለዓመታት ስለ ፋይናንስ ነክ ጉዳይ ሆነ አካላዊ ፍላጎቴ በእምነት ተጉዣለሁ። አሁን ደግሞ ቃሉ መንፈስን የሚያንጽና ጠንካራ የሚያደርግ ፍጹም መተማመንን የሚሰጥ መሆኑን ወደ ማየት አድጌአለሁ። ስሜቶቻችን የሚሰሙትን፤ የሚያዩትንና የሚሰማቸውን በመደገፍ ያምናሉ። መንፈስ ደግሞ ማየትን መስማትን ወይም ስሜትን ከቁጥር ሳያስገባ ያምናል።

አብዛኛውን ጊዜ በተደጋጋሚ እየተጸለየላቸው ፈውሳቸውን ያልተቀበሉ ሰዎች የስሜት እውቀት ያላቸው ናቸው። እነርሱ የመገለጥ እምነት የላቸውም። የእነርሱ እምነት መሰረት የተንጠለጠለው በሚቀባው ዘይት ላይ ወይም በሌላ ሰው እምነት ማለትም በግለሰብ እምነት ወይም ድርጅት ላይ ነው እንጂ በቃሉ ላይ የተተገነ እምነት አይደለም።

ያዕቆብ 5፥14 "ከእናንተ የታመመ ማንም ቢኖር የቤተ ክርስቲያንን ሽማግሌዎች ወደ እርሱ ይጥራ በጌታም ስም ዘይት ቀብተው ይጸልዩለት የእምነትም ጸሎት ድውዩን ያድናል ጌታም ያስነሳዋል።" ይላል። ይህ ሙሉ ስዕል የስሜት እውቀት እምነት ስዕል ነው። የታመመ አንድ ሰው "በመገረፉ ቁስል" መፈወሱን ካወቀና ከገባው ሽማግሌዎችን መጥራት አያስፈልገውም። ነገር ግን ባለማወቁ ምክንያት ተስፋ ቆርጦ ወደ ጌታና ወደ ሽማግሌዎች ተመልሷል።

ኢየሱስ ሥጋ ለብሶ በአካል በመገለጥ ሰውን በሰው ደረጃ ወርዶ እንደተገናኘው የእግዚአብሔርም ጸጋ በተመሳሳይ መልኩ እንደዚሁ ተገልጧል። ይኸውም ቃል ሥጋ ለብሶ በሰዎች መካከል ባደረ ጊዜ ሰው ሊያየው ሊሰማው ሊዳስሰው እንዲችለው ሆኖ ወደ ሰው የስሜት የእውቀት ዓለም መጣ። ኢየሱስ በአካል በምድር በተመላለሰበት ጊዜ ሰው ማየት መስማት ወዘተ እስከቻለ ድረስ ማንኛውም ነገር የተያያዘው ከስሜት ዓለም ጋር ነበር። ከመንፈሳዊው ዓለም አንጻር ደግሞ በኢየሱስ አላመኑም ነበር። ያመኑት እንጂራን ስለ በሉና ተአምራት ስላዩ ብቻ ነበር።

እርሱ በመስቀል ላይ በሞተ ጊዜ ስለ ምን እንደ ሞተ ምንም ዓይነት መንፈሳዊ መረዳት አልነበራቸውም። እነርሱ ስለ ኃጢአታቸው እንደ ሞተ አላወቁም። ለዓላማው እንደ ሞተ ሰማዕት አድርገው ነው ያሰቡት። ዛሬም የስሜት እውቀት ያለው አስተሳሰብ ይህ ነው። የምሁራኑም ዓለም የሚያምነው ኢየሱስ ላመነው ዓላማ ሰማዕት ሆኖ መሞቱን ነው። ይሁን እንጂ በክርስቶስ ስቅለት የስሜት እውቀት እምነት ተዋረደ።

በሙሉ ልባችን ማመን ማለት ከስሜት እውቀት ባሻገር ማመን ነው። መንፈሳችን ለኢየሱስ ጌትነት ለመረታታችን ምላሽ ይሰጣል። ለመጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት ዋናው ቁልፍ የኢየሱስን ጌትነት በልብ መቀበል ነው። አንደኛ ጴጥሮስ 3፥15 "ዳሩ ግን ጌታን እርሱም ክርስቶስ በልባችሁ ቀድሱት።" ይላል። "ቀድሱት" ማለት "ለዩት" "ነጥሉት" ማለት ነው። እኛ ክርስቶስን የምንቀድሰው የምንለየው የምንነጥለው በልባችን ወይም በመንፈሳችን ነው።

እኛ ኢየሱስን የሕይወታችን ጌታ አድርገን ስንቀበለው ቃሉን በሕይወታችን ጌታ አድርገን አነገስነው ማለት ነው። ይህም ለቃሉ ተገቢውን ስፍራ ይሰጠዋል። ኢየሱስ በሰማያት በአብ በግርማው ቀኝ ተቀምጧል። ቃሉ ደግሞ በእኛ ውስጥ ነው። እኛም ለዚያ ቃል ተገቢውን ስፍራ ስንሰጠው እምነት ፍጹም ባሕርያችን ይሆናል።

ምሳሌ 3፥5-7 "በፍጹም ልብህ በእግዚአብሔር ታመን በራስህም ማስተዋል አትደገፍ (በስሜት እውቀት) በመንገድህ ሁሉ እርሱን እወቅ እርሱም ጎዳናህን ያቀናልሃል። በራስህ አስተያየት ጠቢብ አትሁን እግዚአብሔርን ፍራ ከክፉትም ራቅ።" ይላል። ከቃሉ ከሚያለያይና ከእርሱ ውጪ እንድትቆሙ በሚያደርግ የስሜት እውቀት አትጠበቡ።

ሁለተኛ ቆሮንቶስ 10፥3 "በሰው ልማድ ምንም እንኳ የምንመላለስ ብንሆን እንደ ሰው ልማድ አንዋጋም የጦር ዕቃችን ሥጋዊ አይደለምና ምሽግን ለመስበር ግን በእግዚአብሔር ፊት ብርቱ ነው የሰውንም አሳብ በእግዚአብሔርም አውቀት ላይ የሚነሣውን ከፍ ያለውን ነገር ሁሉ እናፈርሳለን ለክርስቶስም ለመታዘዝ አእምሮን ሁሉ እንማርካለን።" ይላል።

በእምነት መመላለስ ከፈለግን ይህ እጅግ አስፈላጊ ጉዳይ ነው። የያዝነው የስሜት እውቀት የእኛ ይሁን የሌላ ሰው ከቁጥር ሳይገባ የእግዚአብሔር ቃል ከስሜት እውቀታችን በላይ መሆን አለበት። ምንጊዜም የስሜት እውቀት ውሱን መሆኑን ማስታወስ አለብን። አንድም ሰው ፍጹም የሆነ የስሜት እውቀት የለውም።

የእግዚአብሔር ቃል ፍጹም ነው። ይህ መገለጥ የእርሱ ፍጹም መገለጥ ነውና በየትኛውም ቀውስና ችግር ውስጥ እያንዳንዱን ፍላጎታችንን ያሟላልናል። ይህንን ቃል ከልባችን ከታመንነው እርሱን ተከትሎ ጸጥታና እረፍት ለመንፈሳችን ይመጣል። ማመን ማወቅ ነው። እኛ የእግዚአብሔር ቃል እውነት እንደ ሆነ አውቀናል።

እርሱ "እግዚአብሔር የሚያስፈልጋችሁን ይሞላባችኋል" ካለ ማንኛውም የሚያስፈልገን ነገር እንደ ተሟላ በመንፈሳችን እንዲያው እናውቃለን ስለሆነም አንሰጋም ጭንቀትም አይኖርብንም። ቃሉን ባነበብን መጠን ልባችን ይደፋፈራል። መታመናችንም ጥልቅ እየሆነ ይሄዳል። ይህ መታመን ከስሜት መረጃና ማረጋገጫ ባሻገር የሆነ ነው። እንደ ተለመደው የስሜት መረጃን ይቃረን ይሆናል ነገር ግን እኛ መንፈሳዊ ነገሮች ልክ እንደ ቁሳዊ ነገሮች እውን መሆናቸውን ተገንዝበናል። መንፈስ የሆነው እግዚአብሔር አካላዊ

ነገሮችን ሁሉ ፈጥሯልና መንፈሳዊ ነገሮች ከአካላዊ ነገሮች በላይ የላቁ መሆናቸውንም አውቀናል።

እኛ መንፈሳዊ ኃይላት ከምድራዊ ኃይላት ይልቅ ብርቱ መሆናቸውን አውቀናል። እኛ "በዓለም ካለው ይልቅ በእኛ ውስጥ ያለው እንደሚበልጥ" አውቀናል። እኛ የሚበልጠው እርሱ የደቄና የድካም ሁሉ ጌታ እንደ ሆነ አወቀናል። እኛ በሙሉ ልባችን ታምነነዋልና እርሱ ተነስቶ ከየትኛውም ምንጭ የማናገኘውን ብርሃን ለአእምሮአችን ይሰጠዋል። እኛ እንደማንሸነፍ አውቀናል። ይህንንም ያወቅነው ሰላመንን ብቻ ነው።

ምእራፍ አስር

ቃሉን መተግበር

ኢየሱስ በዮሐንስ 6፥47 ላይ "በእኔ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው።" አለ። "ማመን" "ባለቤት" መሆን ማለት ነው።

አእምሮአዊ ስምምነት ቃሉን ያደንቃል ቃሉ እውነትና ተፈላጊ መሆኑን ያውጃል ነገር ግን አልያዘውም ስለዚህ ምንም የለውም።

ማመን "የእኔ ነው አሁን አለኝ።" በሚል የሚያስደስት እውነተኛ አዋጅ ይደመድማል።

ዛሬ ዛሬ በቃሉ ላይ እውነተኛ የሆነ ተግባራዊነት ምን ያህል ጥቂት እንደ ሆነ እናያለን።

(ማርቆስ 2፥1-2) ላይ በአራት ጓደኞቹ ተይዞ ወደ ኢየሱስ ፊት የመጣውን ሰው ታስታውሳላችሁ። ኢየሱስ "ተነሣ አልጋህን ተሸክምና ወደ ቤትህ ሂድ።" አለው። ጌታ የተናገረውን ቃል ተግባራዊ ባያደርግ ኖሮ አይፈወስም ነበር ነገር ግን ተግባራዊ በማድረጉ ተፈወሰ። ሉቃስ 5፥5 ላይ ጴጥሮስ "በቃልህ መረቦቹን እጥላለሁ" አለው። እኛም ደግሞ "በቃልህ አደርጋለሁ" ብንል በአንዳንዶቻችን ሕይወት ምን ዓይነት ለውጥ በመጣ ነበር። እኛ ግን የሰዎችን ንድፈ አሳብ ሙጥኝ ብለን ሕያው ቃሉን ችላ አልነው።

ፈውስና ድል የአናንተ ነው። ኢየሱስ ጴጥሮስን "ና ከእኔ ጋር በማእበሉ ላይ ሂድ" ባለው ጊዜ ጴጥሮስ ቃሉን ተግብሯል፡ አገልጋዮቹ ጋኖቹን ውኃ በሞሉአቸው ጊዜ ኢየሱስ ያለውን ታዘዋልና ውኃው ወደ ወይን ጠጅ ተለወጠ። ዮሐንስ 2፥1-12። አንዳንዶቻችን የቃሉ እውነተኝነትና ሐቀኝነት ላይ በአእምሮአችን እንስማማለን ነገር ግን ተግባራዊ አናደርገውም። ተግባራዊ እስካላደረግነው ድረስ ወደ መገለጥ አይመጣም።

የትንሳኤውን እውነት እንደ አንድ አስተምህሮ ወይም እንደ አንድ ቀኖና ልትይዙ ትችላላችሁ ነገር ግን "እርሱ ስለ እኔ ሞቷል። ሞትና ሲዖልን ስለ እኔ አሸንፏል። ስለ እኔም ከሞት ተነስቷል። ስለ እኔ ስለ ተነሳም እኔ ባለ ድል ነኝ። እኔ ዛሬ ሰይጣንን ድል ያደረግሁ ነኝ። ሰይጣን በእኔ ላይ የበላይነት የለውም። እኔ ነጻ ወጥቼአለሁ።"

እስካላላችሁ ድረስ ለእናንተ ምንም ነገር አይከናወንም። ከላይ የተገለጸውን ካወጃችሁ ግን ቃሉ ከአስተምሕሮነት ወይም ንድፈ አሳብነት በላይ እውን ይሆናል።

ቃሉን ተግባራዊ የሚያደርጉ ሰዎች የሚሹትን ይቀበላሉ። ዛሬም እንዲሁ ነው። እምነትን ተግባራዊ ታደርጋላችሁ፤ እምነትን ትናገራላችሁ፤ ተግባራችሁና ቃሎቻችሁም ይስማማሉ። ስለሆነም እናንተ አማኞች ናችሁ። ወደ ቤተሰብነት ለመቀላቀል እምነት አስፈልጓችኋል ነገር ግን ወደ ቤተሰብነት ከገባችሁ በኋላ ሁሉ ነገር የእናንተ ሆኗል። (አንደኛ ቆሮንቶስ 3፥21)።

የእግዚአብሔር ልጅ ለመሆን እምነት አስፈልጓል ነገር ግን ልጆቹ ክርስቶስ ያመጣው ነገር ሁሉ ባለቤት ናቸው። እግዚአብሔር "እፈጽመው ዘንድ በቃሌ እተጋለሁ" ሲል እናንተ አሳይያስ 53፥3-6ን ከተቀበላችሁ እግዚአብሔር በዙፋኑ ላይ እስካለ ድረስ ፈውስ ለእናንተ እንዲሆን የተወሰነ መሆኑን እርግጠኛ ናችሁ። እናንተ ማድረግ ያለባችሁ ነገር ቢኖር ቃሉን ተግባራዊ ማድረግ ነው። ይህንን ጥቂትና ቀላል ትምሕርት መማር እጅግ አስፈላጊያችሁ ነው። ውጤትን የሚያመጣው እግዚአብሔር የተናገረውን ተግባራዊ ማድረግ እንጂ መታገል ወይም መጸለይ ወይም ማልቀስ አይደለም።

## እምነትና ማመን

"እምነት" የሚለው ቃል ስም ነው። "ማመን" የሚለው ቃል ደግሞ ግስ ነው። "ማመን" ማለት በትክክል ቃሉን "መተግበር" ወይም “ተግባራዊ” ማድረግ ነው። በቀላል አነጋገር የሐኪማችሁን ቃል የጠበቃችሁን ቃል የወዳጃችሁን ቃል እንደምትፈጽሙ ሁሉ የእግዚአብሔርንም ቃል ልክ እንደዚያው ተግባራዊ ማድረግ ማለት ነው።

"አምናለሁን?" ወይም "እምነት አለኝን?" ብላችሁ አትጠይቁም። እንዲያው ዝም ብላችሁ "እግዚአብሔር ያለው እንዲህ ነው" ትሉና እንደተባለው ተግባራዊ ታደርጋላችሁ ወይም "እግዚአብሔር ‘በመገረፉ ቁስል’ ተፈውሰሃል ብሏልን? ብላችሁ ትጠይቁና እግዚአብሔር ካለ ተፈውሻለሁ ማለት ነውና እግዚአብሔር በተናገረው ላይ እቆማለሁ።" ትላላችሁ።

እምነት የተግባር ውጤት ነው። ማመን ደግሞ የምትፈልጉትን ነገር ለመጨበጥ ወደ ፊት መራመድ ማለት ነው። "ማመን" የሚለውን ቃል ከመጠቀም ይልቅ "ቃሉን ተግብሩ ወይም ቃሉን አድርጉ" የሚለውን ቃል እጠቀማለሁ። ቀለል ያለ ነው። ፍጹም የሆነ እግዚአብሔራዊ ቃልና ኢየሱስ ማለት የፈለገውም ይህንኑ ነው። ጳውሎስ በየትኛውም መልእክቱ ላይ አማኞች እንዲያምኑ ወይም እምነት አንዲኖራቸው የጎተጎተበት ስፍራ አለመኖሩ ግልጽ ነው። የእኛ ሰዎችን እንዲያምኑ መጎትጎት በሰዎች ዘንድ የቃሉ እውነታ መጥፋት ውጤት ነው።

ጳውሎስ "በክርስቶስ በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ የባረከን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ።" ኤፌ ፡3 በማለት ጽፎልናል። እርሱ በመንፈሳዊ

በረከት ሁሉ ከባረካችሁ ተባርካችኋል ማለት ነው፡፡ እናንተ መንፈሳዊ በረከትን መጠየቅ አያስፈልጋችሁም፡፡ እናንተ የሚያስፈልጋችሁ በረከቱ ስላላችሁ እርሱን ማመስገን ነው፡፡ ያለባችሁም "አባቴ ሆይ ስለ ፈውሴ አመሰግንሃለሁ፡፡ ስለ አርነቴ አመሰግንሃለሁ፡፡" ማለት ብቻ ነው፡፡ ኢየሱስ ያደረገው ነገር ቢኖር የአባቱን ቃል ተግባራዊ ማድረግ ብቻ ነው፡፡ ጴጥሮስም ያደረገው ነገር ቢኖር ክርስቶስ የሰጠውን ቃል ተግባራዊ ማድረግ ብቻ ነበር፡፡ ለሰዎችም ድነት ፈውስና አርነት ያመጣው ጴጥሮስ ተግባራዊ ያደረገው በአንደበቱ የነበረው የክርስቶስ ቃል ነው፡፡

እኛ ቃሉን ልንሰብክ እንችላለን ነገር ግን ተግበራዊ በማድረግ ካልተለማመድነው ውጤትን አያፈራም፡፡ ፈውስን ልንሰብክና በፈውስ ላይ ያለንን እምነት ልናውጅ እንችላለን በተግባር እስካልተለማመድነው ድረስ ግን ዋጋ የለውም፡፡ ያዕቆብ "እምነት አብሮ ከሚሄድ ተግባር ውጪ ሙት ነው፡፡" ብሎናል፡፡ ቃሉን ተግባራዊ ስንደርግ እምነታችንን እናሳያለን፡፡ እኛ በእግዚአብሔር ዘንድ ኃይል አልባ የእግዚአብሔር ቃል እንደሌለ ወይም ለእግዚአብሔር የሚሣነው እንደሌለ አውቀናል፡፡ (ሉቃስ 1፥37)፡፡

እርሱ "እፈጽመው ዘንድ በቃሌ እተጋለሁ" ብሎናልና ያለምንም ፍርሃት እጆቻችንን በድውያን ላይ እንጭናለን፡፡ በኢየሱስ ስምም ደዌው ለቅቆ እንዲሄድ እናዝዛለን እርሱም ይታዘዛል፡፡ በሽተኛውም ይፈወሳል፡፡ እርሱ ባይነግረን ኖሮ አጆቻችንን በድውያን ላይ ጭነን ፈውስን አናውጅም ነበር፡፡ እርሱ "ያመኑትም እጆቻቸውን በድውያን ላይ ይጭናሉ፡፡" አለ፡፡ (ማርቆስ 16፥16-18)፡፡ እንዲህ ሲባል ኢየሱስን የግል አዳኛችን አድርገን በተቀበልን ጌታችን አድርገን ባወጅንና የዘላለም ሕይወትን በተቀበልን ጊዜ በቤተሰቡ ውስጥ መሥራት መጀመር እንችላለን፡፡ እጅ መጫንን መተግበር እንችላለን ማለት ነው፡፡

"ያመነ የተጠመቀም ይድናል" (ማርቆስ 16፥16)፡፡ "ድነት" የሚለው ቃል በግሪክ "ሶዞ" ሲሆን "ፈውስ" ማለት ነው፡፡ ፈውስ የሚለው ቃል የመጨረሻ ትንታኔ መንፈሳዊም አካላዊም ነው፡፡ ደዌ ራሱ በአካል ይገለጥ እንጂ ሥሩ ወይም የጭብጡ እውነታ ግን መንፈስ ነው፡፡ "ማመን"ን የተመለከተ ቃል በዮሐንስ ወንጌል ላይ መቶ ጊዜ ተጠቅሷል፡፡ "እምነት" የሚለው ቃል ደግሞ ሁለት ወይም ሦስት ጊዜ ብቻ ተጠቅሷል፡፡ ለዚህም ምክንያቱ እርሱ እያናገረ የነበረው ከክርስቶስ አካል ውጪ ያሉትን በሕግ ስር የነበሩትን አይሁዶችን በመሆኑ ነበር፡፡ እነርሱ የእምነት ሰዎች አልነበሩም፡፡ እነርሱ እምነት አልነበራቸውም፡፡ ስለዚህ እነርሱን እንዲያምኑ ያነሣሣቸው ነበር፡፡

## ስለማመን ጥቂት መረጃዎች

ጥቂት ሰዎች ማመን አይችሉም ምክንያቱም የክርስቶስን ጌትነት በፍጹም አላወጁምና፡፡ሰውን መፍራት ወጥመድ ሆኖ ይዟቸዋል፡፡ ይህ ሰይጣን በሰው ላይ ያለው ዋና ብርቱ ምሽግ ነው፡፡ ብዙ ጊዜ ሙት የሆነ ሐይማኖታዊ እምነት ሰውን ያስራል፡፡ በአንድ መንገድ ወይም በሌላ እናንተ ይህንን እና ያንን እንዳታምኑ ተምራችኋል፡፡

የእናንተ ክርስቶስ በድንግርግርና ውስብስብ መንገድ ስነ መለኮታዊ ንድፈ አሳቦች ጠፍቷል፡፡ ራሳችሁን ለቃሉ ጌትነት አስገዙ ተግባራዊ አድርጉት እግዚአብሔርም ለእናንተ እውን ይሆናል፡፡

ምእራፍ አስራ አንድ

የእኛ የሆኑ ነገሮች

አብ ከታላቅ ጸጋው ቤተ ክርስቲያን ሃብታምና ጠንካራ እንድትሆን በቂ ስጦታ ሰጥቷታል፡፡ "በክርስቶስ በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ የባረከን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ፡፡" ኤፌሶን 1፥3፡፡ ይህን ሲል ምን ማለቱ ነው? እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ ያደረገው የመዋጀት ሥራ እርሱ ኃጢአት ከሆነበት ጊዜ አንስቶ በላይ በሰማያት በግርማው ቀኝ እስከ ተቀመጠበት ያለው ሁሉ የክርስቶስ አካል የሆነችው የቤተ ክርስቲያን ነው ማለቱ ነው፡፡ እኛ ተባርከናል፡፡ ኢየሱስ ለራሱ አንዳች አላደረገም አብም ምንም አያስፈልገውም፡፡

"በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና፡፡" ዮሐንስ 3፥16፡፡ ኢየሱስ ለጠፋው ዓለም የአብ ስጦታ ነበር፡፡ አሁንም አብ ስጦታውን መልሶ አልወሰደም፡፡ በዓለም ያለ የሰው ዘር ሁሉ የዚህ ስጦታ ባለመብት መሆኑን እውቅና ቢሰጠውም ባይሰጠውም ኢየሱስ አለው፡፡

ኢየሱስ በምትክነት መስዋእትነቱ በመለኮታዊ ልውውጡ የሠራው ሁሉ ኢየሱስ መስዋእትነቱን የከፈለለት ሰው የግል ንብረት ነው፡፡ ሥራው ተሠርቶ ተጠናቅቋልና ኃጢአተኛ እግዚአብሔር እንዲያድነው መማጸን አያስፈልገውም፡፡ ማድረግ ያለበት ነገር ቢኖር ስጦታውን መቀበልና እግዚአብሔርን ማመስገን ነው፡፡ ያን ጊዜ ሁሉ የእርሱ ይሆናል፡፡

"ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም፡፡" ኤፌሶን 2፥8-9፡፡ ድነት ስጦታ ነው፡፡ እምነት ቃሉን ተግባራዊ በማድረግ ይመጣል፡፡ እኛ ቃሉን ተግባራዊ እናደርጋለን፡፡ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኛችን አድርገን እንቀበላለን ጌታችን መሆኑንም እናውጃለን በዚያች ቅጽበትም ዘላለማዊ ሕይወትን እንቀበላለን፡፡

"በክርስቶስ ኢየሱስ የተፈጠርን የእጆቹ ሥራዎች ነን፡፡" ሥራው ኢየሱስ ከሙታን ከመነሳቱ በፊት ተጠናቅቋልና ሥራው ያመጣው ውጤት ለእኛ ተገብቶናል፡፡ ስለዚህ እኛ የሚያስፈልገን እሺ ብሎ መቀበል ብቻ ነው፡፡ አማኝ በታመመ ጊዜ አብ እንዲፈውሰው መጠየቅ አያስፈልገውም ምክንያቱም "በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ ሕመማችንንም

ተሸክሞአል እኛ ግን እንደ ተመታ በእግዚአብሔርም እንደ ተቀሰፈ እንደ ተቸገረም ቆጠርነው፡፡" እግዚአብሔር ደዌያችንን ኢየሱስን አሸክሞታል፡፡

ኢሳይያስ 53፥10 እግዚአብሔር ኢየሱስን በደዌ ያደቅቀው ዘንድ እንደ ወደደ ስለዚህም እኛ በእርሱ ቁስል እንደ ተፈወስን ይገልጻል፡፡ እንግዲያስ ከተፈወስን ስለ ፈውሳችን መጸለይ አያስፈልገንም፡፡ ማድረግ የሚያስፈልገን ነገር ቢኖር ጠላትን በኢየሱስ ስም መገሰጽና ሰውነታችንን ለቅቆ እንዲሄድ ማዘዝ ከዚያም አብን ስለ ፍጹም ፈውሱ ማመስገን ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ የጉዳዩ መፍትሔ ይህን ያህል ቀላል ነው፡፡

ጌታ ኃይል እንዲሰጠን መጸለይ አያሻንም ምክንያቱም እርሱ የሕይወታችን ኃይል ነውና፡፡ "እግዚአብሔር ብርሃኔና መድኃኒቴ ነው የሚያስፈራኝ ማነው? እግዚአብሔር የሕይወቴ መታመኛዋ (ኃይሏ) ነው የሚያስደነግጠኝ ማን ነው?" መዝ (27)፥1፡፡ ይህ አሁን የእኛ መብት ነው፡፡ እርሱ የእኛ መብራትና ድነት ሆኗል፡፡ ይኸውም የእኛ እውቀትና ቤዛችን ሆኗል ማለት ነው፡፡ ደግሞም የእኛ አርነት ወይም ነጻነት ሆኗል፡፡

"ከእግዚአብሔር ዘንድ ጥበብና ጽድቅ ቅድስናም ቤዛነትም በተደረገልን በክርስቶስ ኢየሱስ የሆናችሁ በእርሱ ነው፡፡" አንደኛ ቆሮንቶስ 1፥30፡፡ እግዚአብሔር ኢየሱስን ለእኛ ምን ምን እንዲሆን እንዳደረገልን እስቲ እንመልከት፡፡ እኛ እንድንቀደስ አንጠይቅም ምክንያቱም እርሱ የእኛ ቅድስና ነውና እኛ ቅዱስ ነን፡፡ እኛ ጻድቅ ለመሆን አንጠይቅም ምክንያቱም እርሱ የእኛ ጽድቅ ነውና እኛም በክርስቶስ የእርሱ ጽድቅ ሆነናልና፡፡

አማኝ ባለቤት ነው፡፡ "በእኔ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፡፡" ተብሏልና፡፡ እኛ ከዘላለም ሕይወት ባለቤትነት ውጪ ልናምን አንችልም፡፡ እኛ ከሚያስፈልጉን ነገሮች ባለቤትነት ውጪ "አምላኬም እንደ ባለ ጠግነቱ መጠን በክብር በክርስቶስ ኢየሱስ የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ ይሞላባችኋል፡፡" የሚለውን ፊሊጵስዩስ 4፥19ን ልናምን አንችልም፡፡

ጳውሎስ አማኞች ባለቤት መሆናቸውን ተገንዝቦ ነበር፡፡ እኛ መዋጀታችንን ለማመን መሞከር የለብንም ምክንያቱም ተዋጅተናል፡፡ (ኤፌሶን 1፥7)፡፡ እኛ በክርስቶስ ውስጥ ለመሆናችን ለማመን መሞከር የለብንም ምክንያቱም በእርሱ ውስጥ ነንና፡፡ (አንደኛ ቆሮንቶስ 5፥21)፡፡ እኛ የእግዚአብሔር ልጆች ለመሆናችን ለማመን መሞከር የለብንም ምክንያቱም አንደገና ተፈጥረናልና በእርሱ ቤተሰብ ውስጥ ነን፡፡ (አንደኛ ዮሐንስ 3፥2)፡፡

እኛ ከኃጢአታችን እንዲፈታን ይህን አስመልክቶ ልንጸልይ አያስፈልገንም ምክንያቱም ኃጢአታችን ተወግዶ በነጻ ተለቅቀን በሕልውናው ፊት ጸድቀናል፡፡ የቀድሞው ኃጢአተኛ ባሕሪያችን ተገፍፎ የእግዚአብሔር ባሕርይ ተካፋይ ሆነናል፡፡ (ቆላስያስ 1፥13-14)፡፡ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን አንደሚሰጠን ለማመን መሞከር የለብንም ሰጥቶናልና፡፡ ማድረግ የሚያስፈልገን ነገር ቢኖር እንዲመጣ መጋበዝ ብቻ ነው፡፡ "በሰማይ ያለው አባት ለሚጠይቁት እንዴት አብልጦ መንፈስ ቅዱስን ይሰጣቸው?" (ሉቃስ 11፥13)፡፡

እዚህጋ ኢየሱስ የዘላለም ሕይወትን ለተቀበለ አንድ ሰው እየተናገረ ነው፡፡ ይህ ሰው በርግጥ አሁን ኢየሱስን ከሞት ያስነሳውን መንፈስ ወደ ሰውነቱ መጥቶ ማደሪያ እንዲያደርገው እየጠየቀ ነው፡፡ ስለዚህ እርሱ እያወራ ያለው በክርስቶስ ሆኖ በፍጹም መንፈሱን ለመቀበሉ ንቁ ላልሆነ አዲስ ሕጻን ነው፡፡

የኢየሱስ ስም የእኛ ነው፡፡ እግዚአብሔር የእኛ የእያንዳንዳችን የግል አባት ነው፡፡ ኢየሱስ የእኛ ጌታ ጠበቃና ጥበብ ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ የእኛ አስተማሪ ነው፡፡ ያለ አንዳች ጥርጥር ፈውስ የእኛ ነው፡፡ ኃይል የእኛ ነው፡፡ ብርሃንና ጥበብ የእኛ ነው፡፡ የዘላለም ሕይወት ባለቤት ነን፡፡ እርሱ የእኛ አቅርቦት ነው፡፡ እርሱ ብቃታችን ነው፡፡ እርሱ በእኛ ውስጥ ፍቅር ነው፡፡

ይህ ሁሉ በመጀመሪያ ያመንን ጊዜ የእኛ ሆኗል እንጂ አሁን እንደ አንድ አማኝ በግል እምነታችን ከመደገፋችን ጋር የተያያዘ አይደለም፡፡ እኛ ባለቤት ሆነናል፡፡ እኛ የራሳችን አድርገነዋል፡፡ ይህም የማንኛውም ልጅ መብት ነው፡፡ ይህም ሁሉ በመዋጀታችን የተገኘ መብት ነው፡፡ ስለዚህ አብን አመስግኑ አወድሱት የሚያስፈልጋችሁ ነገር ሲያጋጥማችሁ እርሱም በመዋጀት ውስጥ ተሸፍኗልና የእናንተ ነው፡፡

አንዳንዶች "ታዲያ ስለ ምን ልንጸልይ እንችላለን?" ሊሉ ይችላሉ፡፡ ትልቅ መሻት ላለው ዓለም ደግሞም ከተገባቸው ጥቅሞች በታች በጨለማ ስር ለሚኖሩ ክርስቲያኖች ነጻ ወጥተው ሳለ ነጻ መሆናቸውን ላላወቁ በእስር ላይ ላሉ ወንዶችና ሴቶች አርነት መጸለይ እንችላለን፡፡

## በክርሰቶስ ውስጥ ባለን መብቶች መደሰት

ቤዛነት በእግዚአብሔር የታቀደ ነበረ፡፡ ውጤቱ የእግዚአብሔርን ልብ አርክቷል የሰውንም ፍላጎት አሟልቷል፡፡ ክርስትና ከእግዚአብሔር ጋር ያገናኘናል፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ካለን ስኬታማ ነን፡፡ የዩኒቨርሱ እጅግ ጠንካራ ኃይላት ሁሉ በእኛ ስር ናቸውና፡፡

የእግዚአብሔር ችሎታ ኃይላችን ነው፡፡ "መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ" ሐዋርያት ሥራ ፩፥፰፡፡ የእግዚአብሔር ኃይል ለእኛ ሆኗል፡፡ ይህ እንዴት ያለ እጅግ የሚያስፈነጥዝ መረጃ ነው፡፡ "ልጆች ሆይ እናንተ ከእግዚአብሔር ናችሁ አሸንፋችኋቸውማል በዓለም ካለው ይልቅ በእናንተ ያለው ይበልጣል፡፡" አንደኛ ዮሐንስ ፬፥፬፡፡

እኛ ከእግዚአብሔር ነን፡፡ ሥራችን በእግዚአብሔር ውስጥ ሰጥሟል፡፡ የእግዚአብሔር ኃይል ውርሳችን ነው፡፡ የአትክልት ሥር ከአፈሩ ርጥበትን እንደሚስብ ሁሉ እግዚአብሔር ውስጥ ያለው የእኛም ሥር ከእግዚአብሔር ኃይልን ሕያውነትን ጥንካሬን ብቃትንና ችሎታን ይስባል፡፡ እርሱ ከእኛ ጋር ብቻ ሳይሆን የእኛ ማንነት ሆኗል፡፡ እርሱ በእኛ ውስጥ አለ፡፡ የእኛም ባሕርይ ሆኗል፡፡

"እግዚአብሔር በእኔ ውስጥ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ኃይል ብቃትና ችሎታ የእኔ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ጥንካሬ የእኔ ነው፡፡ እግዚአብሔር የእኔ ጤንንት ነው፡፡ እርሱ የእኔ ስኬት ነው፡፡ እኔ ባለ ድል ነኝ፡፡ እኔ አሸናፊ ነኝ፡፡ እኔ የተሳካልኝ ነኝ ምክንያቱም ታላቁ ከታላቅ ኃይሉ ብቃቱና ችሎታው ጋር በእኔ ውስጥ አለ፡፡" እያልን ይህን ሁልጊዜ እየደጋገምን በናውጅ በጣም ይረዳናል፡፡

ይህን በማለታችን መብታችንን መተዋችን አይደለም ይልቁንስ መብታችንን በርግጠኝነት አውቀት መውሰዳችን ነው እንጂ፡፡ እኛ ይህን አዲስ ሕይወት ከእርሱ ጋር መደሰታችን ነው፡፡ ከእርሱ ጋር የምንኖር ኅብረት የምናደርግ ከዘመኑ ሰው ጋርም አብረን የምንሠራ ነንና፡፡

እኛ ከስሞች ሁሉ በላይ የሆነውን አሸናፊ የሆነውን ስም የመጠቀም መብት አለን፡፡ የኢየሱስን ስም በንግድ ዓለምና በሳይንሳዊው ዓለም ጭምር መጠቀም ይቻላል፡፡ ሰብአዊ ፍጡር ከየትኛውም ጥረቱ ለማረፍ ይህን ስም መጠቀም ይቻላል፡፡ "በስሜ" ሲል ልክ ጌታ አሁን በአካል ያለ ያህል ማለት ነው፡፡ "በስሜ የምትጠይቁትን ሁሉ አደርገዋለሁ፡፡ ማናቸውንም ነገር በስሜ ብትጠይቁ አደርገዋለሁ፡፡" ያንን ስም በምንጠቀምበት ጊዜ ኢየሱስ ክርስቶስን በወቅቱ ካለው ችግራችን ጋር ማገናኘታችን ነው፡፡ ስለዚህ የኃይል ሁሉ ምንጭ ከሕይወታችንና ከሚያጋጥሙን ችግሮቻችን ጋር ተያይዟል ማለት ነው፡፡

## ምእራፍ አስራ ሁለት

## የእምነት እንቅፋቶች

ምንጊዜም እምነት ከምስክርነታችን ከኑዛዜአችን (ከአዋጃችን) በላይ መሆን አይቻለውም፡፡ እዚህ ላይ ኑዛዜ ስንል ስለ ኃጢአት የምናደርገውን ኑዛዜ ሳይሆን ቃሉን በአፋችን ስለ መመስከር ስለ ማወጅ መሆኑን ልብ ልትሉ ይገባል፡፡ እኛ ድካምን ውድቀትንና ሕመምን ካወጅን እምነትን እናጠፋዋለን፡፡ ነገር ግን በድፍረት ደዌያችንን ኢየሱስ እንደ ተሸከመ ካወጅንና አዋጃችንን ጸንተን ከያዝን እግዚአብሔርን ወደ ችግራችን ትዕይንት እናመጣዋለን፡፡

አንዳንዴ እውቀት ማጣት ድፍረት የተሞላ አዋጅን እንዳናውጅ እንቅፋት ይሆንብናል፡፡ ከምናውቀው እውቀት በላይ በቃሉ ላይ መቆም ወይም ቃሉን ተግባራዊ ማድረግ አንችልም፡፡ እምነት ቃሉን በማወቅ ውስጥ ያድጋል፡፡ ብዙ ጊዜ የመዋጀታችንን እንዲሁም ከመዋጀታችን ጋር የመጡ መብቶቻችንን አለማወቅ ለመጠራጠር ምክንያት ይሆኑብናል፡፡

## የመረዳት ጉድለት

አዲስ ፍጥረትነት ምን ማለት እንደ ሆነና በርግጥ ምን እንደ ሆነ አለማወቃችን የእምነት ሕይወታችንን ይገድባል፡፡ ብዙ ሰዎች የዘላለም ሕይወት እንዳላቸው አያውቁም፡፡ እነርሱ ራሳቸውን እንደ አንድ ከ"ኃጢአቱ እንደ ዳነ" ሰው ብቻ አድርገው ያያሉ፡፡ ብዙዎች

ውስጠ እግዚአብሔር ተኮር አይደሉም፡፡ በክርስቶስ ውስጥ ያላቸውን ስፍራና ክርስቶስ በእነርሱ ውስጥ ያለውን ስፍራ ያላቸው የመረዳት ጉድለት ስለ ጽድቅ ምንነትና ስለ ሰጣቸው ነገር ያላቸው የመረዳት ጉድለት ከማንኛውም ነገር የበለጠ ብዙዎችን በቀንበር ሥር ቀፍድዶ ይዟቸዋል፡፡

እኛ በክርስቶስ ውስጥ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ መሆናችንን ካወቅን ከኖርንበት ጠባብ ከሆነው ከውድቀትና ድካም ስፍራ ወጥተን ወደ ወሰን የለሹ የእግዚአብሔር ሙላት እንገባለን፡፡ የኢየሱስን ስም የመጠቀም ሕጋዊ መብታችንን አለመረዳታችን በቀንበር ሥር ያሳድረናል ደግሞም የደካማነት ስሜት እንዲያጠላብን ያደርጋል፡፡ ነገር ግን ስሙ ምን ማድረግ እንደሚችል ስናውቅ ሰይጣንን ማሸነፍና ድልን ማጣጣም እንችላለን፡፡

ስለ አዋጅ ያላቸው የእውቀት አናሳነት ለብዙዎች ውድቀት ምክንያት ነው፡፡ የእኛ አዋጅ ከእምነታችን ጋር እጅ ለእጅ ተያይዞ ይጓዛል፡፡ በተለያየ ቀንበር ሥር የተያዝንበት ምክንያት በቃሉ ላይ መቆም ወይም ቃሉን ተግባራዊ የማድረግ እውቀት እጦት ውስጥ ስለ ተዘፈቅን ነው፡፡ የሚያስፈልገን የእግዚአብሔር ቃል የሚለው ላይ መቆም ወይም ተግባራዊ ማድረግ ሆኖ ሳለ እኛ ግን ለማመን እንጥራለን እንፍጨረጨራለን ንሞክራለን፡፡

እኛ ያ ቃል እውነት መሆኑን ካወቅን ቃሉ እውነት በመሆኑ በቃሉ ላይ እንቆማለን ወይም ተግባራዊ እናደርገዋለን በሕይወታችንም እውን ይሆናል፡፡ ትክክለኛ እምነት የቃሉ እውቀት ልጅ ነው፡፡

## ሁለት አዋጆች

እምነታችን በአዋጆቻችን ይለካል ወይም ይመዘናል፡፡ ለጌታ ሥራ ጠቃሚነታችንም በአዋጆቻችን ይለካል ወይም ይመዘናል፡፡ አሁን ይሁን ወይም በኋላ ያወጅነውን ሆነን መገኘታችን አይቀርም፡፡ ስለዚህም የልባችን አዋጅና የአንደበታችን አዋጅ አለ፡፡ የአንደበታችን ወይም የከንፈራችን ቃል ከልባችን አዋጅ ጋር ፈጽመው አንድ ሲሆኑ ሲስማሙና ሁለቱም በአንድነት የእግዚአብሔርን ቃል ሲያውጁ ያን ጊዜ በጸሎት ሕይወታችን ኃይለኞች እንሆናለን፡፡

ብዙ ሰዎች አሉታዊ አዋጅ አላቸው፡፡ እነርሱ ሁልጊዜ ያልሆኑትን ይናገራሉ ድካማቸውን ውድቀታቸውን የገንዘብ እጦታቸውን የብቃት እጥረታቸውን የጤንነት ጉድለታቸውን ይናዘዛሉ ወይም ያውጃሉ፡፡ ወዳወጁትም ልክ ይወርዳሉ፡፡ አዋጃችን እንደሚገዛን ጥቂቶች ብቻ የተገነዘብነው መንፈሳዊ ሕግ ነው፡፡ እኛ የእርሱን ጌትነት ስናውጅና ልባችንም በዚህ ሙሉ ለሙሉ ሲስማማ ራሳችንን በርሱ እንክብካቤ ሥር አሳልፈን መስጠታችን ነው፡፡ ይህም የስጋት ማብቂያ የፍርሐት ድል መደረግና የእምነት መጀመሪያ ነው፡፡

እርሱ ስለ እኛ ከሞት እንደ ተነሳ በትንሳኤውም ስለ እኛ ጠላትን ድል እንደነሣ ምንም አቅም እንዳይኖረው እንዳደረገ ስናምንና እንዲሁም ይህ የአንደበታችንና የልባችን አዋጅ

ሲሆን የእግዚአብሔር ኃይል ሆንን ማለት ነው፡፡ እኛ እርሱን የግል አዳኛችን አድርገን ስንቀበለውና ጌታችን አድርገን ስናውጅ አዲስ ፍጥረት ሆነናል፡፡ የዘላለም ሕይወት አግኝተናል፡፡ የልጅነትን ሥልጣን ተቀብለናል ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር አብረን የእግዚአብሔር ወራሾች ሆነናል፡፡

በርግጠኝነት ትንሳኤውን በተገነዘብንበት ወቅት የኃጢአት ጉዳይ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እልባት እንዳገኘ አውቀናል፡፡ ሰይጣንም ለእኛ ለዘላለም እንደ ተሸነፈ አውቀናል፡፡ ከመለኮትም ጋር አንድ እንደ ሆንን ተረድተናል፡፡ ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብም እንደ መጣን ተገንዝበናል፡፡ ይህ በአንድ ጊዜ ውስጣችን ላይሰርጽ ይችል ይሆናል፡፡ ሆኖም ቃሉን ስናጠናና ተግባራዊ ስናደርገው ስንኖርበትና በውስጣችን እንዲንሰራፋ ስንፈቅድ ቀስ በቀስ ነገር ግን በርግጥ የሕይወታችን እውነታ እየሆነ ይመጣል፡፡ ይህም እውነታ በአዋጃችን ውስጥ ያድጋል፡፡

እኛ እርሱ በለመለመ መስክ እንዳሳደረን በእረፍት ውኃ ዘንድ እንደ መራን እንናገራለን፡፡ ነፍሳችንን ከእርሱ ጋር ወደሚደረግ ጣፋጭ አስገራሚ ጎብረት እንደ መለሳት እንመሰክራለን፡፡ አዲስ ፍጥረት እንዳደረገን አሮጌው ነገር ሁሉ እንዳለፈ ሁሉ ነገር አዲስ እንደ ሆነ እንዲሁም አብ እኛን  የእግዚአብሔር ጽድቅ እንዳደረገን እናውጃለን፡፡

እኛም በዓለም ፊት ያለ ምንም ፍርሐት ከእርሱ ጋር አንድ መሆናችንንና አንድነታችንን እናውጃለን፡፡ እርሱ የወይን ግንድ እኛ ደግሞ ቅርንጫፎቹ መሆናችንን እንመሰክራለን፡፡ እርሱ በገሊላ ሲመላለስ በእርሱ ውስጥ የነበረው መለኮት ባሕርይ ተካፋይ መሆናችንንም እንናገራለን፡፡ እንግዲህ የእኛ አዋጆች መሆን ያለባቸው እነኚህና እነኚህን የመሳሰሉ ናቸው፡፡ እኛ ሰይጣን እንደ ተሸነፈ አጋንንታትም በአንደበታችን ላለው ለኢየሱስ ስም እንደ ተገዙ ደቄም ሕያው በሆነው በውስጣችን ባለው በክርስቶስ ሕልውና ፊት ሊኖርና ሊቆም እንደማይችል ወደ ማወቅ መጥተናል፡፡

እንግዲያስ አሁን ቃሉ በሚያስተምረን ላይ ለመቆም ወይም ተግባራዊ ለማድረግ እንደፍራለን፡፡ እኛም ቃሉ ስለ እኛ የተናገረው እውነት መሆኑን ተገቢ ስፍራችን ላይ በመቆም ለማወጅ እንደፍራለን፡፡ ከውድቀት ከድካም ከብቃትና ከችሎታ አልባነት አዋጅ ጋር ፈጽመን ተለያይተናል፡፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር ብቃታችንና ችሎታችን ሆኖልናልና፡፡ እግዚአብሔር ራሱ የእኛ ብቃትና ችሎታ ሆኗልና የአዲስ ኪዳን አገልጋይ እንድንሆን አብቅቶናል፡፡ እርሱ ውድቀት ከነገሰበት አሮጌው ዓለም አውጥቶ ድል ሃሴትና ሰላም ወደ ነገሰበት አዲስ ዓለም አስገብቶናል በማለት እናውጃለን፡፡ እኛ ይህን ስናውጅና ቃሉ ላይ ስንቆም ወይም ተግባራዊ ስናደርግ እምነታችን ያድጋል ደግሞም መዋጀታችን እውን ይሆናል፡፡

ትክክለኛ አዋጅ

ኢየሱስ "እኔ ከራሴ አልተናገርሁምና ነገር ግን የላከኝ አብ እርሱ የምለውን የምናገረውንም ትእዛዝ ሰጠኝ።" ዮሐንስ 12፥49። ኢየሱስ ያከናወናቸው ማንኛውም ፈውሶች ከአባቱ ተስተካክሎና ተሠርቶ ከመጣ ቃል ነው። የተናገረው የትኛውም ቃል የአባቱን ቃል ነው። ኢየሱስ ማንነቱን ያውቃል ስፍራውን ያውቃል መሥራት ያለበትም ምን እንደ ሆነ ጠንቅቆ ያውቃል። እርሱ በመልእክቱ ሁል ጊዜ አዎንታዊ ነው። የሚናገረው ቃል ሁሉ የአባቱ ቃል እንደ ሆነም ያውቃል። የልጅነት ስፍራውን ወስዶ ድርሻውን ተግብሯል። ያለማቋረጥም ልጅነቱን ያውጅ ነበር።

ኢየሱስ ሁል ጊዜ ማን መሆኑን ያውጅ ነበር። እርሱ "እኔ መልካም እረኛ ነኝ። እኔ የሕይወት እንጀራ ነኝ። እኔ የሕይወት ውኃ ነኝ። እግዚአብሔር አባቴ ነው። እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ።" ይል ነበር። በዮሐንስ 5፥19-30 ኢየሱስ ስለ ራሱ አስር መግለጫዎችን ሰጥቷል። በትክክልም እውነተኛ አዋጆች ነበሩ እያንዳንዳቸውም እርሱን ከመለኮት ጋር ያያይዙታል። እርሱ የአባቱን ቃል ብቻ ይናገር ነበር። ዮሐንስ 7፥29 "እኔ ግን ከእርሱ ዘንድ ነኝ እርሱም ልኮኛልና አውቀዋለሁ።"

እርሱ ማንነቱን ብቻ አልነበረም ያወጀው ነገር ግን ሰው አዲስ ፍጥረት ከሆነ በኋላ ምን እንደሚሆን በድፍረት ተናግሮም ነበር። ዮሐንስ 15፥5 "እኔ የወይን ግንድ ነኝ እናንተም ቅርንጫፎቼ ናችሁ።" ዮሐንስ 7፥38-39 "በእኔ የሚያምን መጽሐፍ እንዳለ የሕይወት ውኃ ወንዝ ከሆዱ ይፈልቃል ብሎ ጮኸ። ይህን ግን በእርሱ የሚያምኑ ሊቀበሉት ስላላቸው ስለ መንፈስ ተናገረ ኢየሱስ ገና ስላልከበረ መንፈስ ገና አልወረደም ነበርና።" በጴንጤ ቆስጤ ቀን እንዴት አውን ሆኖ የተገለጠ ድንቅ ዓይነት አዋጅ ነበር!

ዮሐንስ 8፥54-55 "ኢየሱስም መለሰ አለም ፦ እኔ ራሴን ባከብር ክብሬ ከንቱ ነው የሚያከብረኝ እናንተ አምላካችን የምትሉት አባቴ ነው አላወቃችሁትምም እኔ ግን አውቀዋለሁ። አላውቀውም ብል እንደ እናንተ ሐሰተኛ በሆንሁ ዳሩ ግን አውቀዋለሁ ቃሉንም እጠብቃለሁ።" ዮሐንስ 17፥5 "አሁንም አባት ሆይ ዓለም ሳይፈጠር በአንተ ዘንድ በነበረኝ ክብር አንተ በራስህ ዘንድ አክብረኝ።" ይህ እጅግ አስደናቂ ምስክርነት ነው።

ዮሐንስ 17፥26 "ስምህን አስታወቅኋቸው አስታውቃቸውማለሁ።" ኢየሱስ እግዚአብሔር ሊቀበል ያለውን አዲስ ስም አውቋል። ዮሐንስ 17፥6 "ከዓለም ለሰጠኸኝ ሰዎች ስምህን ገለጥሁላቸው።" እኔ ኢየሱስ እየተናገረ ያለው አዲስ ስም "አብ ወይም አባት" እንደ ሆነ አምናለሁ። ከዚህ ቀደም ሲል ማንም "አባት" ብሎ ጠርቶት አያውቅምና።

ዮሐንስ 9፥35-36 "ኢየሱስም ወደ ውጪ እንዳወጡት ሰማ ሲያገኘውም ፦ አንተ በእግዚአብሔር ልጅ ታምናለህን? አለው። እርሱም መልሶ ፦ ጌታ ሆይ በእርሱ አምን ዘንድ ማን ነው? አለ።" በቁጥር 37 ላይ ዓይነ ስውር ለነበረው ሰው "አየተኸዋልም ከአንተ ጋርም የሚናገረው እርሱ ነው።" አለው። ኢየሱስ በእንደዚህ ዓይነት መልክ

ማንነቱን ይገልጽ ያውጅ ነበር። ኢየሱስ ሁልጊዜ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን በግልጽ ይናገር ነበር። በዮሐንስ 4፥26 ላይ ሌላ አስገራሚ አዋጅ እንሰማለን። እርሱም ከሰማሪያዊቷ ሴት ጋር እየተነጋገረ ሳለ እርሱ መሲህ መሆኑንና የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ያወጀበት ነበር።

## ኢየሱስ ማንነቱን ያውቅ ነበር

ኢየሱስ ያከናወናቸው የትኛዎቹም ተአምራቶች የተከናወኑት በኢየሱስ አንደበት በነበሩ የአባቱ ቃል ነበር። ኢየሱስ የተገለጠ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነበር። ዮሐንስ 4፥34 "የእኔስ መብል የላከኝን ፈቃድ አደርግ ዘንድ ሥራውንም እፈጽም ዘንድ ነው።" ዮሐንስ 5፥30 "እኔ ከራሴ አንዳች ላደርግ አይቻለኝም እንደ ሰማሁ እፈርዳለሁ ፍርዴም ቅን ነው የላከኝን ፈቃድ እንጂ ፈቃዴን አልሻምና።" ዮሐንስ 6፥38 "ፈቃዴን ለማድረግ አይደለም እንጂ የላከኝን ፈቃድ ለማድረግ ከሰማይ ወርጃለሁ።" ዮሐንስ 8፥29 "የላከኝም ከእኔ ጋር ነው እኔ ደስ የሚያሰኘውን ዘወትር አደርጋለሁና"

እንዴት ድንቅ የሆነ የጌታ መገለጫያ ስዕል ነው! እርሱ የተለየ ግላዊ መሻት ወይም ምኞት አልነበረውም ለግሉ ሊያሳካው የሚፈልገውም አንዳችም ነገር አልነበረም። እንዲያው የአባቱን ፈቃድ ይፈጽም ነበር ይኸውም አባቱን "እኔን ያየ አብን አይቶአል" (ዮሐንስ 14፥9) እስኪል ድረስ መግለጥ ነበር። እኛም ከዓለማዊ ምኞት በራቅን ቁጥር ዓለማዊ መሻታችን ሲቀንስ አብ ራሱን በሙላት ለእኛ ይገልጣል። በአንደበታችን ያለ ቃል ፍጹም አስገራሚ የሆነ በኢየሱስ አንደበት በነበረ ጊዜ ያከናውን የነበረውን ድንቅ ነገር ይፈጽማል።

ለራስ ብቻ መጠማት ይገድባል። ስግብግብ ሰው ውሱን ይሆናል። ነገር ግን በቃሉ የሚኖርና ቃሉ በእርሱ የሚኖር ደግሞም ቃሉን ተግባራዊ የሚያደርግና በቃሉ ላይ የሚቆም አብን የሚገልጥ እርሱ ብቻ ይሆናል። እኛ በእግዚአብሔር ቃል ላይ ስንቆም አብን ወይም አባትን ገለጥን ማለት ነው።

## የተሳሳተ አዋጅ

አሉታዊ አዋጃችን እስረኛ አድርጎ እንዳስቀመጠን የምናውቅ ጥቂቶቻችን ነን። ነጻ የሚያወጣን ግን ትክክለኛ አዋጃችን ብቻ ነው። በእኛ ውስጥ ኃይልን ወይም ድክመትን የሚገነባው አስተሳሰባችን ብቻ ሳይሆን ከአንደበታችን የሚወጣው ቃልና የምናደርጋቸው ውይይቶች ጭምር ናቸው። ቃሎቻችን በእምነት መንግስት ውስጥ መገበያያ ገንዘብ ናቸው። ቃሎቻችን ወጥመድ ሆነው በምርኮኝነት አስረው ሊያስቀምጡን ወይም ነጻ አውጥተውን በሌሎች ሕይወት ሳይቀር ኃያል እንዲሆን ያደርጋሉ።

እኛ ሳናውቀው ያንኑ ያመንነውን እናውጃለንና ውስጣዊ ማንነታችንን በትክክል የሚገዛው በአንደበታችን የምናውጀው ነው። ስለ በሽታ የምናወራ ከሆንን ምክንያቱ በሽታን

ማመናችን ነው፡፡ ድካምንና ውድቀትን የምናወራ ከሆን ምክንያቱ በድካምና በውድቀት ማመናችን ነው፡፡ የእምነት ሰዎች ከተሳሳተ አዋጅ ጋር ምን ግንኙነት እንዳላቸው ያስገርማል፡፡ አጥብቀው በካንሰር በጨጓራ አልሰር በቲዩበር ክሎሲስና ሌሎች የማይድኑ ደዌዎች ተብለው በሚጠሩት ላይ ያምናሉ፡፡ በደዌው ላይ ያላቸው እምነትም ከፍ ብሎ እነርሱን ሙሉ ለሙሉ ወደ እሚጨቁንበትና ወደሚገዛበት ከፍታ ነጥብ ይደርሳል፡፡ እነርሱም የእርሱ ፍጹም ባርያ ይሆናሉ፡፡

ድካማቸውን የማወጅ ልምድ አዳብረዋልና አዋጃቸው ለድካማቸው ብርታትን ይጨምርለታል፡፡ እምነት እንደ ጎደላቸው ያውጃሉ ስለዚህ በጥርጣሬ ይሞላሉ፡፡ ፍርሃታቸውን ያውጃሉና የበለጠ ፈሪዎች ይሆናሉ፡፡ የደዌ ፍርሃታቸውን ያውጃሉ ደዌውም በአዋጃቸው ስር ያድጋል፡፡ እጥረት እንዳለባቸው ያውጃሉና በሕይወታቸው የበላይነት የሚጨብጥ የእጥረት መግዘፍን ይገነባሉ፡፡

እኛ ከምናውጀው አዋጃችን በላይ በፍጹም ከፍ ልንል እንደማንችል ስንገነዘብ በርግጥ እግዚአብሔር በትክክል እኛን መጠቀም ወደ እሚችልበት ስፍራ ደርሰናል ማለት ነው፡፡ በመገረፉ ቁስል መፈወሳችሁን አውጁና አዋጃችሁን በጽናት ያዙ ያን ጊዜ ምንም ዓይነት ደዌ በፊታችሁ አይቆምም፡፡ አመንንም አላመንንም ልክ ኢየሱስ በሉቃስ 8፥11 ላይ እንዳለው ቃሎችን እየዘራን ነው፡፡ "ዘሩም የእግዚአብሔር ቃል ነው፡፡" ዘሪ ዘርን ሲዘራ ወጣ ዘሩም የእግዚአብሔር ቃል ነው፡፡

ልንዘራ የሚገባንም ዘር ይኸው ነው፡፡ ሌሎች ግን የስሜት እውቀት የሆነውን ፍርሃትንና ጥርጣሬን እየዘሩ ነው፡፡ እኛ የእግዚአብሔርን ቃል ስናውጅ በአጽንኦትም "በመገረፉ ቁስል ተፈውሻለሁ" ስንል ወይም "አምላኬም እንደ ባለ ጠግነቱ መጠን የሚያስፈልገኝን ሁሉ ይሞላብኛል" በማለት ስናውጅና አዋጃችንንም አጽንተን ስንጠብቅ አርነታችንን የምናየው ያኔ ነው፡፡

የእኛ ቃሎች በሌሎች ላይ እምነትን ወይም ጥርጣሬን ያስከትላል፡፡ ራዕይ 12፥11 "እነርሱም ከጠቦቱ ደም የተነሣ ከምስክራቸውም ቃል የተነሣ ድል ነሱት" ሲል ያውጃል፡፡ በምስክርነታቸው ውስጥ ባለው የእግዚአብሔር ቃል ድል ነሱት፡፡ ዲያብሎስን በቃላቸው አሸነፉት ማለት ነው፡፡ ኢየሱስ በምድር በነበረው አገልግሎቱ ዘመን አብዛኛዎቹ በሽተኞች የተፈወሱት በቃል ነበር፡፡

እምነትን በተሞሉ ቃሎች እግዚአብሔር ዩኒቨርሱን ፈጠረ፡፡ ኢየሱስ "እምነትሽ አድኖሻል" አለ፡፡ ሟቹን አልአዛርን ደግሞ "ወደ ውጭ ና" አለው ቃሎቹም ሟቹን አስነሣ፡፡ ሰይጣን ከእግዚአብሔር ቃል የተነሣ ተሸነፈ በቃሉም ተገረፈ፡፡ የእኛ አንደበት የእግዚአብሔርን አርነት ከሰማይ አዚህ በምድር ላይ ላለው ሰው ፍላጎት ለማሟላት ማጓጓዣ መንገድ ይሆናል፡፡ እኛ የእግዚአብሔርን ቃል ተጠቅመን "አጋንንት በኢየሱስ ስም ውጣ፡፡"

እንላለን፡፡ ኢየሱስ "በስሜ አጋንንትን ታወጣላችሁ በስሜ እጆቻችሁን በድውያን ላይ ትጭናላችሁ እነርሱም ይፈወሳሉ" ብሏል፡፡

ሁሉም ነገር የተከናወነው የሚከናወነውም በቃሉ ነው! እጆች ስሜትን ከማስተላለፍ ባሻገር ሌላ ሚና አላቸው ወይ ብዬ እጠይቃለሁ፡፡ የሚፈውሰው ቃሉ ነውና፡፡ ኢየሱስ "ማናቸውንም በስሜ ይገባኛል የምትሉትን ሁሉ እኔ አደርገዋለሁ" ወይም "ማናቸውንም ነገር በስሜ ብትጠይቁ እኔ አደርገዋለሁ" አለ፡፡ (አማርኛው "ብትለምኑ" እንግሊዘኛው ግን "ብትጠይቁ" ይላል እነኚህ ሁሉቱም በግሪኩ "ይገባኛል" የሚል ትርጉም ይዘዋል)

እኛ ልክ ጴጥሮስ መልካም በሚሉአት ስፍራ ይገባዋል ብሎ አንካሳውን "በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሳና ተመላለስ" አንዳለውና የተገባውን እንደ ሰጠው እናደርጋለን፡፡ የእግዚአብሔር ቃላት ያንን ሰው ፈወሱት፡፡ እንግዲህ እኛ ቃሎቹን አዋጃችን አድርገናቸዋል፡፡ ደግሞም አዋጃችንን አጽንተን እንጠብቃለን፡፡ በአዋጃችን ተሸናፊ መሆንን አሻፈረኝ ብለናልና፡፡

ዮሐንስ 8፥32 "እውነትንም ታውቃላችሁ እውነትም አርነት ያወጣችኋል" ወይም ዮሐንስ 8፥36 "እንግዲህ ልጁ አርነት ቢያወጣችሁ በእውነት አርነት ትወጣላችሁ" ይላል፡፡ እኛም ልጁ አርነት እንዳወጣን አውቀናልና እናውጀዋለን፡፡ ኢየሱስ የአዋጃችንም ሊቀ ካህን ነው፡፡ ክርስቶስ የሰው ጠላቶች የሆኑትን ሰይጣንን ኃጢአትን በሽታን ፍርሐትንና ጉድለትን አሸንፎ ገዝቶታል፡፡ እነዚህን ሁሉ ምርኮኛ አድርጎ ሰውን ነጻ ለቅቆታል፡፡

ዕብራውያን 4፥14 የእምነታችንን አዋጅ ጸንተን እንድንጠብቅ ነግሮናል፡፡ (አመት)፡፡ "እንግዲህ ወደ ሰማያት ያረገ ታላቅ ሊቀ ካህናት የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ስላለን እምነታችንን አጥብቀን እንያዝ፡፡" (አመት) አዲሱ ኪንግ ጄምስ እትም አዋጃችንን አጥብቀን እንያዝ ይላል፡፡ ይህ አዋጅ የእምነት ንግግር ነው፡፡ በጠላት ላይ ያለን ድላችን ነው፡፡ እርሱ ማረጋገጫችን ነው፡፡

ቆላስያስ 2፥5ን አንደኛው ትርጉም "ምንም እንኳ እናንተ እንደምትሉት ከእናንተ በአካል ብርቅም በመንፈስ ግን ከእናንተ ዘንድ ተገኝቼ መልካም የሆነውን ሥርዓታችሁንና ቀጣይ ጽናታችሁን እያየሁ ደስ እሰኛለሁ" ሲል ይነበባል፡፡ "ቀጣይ ጽናት" የሚለው ቃል የማያቋርጥ የድል አዋጅ ማለት ነው፡፡ እኛ ከድልና ከአሸናፊነት አዋጅ በስተቀር ሌላ አዋጅ አናውጅም፡፡

ሮሜ 8፥37 "በዚህ ሁሉ ግን በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን፡፡" ኢየሱስ ከእርሱ ጋር የተዋጉትን አለቅነትንና ሥልጣናትን ገፎ በግልጽ አሳፍሮአቸዋል፡፡ ይህ ከኮኒቤርስ ትርጉም ላይ የተወሰደ የቆላስያስ 2፥15 ትርጉም ነው፡፡ እኛ የተሳሳተ ዓይነት አዋጅ ማወጅን ማቆምና እንዴትና ምንን ማወጅ እንዳለብን ፈጥነን መማርና መጀመር አለብን፡፡ እኛ እርሱ ያለንን እንደ ሆንን ማወጅ መጀመርና አዋጃችንን በማንኛውም ተጻራሪ መረጃ ፊት አጥብቀን መያዝ አለብን፡፡ እንዲህ ካደረግን፡-እኛ ድካምን ወይም

ለድካም እውቅና መስጠትን አሻፈረኝ ብለናል። እኛ ከማንኛውም የተሳሳተ አዋጅ ጋር ጉዳይ የለንም ብለናል። እኛ እርሱ ያለንን ነን። እኛ ያለ ፍርሐት በንቃት የትኛውም የእግዚአብሔር ቃል እንደማይከሽፍ አዋጃችንን አጥብቀን ይዘናል ማለት ነው።

## ምእራፍ አስራ ሦስት

## ጸሎት

ጸሎት ኃይላችንን ከአብ ወይም ከአባታችን ጋር ማገናኘት ማለት ሲሆን የእርሱንም ፈቃድ በምድር ላይ በማከናወን ከእርሱ ጋር ኅብረት ማድረግ ማለት ነው። እግዚአብሔር በእኛ ጸሎት ሕይወት ምክንያት የተወሰነ ይመስላል። አንድ ሰው የሚፈልገውን ማንኛውንም ነገር እግዚአብሔርን አንዲያደርግለት ካልጠየቀው በስተቀር እግዚአብሔር ምንም ማድረግ አይችልም። ይወሰናል ማለት ነው። ይህ ስለ ምን እንደ ሆነ አላውቅም። የዚህን ፍንጭ ዘፍጥረት 18 ላይ እግዚአብሔር ሰዶምና ገሞራን ከደም ኪዳን ወዳጁ አብርሃም ጋር ሳይነጋገር ሊያጠፋቸው ፈቃደኛ እንዳልሆነ በነበረው ውይይት ውስጥ እናገኘዋለን።

## ጸሎት በብሉይ ኪዳን ስር

በዘፍጥረት 18፥22-25 የተመዘገበው በብሉይ ኪዳን ጊዜ ስለ ነበረው ጸሎት በሚገባ የሚያብራራና ገላጭ ነው። አብርሃምም እግዚአብሔርን "በውኑ ጻድቁን ከኃጢአተኛው ጋር ታጠፋለህን? አምሳ ጻድቃን በከተማይቱ ውስጥ ቢገኙ በውኑ ሁሉን ታጠፋለህን? ከተማይቱንስ በእርስዋ ስለሚገኙ አምሳ ጻድቃን አትምርምን? ይህ ከአንተ ይራቅ ጻድቁን ከኃጢአተኛ ጋር ትገድል ዘንድ ጻድቁም እንደ ኃጢአተኛ ይሆን ዘንድ እንደዚህ ያለው አድራጎት ከአንተ ይራቅ። የምድር ሁሉ ፈራጅ በቅን ፍርድ አይፈርድምን?" አለው።

እዚህ ላይ አብርሃም በኪዳኑ የነበረውን ስፍራ መያዙ ነበር። አብርሃም እኛ በጥቂቱ ብቻ የተረዳነው መብትና ልዩ ጥቅም በኪዳኑ ውስጥ ነበረው። አብርሃም የነበረው ኪዳን ከያሕዌ ጋር የከበረ ነበርና ከእግዚአብሔር ጋር የመቆም ሕጋዊ መብት ሰጥቶታል። እርሱም በግልጽ "የምድር ሁሉ ፈራጅ በቅን አይፈርድምን?" በማለት ሲናገር እንሰማዋለን። ይህም ለሰዶምና ገሞራ ያደረገው ምልጃ ነው። በብሉይ ኪዳን ውስጥ ኪዳናቸውን የተረዱና ስፍራቸውን የያዙ ሰዎችን እናገኛለን።

ኢያሱ ዮርዳኖስን መክፈል ችሏል። ፀሐይን ጨረቃንና ከዋክብትን በሰማይ ላይ እንዳሉ እንዳይነቃነቁ ማዘዝ ችሏል። ኤልያስ መስዋእቱንና መሰዊያውን እንዲበላ እሳት ከሰማይ ማውረድ ችሏል። የዳዊት ኃያላን በጦርነታቸው ወቅት ፈጽመው ከሞት ተከልለዋል። ኪዳናቸውን እስካስታወሱ ድረስ ልዕለ ኃያላን ሆነዋል። የብሉይ ኪዳን ጸሎቶች በሙሉ በኪዳን ሰዎች በተግባር የተደረጉ ጸሎቶች ናቸው። እነርሱም መመለስ የነበረባቸው ጸሎቶች ስለ ነበሩ የጸሎት አቤቱታቸውን እግዚአብሔር መቀበል ነበረበት።

## ጸሎት በአዲስ ኪዳን ስር

አዲስ ኪዳን አዲስ ቃል ኪዳን ነው፡፡ አማኝ የጸሎት ኪዳን መብት አለው፡፡

ኢሳይያስ 43፥25-26 "መተላለፍህን ፦ ስለ እኔ ስል የምደመስስ እኔ ነኝ ኃጢአትህንም አላስብም፡፡ አሳስበኝ በአንድነትም ሆነን እንፋረድ እንድትጸድቅ ነገርህን ተናገር፡፡" ይላል፡፡ ይህም ቃል ኪዳኑን የሚጠብቅ የእስራኤል እግዚአብሔር ግድድር ነበር፡፡ አሁንም ለቤተ ክርስቲያን ያቀረበው ተግዳሮት ነው፡፡ እርሱ "አሳስቡኝ፡፡" ብሏል፡፡ በሌላ አባባል ጸሎትን አስመልክቶ በክብር የገባላችሁን የተስፋ ቃል አስታውሱት፡፡

በጸሎት ኃይለኛ የነበሩ ሰዎች ምንጊዜም እግዚአብሔርን ተስፋ የገባውን ቃል አስታውሰውት ጉዳያቸውን በሕጋዊ መንገድ በፊቱ ያቀርቡ ነበር፡፡ ስትጸልዩ ልክ እንደ ጠበቃ በዙፋኑ ፊት ቆማችሁ ጉዳያችሁን በአስቸኳይ አቅርቡ፡፡ ጠበቃ ቀደም ሲል ለተመሳሳይ ጉዳይ የተወሰነ ውሳኔንና ሕጉን በተደጋጋሚ ያቀርባል፡፡ እናንተም ቃሉን የቃል ኪዳኑን ተስፋ በማቅረብ መብታችሁን ጠይቁ፡፡

"አሳስበኝ በአንድነትም ሆነን እንፋረድ እንድትጸድቅ ነገርህን ተናገር፡፡" ኢሳይያስ 43፥26፡፡ ጉዳያችሁን በፊቱ ታቀርቡ ዘንድ እግዚአብሔር እየተገዳደራችሁ ነው፡፡ "ስለሚመጣው ነገር ጠይቁኝ ስለ ልጆቼና ስለ እጄ ሥራም እዘዙኝ፡፡" ኢሳይያስ 45፥11፡፡ ይህ ሊመጣ ላለው አዲስ ስርዓት ትንቢታዊ ቃል ነው፡፡ እርሱም የቀድሞዋን እስራኤልን አይመለከትም፡፡ የእናንተ ነውና፡፡

"ስለሚመጣው ነገር ጠይቁኝ" እነኚህ የወደፊት ጊዜያት ጉዳዮች ናቸው ምናልባትም ከሕይወታችሁ ከቤተሰባችሁ ከማኅበረሰባችሁ ወይም ከመንግስታችሁ ጋር የተያያዙ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ "ስለ እጄ ሥራም እዘዙኝ፡፡" ይህ በትክክል ከዮሐንስ 15፥7 ጋር አብሮ የሚሄድ ነው፡፡ "በእኔ ብትኖሩ ቃሎቼም በእናንተ ቢኖሩ የምትወዱትን ሁሉ ጠይቁ ይሆንላችሁማል፡፡"

"ጠይቁ" የሚለው ቃል የምትወዱትን የምትፈልጉትን ይገባኛል የምትሉትን "ስጠኝ" ወይም "አምጣ" ማለት ነው፡፡ እንደ ፍቅረኛ አጋር ወይም ሸሪክ እንጂ ትእቢት በተሞላ መልክ ታዝዛላችሁ ማለት አይደለም፡፡ ጉዳያችሁን በክብር በትህትና በፊቱ ታቀርባላችሁ፡፡ በየትኛውም የሕይወት ትዕይንት ውስጥ የእርሱን ወይም የእግዚአብሔርን ድርሻ ትኩረት ትጠራላችሁ፡፡

ባለማቋረጥ መጠቀም ያለባችሁ የእግዚአብሔር ቃል ኢሳይያስ 55፥11 ይሁን፡፡ ቁጥር 9ኝና 10ን በጥንቃቄ አንብቡ "ሰማይ ከምድር ከፍ እንደሚል እንዲሁ መንገዴ ከመንገዳችሁ አሳቤም ከአሳባችሁ ከፍ ያለ ነው፡፡" ቁጥር 10 "ዝናብና በረዶ ከሰማይ እንደሚወርድ ምድርን እንደሚያረካት ታበቅልና ታፈራም ዘንድ አንደሚያደርጋት ዘርንም ለሚዘራ እጆራንም ለሚባላ እንደሚሰጥ እንጂ ወደ ሰማይ እንደማይመለስ" 11 "ከአፌ የሚወጣ

ቃሌ እንዲሁ ይሆናል የምሻውን ያደርጋል የላክሁትንም ይፈጽማል እንጂ ወደ እኔ በከንቱ አይመለስም።"

ይህ የጸሎት ዋነኛ የጀርባ አጥንት ነው። ከእግዚአብሔር አፍ የወጣ ቃል ወደ እርሱ በከንቱ አይመለስም። ኤርምያስ 1፥12 "እፈጽመው ዘንድ በቃሌ እተጋለሁና" ከእርሱ ጋር ለመቆም እስከ ደፈራችሁ ድረስ ቃሉን ይፈጽማል።

## የያሕዌ አሳሳቢዎች

"እናንተ እግዚአብሔርን የምታሳስቡ ኢየሩሳሌምን እስኪያጸና በምድርም ላይ ምስጋና እስኪያደርጋት ድረስ አትረፉ ለእርሱም ዕረፍት አትስጡ።" ኢሳይያስ 62፥7። እዚህ ላይ እግዚአብሔር ሥራቸው እነኚህን የተስፋ ቃሎችና ርግጠኛ መግለጫ መረጃዎች ይዞ በጌታ ጎሊና ፊት የሚያቀርቡ "አሳሳቢዎች" እንዳሉ እያመለከተ ነው።

"ማንም በጸሎት ስምህን አይጠራም አንተንም ለመያዝ የሚሞክር የለም ፊትህን ከእኛ ሰውረሃል ስለ ኀጢአታችንም ትተኸናል።" ኢሳይያስ 64፥7 (አመት)

ዳንኤል ለመጸለይ ራሱን አነሳሳ። ራሱንም ለጸሎት ሰጠ። የእግዚአብሔርንም ትኩረት በኤርምያስ በኩል ለእስራኤል ተሃድሶ ይሆናል የባቢሎን ምርኮኝነታቸው አብቅቶ እንደገና ወደ ተስፋይቱ ምድር ይመለሳሉ ሲል ወደ ተናገረው የተስፋ ቃል ጠራ። ዳንኤል ዘጠኝን በጥንቃቄ አንብቡ። ስይጣን ጸሎትን ለመቃወም በመንገድ ላይ ይቆማል። በዳንኤል 10፥20 ላይ የተመዘገበውን በመላእክትና በአጋንንታት መካከል የተደረገውን የውጊያ ታሪክ አንብቡ።

"ወደ እኔ ጩኽ እኔም እመልስልሃለሁ አንተም የማታውቀውን ታላቅና ኃይለኛ ነገርን አሳይሃለሁ።" ኤርምያስ 33፥3። እግዚአብሔር ሊባርከን ይፈልጋልና ከእርሱ ጋር በጸሎት ሕይወታችን ያለንን ጎብረት እየተገዳደረ ነው። የመዝሙር 78፥41 (ኪንግ ጄምስ) "ተመለሱ እግዚአብሔርንም ፈተኑት የእስራኤልንም ቅዱስ ወሰኑት።" ይላል። እኛም ይህንን አድርገናል። እኛም በጸሎት ሕይወታችን ወስነነዋል። እኛ ከእግዚአብሔር ጋር ጎብረትና ትብብር አንዲኖረን የተገባልንን ታላቁን የተስፋ ቃል ሳንነካውና ሳንገነዘበው በከንቱ እንዲያልፈን ለቅቀነዋል።

ኢየሱስ የጸሎት አስተማሪ ብቻ አልነበረም ራሱ ጸሎት ነበር እንጂ። እርሱ ስለ ጸለየላቸው ነገሮችና እርሱ ስለ ጸለየበት ዘዴ የተመዘገበና የተሰጠን ነገር ቢኖር ምኞቴ ነበር። እኛ በተደጋጋሚ እንዲያውም አንዳንዴ ምሽቱን በሙሉ በጸሎት ከአባቱ ጋር ለማሳለፍ ብዙ ሕዝብን ትቶ እንደሚሄድ እናውቃለን። ሆኖም በርግጠኝነት ጎብረት ለማድረግ ይሁን ወይም ለጠፋው ዓለም እየጸለየ ይሁን ልንናገር አንችልም።

## የስምምነት ጸሎት

ስለ ስምምነት ጸሎት ማቴዎስ 18፥18-20 ጥሩ ስዕል ይሰጠናል፡፡ "እውነት እላችኋለሁ በምድር የምታስሩት ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል በምድርም የምትፈቱት ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል፡፡ ደግሞ እላችኋለሁ ከእናንተ ሁለቱ በምድር በማናቸውም በሚጠይቁት ነገር ሁሉ ቢስማሙ በሰማያት ካለው ከአባቴ ዘንድ ይደረግላቸዋል፡፡ ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁና፡፡"

ይህ ቃል እጅግ አስገራሚ ነው፡፡"ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁና፡፡" ይህ ከጌታ ጋር የአፈጻጸም ጉባኤ ማድረግ ማለት ነው፡፡ እኛ በጋራ ሥራን ለመሥራት በሕልውናው ፊት ተቀምጠን እናቅዳለን እንወያያለን ከዚያም እንጸልያለን ምክንያቱም እርሱ "ሁለቱ በምድር በማናቸውም በሚጠይቁት ነገር ቢስማሙ" ብሎናልና፡፡ የቡድኑ ቁጥር በጣም ትንሽ ሊሆን ይችላል፡፡ ባልና ሚስት ብቻ ሊሆኑ ይችላሉ ነገር ግን በሚጠይቁት ማንኛውም ነገር ከተስማሙ ከሰማይ አባት ዘንድ ይደረግላቸዋል፡፡ ይህ ድንቅ ነው፡፡ ማንኛውም አማኝ በጸሎት አብሮት የሚሆንና የሚስማማ አንድ ሰው ማግኘት ይኖርበታል፡፡ እኛ በጸሎት ፕሮግራም ላይ ልንጸልይባቸው የምንፈልገውን ጉዳይ ዝርዝርና ሰዎች በማዘጋጀት በአባታችን ፊት ማቅረብ አለብን፡፡

"በእኔ ብትኖሩ ቃሎቼም በእናንተ ቢኖሩ የምትወዱትን ሁሉ ጠይቁ ይሆንላችሁማል፡፡ ብዙ ፍሬ ብታፈሩና ደቀ መዛሙርቴ ብትሆኑ በዚህ አባቴ ይከበራል፡፡" ዮሐንስ 15፥7-8፡፡ እኛ ዳግም ከተወለድን በእርሱ እንኖራለን፡፡ የእርሱ ቃል ሕይወታችንን በሚገዛበት መጠን ልክና እኛም ቃሉን ተግባራዊ በምናደርግበት መጠን ልክ በእኛ ውስጥ ይኖራል፡፡

የእምነት ችግር ጸሎት ውስጥ አይገባም፡፡ በእርሱ የሚኖሩ ያለ ጥርጥር እምነት እንዳላቸው ይታመናል፡፡ ወደ ቤተሰብነት ለመቀላቀል እምነት አስፈልጓል፡፡ እኛ አሁን በቤተሰብ ውስጥ ነንና ስለዚህ ያለብን የእምነት ችግር አይደለም፡፡ ችግር ካለም ቃሉ በውስጣችን በሙላት ያለመኖሩ ጉዳይ  ነው፡፡ ቃሉን የምንኖር ከሆነ ለመጸለይ ስንነሳ በሙላት በውስጣችን ያለው ቃል በአንደበታችን የእርሱ ቃል ይሆናል፡፡ ልክ በጌታ አንደበት እንደ ነበረው የአብ ቃል ይሆናል ማለት ነው፡፡

## እንዴት እንጸልይ?

"እኔ መረጥኋችሁ እንጂ እናንተ አልመረጣችሁኝም አብም በስሜ የምትጠይቁትን ሁሉ እንዲሰጣችሁ ልትሄዱና ፍሬ ልታፈሩ ፍሬአችሁም ሊኖር ሾምኋችሁ፡፡" ዮሐንስ 15፥16፡፡ እዚህ ላይ ጸሎት በኢየሱስ ስም ወደ አብ መጸለይ እንዳለበት ያሳያል፡፡ ይህ መለኮታዊ ሥርዓት ነው፡፡ ይህ መግለጫ በውስጡ እግዚአብሔርን ወደ ፋይናንሳችን ወይም በቤታችን ውስጥ ስላለ የትኛውም መሻት በንግዳችን ወይም በሕዝባችን ውስጥ ወዳሉ ሁኔታዎቻችን የማምጣት ብቃትን ጠቅልሎ ይዟል፡፡

"አብም በስሜ የምትጠይቁትን ሁሉ እንዲሰጣችሁ" እኛ ወደ ኢየሱስ አንጸልይም። የምንጸልየው በኢየሱስ ስም ወደ አብ ነው። ኢየሱስ በትክክል ሙሉ ውክልናን ሰጥቶናል። ይህ ማለት እኛ ኢየሱስ ማድረግ የሚችለውን ማድረግ እንችላላን ማለት ነው። እንዲህ ማለትም የኢየሱስ ስም ወደ ሕልውናው እንድንሄድና ጸሎታችን እንዲመለስ መብት አጎናጽፎናል ማለት ነው። ኢየሱስ ጸሎታችንን ይደግፋል እንዲፈጸምም ያደርጋል።

"በዚያ ቀንም ከእኔ አንዳች አትጠይቁም። እውነት እውነት እላችኋለሁ አብ በስሜ የምትጠይቁትን ሁሉ ይሰጣችኋል። እስከ አሁን በስሜ ምንም አልጠየቃችሁም ደስታችሁ ፍጹም እንዲሆን ጠይቁ ትቀበሉማላችሁ።" ዮሐንስ 16፥23-24። እኛ በኢየሱስ ስም ወደ አብ እንጸልያለን። እኛ ከጌታ ጋር ጉዳያችንን መነጋገርና ኅብረት ማድረግ እንችላለን ነገር ግን ሕጋዊ መሰረትን የያዘ ጸሎትን በተመለከተ ጉዳይ በኢየሱስ ስም ወደ አብ እንመራዋለን።

እዚህ ላይ ምንም ዓይነት አስቸጋሪ ጉዳይ የለም። ከእርሱ ጋር እንመላለሳለንና አባታችን እግዚአብሔርን ከፈቃዱ ውጭ የሆነ አንዳችም ነገር አንጠይቀውም። በእዚህ ግንኙነት ውስጥ "እምነት" የሚል ቃል አልተጠቀሰም። እኛ ወደ ቤተሰብ ውስጥ ለመምጣት እምነት አለን ስለዚህ ኢየሱስ የፈጸመው ሁሉ አሁን ለእኛ ተገብቶናል። እኛም ይህንን አጋጣሚ እንጠቀማለን። እኛ የእግዚአብሔር ልጅነት ድርሻችንን እንወጣለን።

"በእርሱ ዘንድ ያለን ድፍረት ይህ ነው እንደ ፈቃዱ አንዳች ብንጠይቅ ይሰማናል። የምንጠይቀውንም ሁሉ እንዲሰማልን ብናውቅ ከእርሱ የጠየቅነውን እንደተቀበልን እናውቃለን።" አንደኛ ዮሐንስ 5፥14-15።

## የአብ ፈቃድ ነው

ከቃሉ ጋር ኅብረት ያለው አማኝ ከአብ ፈቃድ ውጭ የሆነ አንዳችም ነገር በፍጹም አይጠይቅም። እኛ ስለዚህ ጉዳይ ምንም ነገር ልናስብ አይገባንም። እኛ የጠፉ ነፍሳትን ማዳን የእርሱ ፈቃድ መሆኑን እናውቃለን ኢየሱስ ስለዚህ ጉዳይ ሕይወቱን ሰጥቷልና። "በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና" ዮሐንስ 3፥16።

እኛ በሸተኞችን መፈወስ ፈቃዱ መሆኑን እናውቃለን ስለዚህም ምክንያት ክርስቶስ ድካማችንንና ሕመማችንን ተሸክሟል። "ለኃጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ በመገረፉ ቁስል ተፈወሳችሁ።" አንደኛ ጴጥሮስ 2፥24

እኛ የሚያስፈልገንን ለሚሟላት ስለ ገንዘብ ጉዳዮቻችን መጸለይ የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን እናውቃለን። "አምላኬም እንደ ባለጠግነቱ መጠን በክብር በክርስቶስ ኢየሱስ

የሚያስፈልጋችሁን ይሞላባችኋል።" ፊሊጵስዩስ 4፥19። ተግባራዊ በሆነ መልኩ ሁሉም ጉዳዮች በዚህ ተሸፍኗል። እኛ ለአገልጋዮች በመንፈስ ኃይል እንዲናገሩ እንጸልይላቸዋለን። ያልዳኑ ነፍሳት ላሉበት ምድር መጸለይ እንችላለን። ይህ ሁሉ በፍቃዱ ውስጥ አለ።

በምን ዓይነት ድፍረት በፊቱ እንቅረብ። ኢየሱስ ለአይሁዶች በማቴዎስ 21፥22 ላይ ሲናገር "አምናችሁም በጸሎት የምትጠይቁትን ሁሉ ትቀበላላችሁ አላቸው።" "ስለዚህ እላችኋለሁ የጸለያችሁትን የጠየቃችሁትንም ሁሉ እንዳገኛችሁት እመኑ ይሆንላችሁማል።" ማርቆስ 11፥24። እዚህ ላይ እምነት ወደ መገለጥ ያልመጣውን ወይም ያልተገለጠውን ቁስ ሆኖም ባለቤትነቱ የእርሱ እንደ ሆነ ስላወቀው ነገር እያመሰገነ ነው። "ለሚያምን ሁሉ ይቻላል።" ማርቆስ 9፥23። ከጌታ ጋር ለሚተባበር ከጌታ ጋር ኅብረት ለሚያደርግ ከጌታ ጋር አብሮ ሠራተኛ ለሆነ ሁሉ ነገር ይቻላል።

## ምእራፍ አስራ አራት

## ማመን የሚገባን ጥቂት ነገሮች

በቀድመችው ቤተ ክርስቲያን ክርስቲያኖች "አማኞች" ተብለው ተጠርተዋል። ኢየሱስ "ለሚያምን ሁሉ ይቻላል።" ሲል የግሪኩ ቃል "የሚያምን" የሚለውን "ከሚያምን አንዱ" ይለዋል። እርሱ "ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል።" አለ። ይህም ቃል የሚያምን አንዱ ማለት ነው። አማኝ ማለት ያለው የያዘ ባለቤት የሆነ ማለት ነው። ክርስቶስን የተቀበለ የዘላለምን ሕይወት ተቀብሏል በቤተሰቡ ውስጥም ስፍራውን ይዟል። በአእምሮው ብቻ የተስማማና የሚያውጅ ክርስቲያን በመንፈሱ ከዘላለም ሕይወት እውነታ ይጎድላል። እርሱም አንድ ቀን እንደሚያገኘው ያልማል ተስፋ በማድረግ ይጓጓል ነገር ግን አማኝ የሆነ ክርስቲያን ስለ ጉዳዩ አባቱን በሐሴት ያመሰግናል።

ማመን የሚለው ቃል ግስ ነው። እምነት የሚለው ቃል ደግሞ ስም ነው። ኢየሱስ የትኛውም ስፍራ ላይ ማመን የሚለውን ቃል ከተጠቀመ ያለው ወይም ባለቤት የሆነ ማለቱ ነው። "እውነት እውነት እላችኋለሁ በእኔ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው።" ዮሐንስ 6፥47። እዚህ ላይ ማመን የሚለው ቃል አለው ከሚለው ባለቤትነት ጋር እኩል ነው። ዛሬም ይህ ነገር እውነት ነው።

## ማመን የማይገባን ጥቂት ነገሮች

እኛ በውድቀት ማመን የለብንም። እኛ በፍጹም ውድቀትን ማሰብ ወይም ማውራት የለብንም ምክንያቱም እኛ አማኞች ነን። በአብ ጎሊና በአብ ዓይን አማኝ ሁሉ የተሳካለት ነው። አማኝ የሆነ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ ነው። እኛ በፍጹም እጦትን ወይም ነገሮችን ለመፈጸም አቅመቢስነትን ጨርሶ ማውራት የለብንም። እኛ ድክመትን በፍጹም ማንሳት የለብንም።

እኛ እግዚአብሔር የሕይወታችን ኃይል መሆኑንና የእግዚአብሔርን ብቃትና ችሎታ እንደ ተቀበልን እናስታውሳለን፡፡ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ኃይልን ከላይ እስኪቀበሉ ድረስ በኢየሩሳሌም እንዲቆዩ ነገራቸው፡፡ "ኃይል" የሚለው ቃል በግሪክ "ችሎታ ወይም ብቃት" ተብሎ ተተርጉሟል፡፡

ከዚያም የእግዚአብሔርን ብቃት ወይም ችሎታ እስኪቀበሉ ድረስ በኢየሩሳሌም መቆየት ነበረባቸው፡፡ እኛ ይህንን በዋናነት እንደሚገባ አልተጠቀምንበትም፡፡ በትክክል ሲገለጽም በጭራሽ አልሰማንም፡፡ ስለዚህ እኛ ጮክ ብለን "እግዚአብሔር ብቃቴ ወይም ችሎታዬ" ነው ለማለት ብዙም አልደፍርንም ሆኖም እውነቱ ልባችንን ማርኮ ይዞታል፡፡

እኛ ጌታ ያደረገውን ማንኛውንም ነገሮች የማድረግ ብቃት ወይም ችሎታ አለን፡፡ እኛ የማይፈቀሩትን ማፍቀርና ጥላቻ የተሞሉትንም ልክ ጌታ እንዳፈቀራቸው ማፍቀር እንችላለን፡፡ ክርስቶስ ጊዜው ሲደርስ ለደካሞችና ላልተገባቸውም ሞቷልና፡፡ እኛ ለደካሞችና ላልተገባቸው ልንኖር ብቃት ወይም ችሎታ አለን፡፡

እኛ ቃሉን ለማወቅ ብቃት ወይም ችሎታ አለን ምክንያቱም እግዚአብሔር ብቃታችን ነውና፡፡ የቃሉ ደራሲም እርሱ ራሱ እግዚአብሔር ነው፡፡ እኛ በፍጹም ጥላቻን ማውራት የለብንም ምክንያቱም ጥላቻ የጠላት ዲያብሎስ መለያ ነውና፡፡ እኛ እንዲህ ዓይነቱን ነገር ለማሰብ ለራሳችን መፍቀድ የለብንም፡፡ እኛ ለደቂቃም ቢሆን ስህተት ሊያሸንፍ እንደሚችል ወይም ኃጢአት ድል ሊያደርግ እንደሚችል ለመቀበል ለራሳችን መፍቀድ አይኖርብንም፡፡

እኛ የእግዚአብሔር ተወካዮች ነን፡፡ እኛ የኢየሱስን ስፍራ ወስደን የኢየሱስን ሥራ የምንሠራ ነን፡፡ እኛ የእርሱ ስም ከእነ ሙሉ ሥልጣኑ አለን፡፡ እርሱን ጥበባችን አድርገን ይዘነዋል፡፡ እኛ እርሱን የእኛ ብቃታችን ወይም ችሎታችን አድርገነዋል፡፡ እኛ ይህን በማወቃችን ብቻ ልዕለ ኃያል ነን፡፡

እርሱ እኛን እንዴት እንደሚመለከተን እንዴት እንደሚያስበን ብናውቅ በፍጹም መልሰን ስለ ድካም ውድቀትና እጦት አናወራም፡፡ እኛ በእግዚአብሔር መደብ ነን፡፡ እኛ የእርሱ ባሕሪ ተካፋዮች ነን፡፡ እኛ ኢየሱስ በአካል በሌለበት የእርሱን ስፍራ ተክተናል፡፡ እኛ ኢየሱስ የሠራውን ዓይነት ሥራ እየሠራን ነው፡፡ "በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል እኔ ወደ አብ እሄዳለሁና አብም ስለ ወልድ እንዲከበር በስሜ የምትጠይቁትን ሁሉ አደርገዋለሁ፡፡" (ዮሐንስ 14፥12-13)፡፡

እኛ ድካምና ውድቀት ከጨቆነው ከአሮጌው የስሜት ዓለም ወጥተን ወደ ስኬትና ድል አዲሱ ዓለም ገብተናል፡፡ እኛ ጽድቅ ወደ እግዚአብሔር ዙፋን ክፍል የመግባት ዕድል እንደ ሰጠን እናውቃለን እኛ እንደ ኢየሱስ ወደ ዙፋኑ ክፍል የመግባት መብት አለን፡፡ ይህ ጸሎትን አዲስ መሰረት ያስይዘዋል፡፡ እኛ አንለምንም አናለቅስም ነገር ግን እንደ ወንዶችና ሴት ልጆቹ ኃላፊነታችንን ይዘን የዓለምን ፍላጎት በፊቱ እናቀርባለን፡፡ ጸሎት

ልክ እንደ ባለ ሥልጣናት ጉባኤ ይሆናል። እኛ የተለየ ፍላጎትን ለመሙላት በሕጋዊ መንገድ በመጠየቅ ለመውሰድ እንገባለን።

ምእራፍ አስራ አምስት

መቀበል እንጂ መስጠት አይደለም

እኛ ለዓለም የተሳሳተ መልእክት ሰጥተናል። የእግዚአብሔር እውነት ዓለም ምንም ነገር እንዲተው የማይጠይቅ ሆኖ ሳለ እኛ ግን ለዓለም ያለን መልእክት "መስጠትና መተው" የሚል ሆነና ምን ማድረግ እንዳለባቸው ነገርናቸው። አንድ ሰው "እርሱ ኃጢአታቸውን እንዲተዉ አልጠየቀምን?" ሊል ይችላል። መልሱ ግን በፍጹም አልጠየቀም የሚል ነው።

"እርሱ በእርሱ ላይ ያላቸውን ክፋታቸውንና አመጸኝነታቸውን እንዲተዉ አልጠየቀምን?" ሊባል ይቻላል ነገር ግን መልሱ አሁንም አልጠየቀም ነው። ጉዳዩ የመቀነስ አይደለም የመጨመር እንጂ። ጉዳዩ የመውሰድ ሳይሆን የመጨመር ጉዳይ ነው። ሰጪ እግዚአብሔር ነው። እኛ ደግሞ ተቀባዮች ነን። "አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።" ዮሐንስ 3፣16

እርሱ ሰብአዊ ፍጡር አንዳችም ነገር እንዲተው አልጠየቀም። እርሱ ድህነታችንን አይቷል። እርሱ እኛ ልንሰጠው የምንችለው ለእርሱ ምንም ጥቅም የሌለውን ነገሮች ብቻ እንደሆነ ተመልክቷል። ሰጪ እግዚአብሔር ነው። እርሱ ልዑል ንጉስ እንደሚሰጥ መስጠት ይችላል። እርሱ ምንም ነገር እንድንተው ወይም እንድንጥል አልጠየቀንም። እርሱ የጠየቀን ነገር ቢኖር አንድ ነገር እንድንቀበል ነው።

የሰጠን የመጀመሪያው ነገርም ከእጦት ከውድቀት ከድካም ከበሽታና ደዌ ፍርሃት መዋጀትን ነው። እርሱ ከእነዚህ ነገሮች ሁሉ መዋጀትን ሰጥቶናል። ይህ የሚታመን ወይም የሚቻል አይመስልም ይሁን እንጂ እውነት ነው። እርሱ ከጠላት ግዛትና ሥራ መዋጀትን ሰጥቶናል። ይህንን ማሰላሰል እንዴት ልብን ያስፈነጥዝ!! ቆላስያስ 1፣13-14 አስደናቂውን እውነት ይሰጠናል "እርሱ ከጨለማ ሥልጣን አዳነን ቤዛነቱንም እርሱንም የኃጢአትን ስርየት ወዳገኘንበት ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግስት አፈለሰን።"

በጥንቃቄ እናስተውል። እርሱ እኛን አንዳች አልጠየቀንም። እርሱ በገዛ ፈቃዱ በራሱ ወጪ መጥቶ ከጨለማ ሥልጣን ድካም ድንቁርናና ውድቀት ተቤዠንና መልካም የምስራች የሆነውን መዋጀታችንን ሊነግረን መገለጥን ላከልን። በፍጹም መልካም ከሆንንና ኃጢአቶቻችንን ከተውን አርነት እንደምንወጣ ሊነግረን አልላከም። እኛ ከጨለማው ሥልጣን አርነት ወጥተናል። "ጨለማ" በሚለው ቃል ውስጥ ሰይጣናዊ ጥላቻ ምሬትና ቅንአት አጠቃላይ የእስራት ስርአት አለ። ሰይጣን የሆነው ነገሮች ሁሉ "ጨለማ" በሚለው ቃል ውስጥ ተጠቃለለው አሉ። ድንቁርና አለ። እንባዎች አሉ።

ረሃብ አለ። እጦት አለ። እጥረት አለ። በሽታ ሕመምና ስቃይ አለ። ነገር ግን እኛ ከጨለማ ሥልጣን ከሰይጣን ጭቆና ነጻ ባደረገን በኢየሱስ ከዚህ ወጥተናል።

እርሱ ነጻ ብቻ አላወጣንም ነገር ግን ቤዛነትንም እርሱንም የኃጢአትን ስርየት ወዳገኘንበት ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግሥት አፍልሶናል። በዚህ ዓይነት ፍቅር እንዴት አድርጎ ልባችንን ማረከው። እንድንሰብክ ያስተማሩን ግን ይህንን መልእክት አይደለም። ያስተማሩን የዚህን ተገላቢጦሽ ነው። እርሱ እኛ ወደ ዓለም ሄደን ኃጢአተኛን አንድንወግርና ምን መተው እንዳለበትና እንደሌለበት ምንን አሳልፎ መስጠት እንዳለበት እንደሌለበት እንድንነግር የተናገረበት አንድም ስፍራ የለም። አንድ ሰው ክርስቶስን እንደ አዳኙ ከተቀበለ ያ ንስሃ ነው። በልቡ እርሱን እንደ ራሱ ጌታ አድረጎ ከተናዘዘ ያ ማመን ነው። እርሱ ይህንን ድንቅ ቤዛነት እንድንቀበል ብቻ አልጠየቀንም ነገር ግን የጠየቀን ኢየሱስን እንደ ጌታ አድርገን እንድንቀበል ጭምር ነው።

ይህም ልክ ሞአባዊቷ ሩት ቦኤዝን ባሏ አድርጋ እንደተቀበለችው ማለት ነው። ቦኤዝን መቀበል የድህነትና እጦት ማብቂያ የስጋትና ፍርሃት ግርፊያ ማብቂያ የርሃብና የችግር ማብቂያ ማለት ነው። እርሷ በኮረብታው ላይ የሚገኘው ትልቅ ቤት አስተዳዳሪ ሆነች። እነዚያ የወይራ የሮማን የኮክና የብርቱካን አትክልት ስፍራዎች እነዚያ ሰፋፊ የስንዴ ማሳዎች የራሷ ሆኑ።

እርሷ ድህነቷን አልጣለችም። የእርሱን ብልጽግና ተቀበለች እንጂ። እርሷ ብቸኝነቷን አልጣለችም። የእርሱን ጎብረት ተቀበለች እንጂ። እርሷ ድካሟን፤ ስጋቷንና ፍርሃቷን አልጣለችም። የእርሱን መትረፍረፍ ከለላና ጥበቃ ተቀበለች እንጂ።

እግዚአብሔር ወደ እኛ መጣ። እርሱም ኢየሱስን እንደ ጌታችን አድርገን እንድንቀበል ጠየቀንና በሃሴት ለዓለም የድካምና የውድቀት ማብቂያ ላይ እንደ ደረስን እኛም የእርሱን ኃይል ሙላት ችሎታና ብቃት እንዳገኘን ነገረን። "ጌታ" የሚለው ቃል የእንጀራ አቅርቦትነት ትርጉምም አለው። እርሱ የእኛ እንጀራ አቅርቦት ነው። እርሱ የእኛ ኃይል አቅርቦት ነው። እርሱ የእኛ ብቃት አቅርቦት ነው።

"እኛ ሁላችን ከሙላቱ ተቀብለን በጸጋ ላይ ጸጋ ተሰጥቶናልና።" ዮሐንስ ፩፥16። እኛ ተቀባዮች ነን። እኛ ከዚህ ወዲያ እርሱ መጥቶ እንዲባርከን እያለቀስን የምንለምን አይደለንም። እኛ በሰማያዊ ስፍራ በማንኛውም መንፈሳዊ በረከቶች ተባርከናልና። እኛ በእርሱ ባለጠግነት ባለጠጎች ነን። እኛ በእርሱ ሙላት ሙሉ ነን። እኛ በእርሱ ረክተናል። እርሱ ስለ እኛ በትንሳኤ የተነሣ የእኛ ጌታ ነው።

እርሱ የራሱ ባሕሪ የሆነውን የዘላለም ሕይወት እንድንቀበል ጠየቀን። ይህም እኛን አዲስ ፍጥረት አድርጎናል። እኛ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጥረናል። የአሮጌው ሥርአት ውጤት የነበሩት ውድቀት ድካምና ኃጢአት አልፈዋል እነሆ ሁሉ ነገር አዲስ ሆኖአል። ይህም ሁሉ የሆነው ከራሱ ጋር በክርስቶስ ካስታረቀን ከእግዚአብሔር ነው።

እኛ ራሳችንን ከእርሱ ጋር አላስታረቅንም፡፡ እኛ ስለ እርቁ አንዳች አስተዋጽኦ የለንም፡፡ እኛ ከመቀበል በቀር ስለ አዲስ ፍጥረትነትም ምንም አስተዋጽኦ የለንም፡፡ ሁሉም ከእግዚአብሔር ነው፡፡ እኛ ልንረዳው አንችልም፡፡ ከእኛ የመረዳት አቅም በላይ ነው፡፡ ይህ ያለው በመንፈሳዊ ዓለም ውስጥ እርሱም በጸጋው ባለጠግነት ክብር ዓለም ውስጥ ነው፡፡ አዲስ ፍጥረትነት የኃያሉ እግዚአብሔር ልጆች አድርጎናል፡፡ አሁን እግዚአብሔር አባታችን ነው፡፡ እኛም ልጆቹ ነን እኛ በእርሱ ቤተሰብ ውስጥ ነን፡፡

አስደናቂነቱ! ጸጋው! ሃሴቱ! እንዴት ያጽናናል ያበረታታል፡፡ ቤዛነቱን ስንቀበል እኛ ከአሮጌው እስራትና ልማድ ተፈትተናል፡፡ የእርሱን ጌትነት ስንቀበልና ለዓለም በሃሴት ስንናገር መዋጀትን ተቀብለናል፡፡ የዘላለም ሕይወት ከእርሱ ጋር አያያዘን፡፡ ስለዚህም ጉዳይ ቢሆን እኛ አልጠየቅነውም፡፡ እኛ እርሱ ይህን ከሰጠን የተወሰኑ ነገሮች ለማድረግ ቃል ገብተን አልለመንም አልጠየቅንም ወይም አልጸለይንም፡፡ ማድረግ የተገባን ነገር ቢኖር ስጦታውን እውቅና መስጠትና ስለ ስጦታው እርሱን ማመስገን ነው፡

"ነገር ግን" እናንተ "ስላደረግናቸው ኃጢአቶቻችንስ?" ትላላችሁ አይደል፡፡ ኃጢአቶቻችንንማ እርሱ በራሱ መስዋእትነት አስወገደው፡፡ ይህንንም ለማድረግ እኛ አንዳች አስተዋጽኦ የለንም፡፡ እኛ ለዘመናት ረዳት አልባ ሆነን በኃጢአት ሰእስራት ስር ነበርን ከዚያ አንድ ቀን አንድ ሰው መጥቶ "እርሱ ራሱ መስዋእት ሆኖ የአንተን ኃጢአት እንዳስወገደልህ አውቀሃልን?" አለን፡፡ እኛም "አዎን አንብበናል ነገር ግን አልተረዳነውም፡፡" አልን፡፡ እኛን ለጠላት እስረኛ ያደረገንና ኩነኔ ያመጣብን ተወግዷል፡፡ ስለዚህ የእኛ ልብ በሃሴት ተሞላ፡፡

"እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ፡፡" አንደኛ ጴጥሮስ 2፥24፡፡ እኛ በእርሱ ጽድቅ ጽድቅ እንሆን ዘንድ እርሱ በእኛ ኃጢአት ምክንያት ስለ እኛ ኃጢአት ሆነ፡፡ ከዚህ በኋላ እኛን ኃጢአት አይገዛንም፡፡ "እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን ከእኛ እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ" ስለዚህ አብ ሁላችን የሆንነውንና የፈጸምነውን ሁሉ በክርስቶስ ላይ አኖረ፡፡ (ኢሳይያስ 53፥6)

ዮሐንስ መጥምቁ "እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር ጠቦት" አለ፡፡ ዮሐንስ 1፥29፡፡ እግዚአብሔር የኃጢአትን ችግር ፍጻሜ አበጅቶለታል፡፡ እርሱ ኃጢአተኛነታችንን እኛ እንድናስወግድ አልጠየቀንም፡፡ ስለዚህ ጉዳይ አንዳች እንድናደርግ አልጠየቀንም፡፡ ሌላው ቀርቶ እኛ ኃጢአተኞች ስለ ነበርን እንድናዝን አልጠየቀንም፡፡

ለምን? ኃጢአተኛ ሆነን ለመገኘታችን መወንጀል ያለብን አኛ ስላልሆንን ነው፡፡ ሰው ስለ ተወለደበት አንድ አገር ሊወነጀል ይገባዋልን? ከእርሱ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም፡፡ እኛ ከኃጢአት ሁኔታዎቻችን ጋር ምንም ግንኙነት የለንም፡፡ ሌላው ቀርቶ የፈጸምናቸውን ኃጢአቶች ላለመፈጸም አንችልም ነበር፡፡ እነርሱ ምንም የማያስፈልጋቸው የኃጢአት ተፈጥሮአዊ ባሕሪያችን ሁኔታ እድገቶች ናቸው፡፡

አሁን እርሱ መጣና ያንን ኃጢአት እንዳስወገደው ነገረን፡፡ እርሱ የሰራናቸውን ኃጢአቶች ሁሉ እንደ ደመሰሰው ነገረን፡፡ እርሱ አንዳች ነገር እንድናደርግ በጭራሽ አልጠየቀንም፡፡ ሁሉም በጸጋ ነው፡፡ እርሱ "ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም፡፡ እኛ ፍጥረቱ ነንና እንመላለስበት ዘንድ መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን፡፡" ኤፌሶን 2፥8-10፡፡

አዲስ ፍጥረትነት በአብ ጎሊና እውን የሆነው መቼ ነበር? ኢየሱስ ከሞት ሲነሳ ነው፡፡ እኛስ የጸደቅነውና ጽድቅ ተብለን የተጠራነው መቼ ነበር? እርሱ ከሙታን ተለይቶ በትንሳኤ በተነሳና  በሰማያት በግርማው ቀኝ በተቀመጠ ጊዜ ነበር፡፡ ስለሆነም እርሱ አንዳች ነገር እንድናደርግ አልጠየቀንም እንድንቀበል ብቻ እንጂ፡፡

እኛ ስለመዋጀታችን ልንከፍለው ከፈለግን ጉዳዩ በሥራ እንጂ በጸጋ አልሆነም ማለት ነው፡፡ "ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም፡፡" ልጅነት ስጦታ ነው፡፡ መዋጀት ስጦታ ነው፡፡ የዘላለም ሕይወት ስጦታ ነው፡፡ አዲስ ፍጥረትነት ስጦታ ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ ስጦታ ነው፡፡ እግዚአብሔር ስለ ወደደ ልጁን ሰጠ፡፡ ኢየሱስ ስጦታ ነው፡፡ አብ ወይም አባት ስጦታ ነው፡፡ ስለዚህ እኛ ስጦታን  እንቀበላለን እንጂ ለስጦታ አንከፍልም፡፡

ምእራፍ አስራ ስድስት

በስሜት የሚገዛ አእምሮ

(ሮሜ 12፥1-2)

በስሜት የሚመራ አእምሮ በፍጹም ድል ነሺ የመገለጥ እምነትን አንደማያገኝ የተገነዘብን ጥቂቶች ብቻ ነን፡፡ በቃሉ ላይ ያለ እምነት ኃይል የሚኖረው አእምሮ ቃሉን ሲለማመድና ያንንም ተግባራዊ ሲያደርግ ብቻ ነው፡፡ የአእምሮ መታደስ በየትኛውም ቀውስ ውስጥ በቃሉ ላይ በመቆም እለት እለትም ቃሉ በሕይወታችን ተግቢውን ስፍራ እንዲይዝ በመልቀቅ ይመጣል፡፡ አማኝ በአእምሮ መንፈስ እስካልታደሰ ድረስ በሙላት በሕያው ቃሉ ሃሴትን ሊያደርግ አይችልም፡፡

በመንፈስ ያልታደስ አእምሮ ደግሞ የፍጥረታዊ ሰውን ቃል መመገብ ይመርጣል፡፡ በሰዎች ቃል ላይ የሚቆመውን ምክራቸውን ተግባራዊ የሚያደርገውን ያህል በእግዚአብሔር ቃል ላይ አይቆምም፡፡ ሰዎች ዶክተሩ ምን እንዳላቸው ይነግሯችሁና የእርሱን ቃል ተግባራዊ ያደርጋሉ ወይም በዶክተሩ ቃል ላይ ይቆማሉ፡፡ እኔ ግን ሁልጊዜ እግዚአብሔር ያለውን እነግራቸዋለሁ እነርሱ ደግሞ ራሳቸውን በመነቅነቅ "አይ እኛ ይህን ተግባራዊ ልናደርግ ወይም በእዚህ ላይ ልንቆም አንችልም፡፡" ይላሉ፡፡

በስሜት የሚመራ አእምሮ ሁልጊዜ ከጥርጣሬ ጋር ጦርነት ይገጥማል፡፡ በስሜት የሚመራ አእምሮ በፍርሃትና በመዋዠቅ ዓለም ውስጥ ይኖራል፡፡ ለእርሱ የእግዚአብሔር ቃል የመጨረሻ ወሳኝ ማሳረጊያ አልሆነም፡፡ ስለዚህ ቃሉ በእርሱ ዘንድ ለየትኛውም ጉዳይ መፍትሄ አይደለም፡፡ ስለሆነም በተደጋጋሚ ተሸናፊ የሚሆንበት ውጊያ ውስጥ ይመላለሳል፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ከቃሉ ይልቅ አእምሮው የሚመራው በስሜት መሆኑ ነው፡፡ በስሜት የሚመራ አእምሮ ደግሞ በጥርጣሬ ዓለም ውስጥ ከመኖር ውጭ ሊሆን አይችልም፡፡

ቃሉ የጌትነቱን ስፍራ እስኪወስድ ድረስ በዚህ የመገለጥ አውቀት ከመመላለስ ይልቅ በስሜት በሚያያቸውና በሚሰማቸው ነገሮች ይወሰዳል ይዋዥቃል፡፡ በስሜት የሚመሩ ሰዎች ቃሉን በሚያነብቡበት ጊዜ እውነት ስለ መሆኑ ያውጃሉ ነገር ግን በቀጣዩ እስትንፋሳቸው የስሜት እውቀት እፎይታን ይናገራሉ፡፡ በስሜት እውቀት የሚመራ የታመመ ግለሰብ ቃሉ ፍጹም እውነት ለመሆኑ ያውጅና ከዚያ በመቀጠል ወደ ሌላ መፍትሔ ይዞራል፡፡ በስሜት የሚመራ አእምሮ በቃሉ መፍትሔነት ላይ ተደላድሎ በጸጥታ አያርፍም፡፡

እርሱ ሁለት አሳብ አለው ወይም በሁለት አሳብ ያነክሳል፡፡ እርሱ የእግዚአብሔር ቃል እውነት ነው ብሎ ስለ ቃሉ ፍጹም ታማኝነት ለመሟገትም ፈቃደኛ ነው ይሁን እንጂ በእለታዊ ድርጊቱ በተከታታይ ይክደዋል፡፡ ሐዋርያው ያዕቆብ እንዲህ ዓይነቶቹን "እምነትን" የሚያወሩና "ስሜታዊ ምክንያትን" ተግባራዊ የሚያደርጉ ሰዎችን ሁለት አሳብ ያላቸው ወገኖች ሲል ይጠራቸዋል፡፡

እነዚህ ወገኖች ከ"ስሜት ምክንያታዊ" ተግባር የ"እምነት" ውጤትን ይጠብቃሉ፡፡ ሁለት አሳብ ያላቸው ምንጊዜም ዋጥቂዎች ናቸው፡፡ እነርሱ በእምነትና በስሜታዊ ምክንያታዊነት ወሰን መካከል ባለው ስፍራ ይኖራሉ፡፡ የእነርሱ ቤት በእነዚህ ሁለት ዓለሞች መካከል ተገንብቷል፡፡ እነርሱ በሁለቱ መንግሥታት መካከል ዜግነትን ለማግኘት የሚፈልጉ ናቸው፡፡ እምነት ግን በእግዚአብሔር ቃል ላይ ብቻ ተመስርቶ የሚገለጥ ነው፡፡

## ምእራፍ አስራ ሰባት

## አዲሱ ትእዛዛትና ጽድቅ

ቤተ ክርስቲያንን የሚገዛት የሕይወት መንፈስ ሕግ አስርቱ ትእዛዛትን የተካው የሕይወት መንፈስ ሕግ የሰብአዊ ፍጡራንን ሕግ የበላይ ሆኖ የሚገዛው መንፈሳዊ ሕግ የሕይወት መንፈስ የሆነው የፍቅር ሕግ ነው፡፡ አንድ ሰው በኢየሱስ ዓይነት ፍቅር ከተመላለሰ ኃጢአትን ሊሰብ የሚችል ምንም ዓይነት ሕግን ሊተላለፍ አይችልም፡፡

አንድ ሰው በፍቅር ከተመላለሰ እርሱ በርግጠኝነት በእግዚአብሔር እየተመላለሰ ነው ምክንያቱም እግዚአብሔር ፍቅር ነውና፡፡ አንድ ሰው በፍቅር ከተመላለሰ እርሱ

አሉታዊነቱ ወይም ገለልተኛነቱ አለያም መሐል ሰፋሪነቱ አብቅቷል። ስለሆነም እርሱ ለዓለም አዎንታዊ የበረከት መሰረት ሆኗል። ሆኖም አንድ ሰው አንዲት ርምጃ ከፍቅር ሕግ ፈቀቅ ሲል ከእግዚአብሔር ንፍቀ ክበብ ወጥቶ ወደ ጠላት ንፍቀ ክበብ ይራመዳል።

አንድ ሰው ከፍቅር ውጪ ሲመላለስ በተግባር ከጠላት ጋር እየተባበረ ነውና ራሱን መከላከል ወደ ማይችልበት ስፍራ እየወሰደ ነው። ጠላትም የበላይነቱን ይይዛል። በፍቅር እስከ ተመላለሰ ጊዜ ድረስ ግን ሰይጣን በአርሱ ላይ አንዳች የለውም። አንድ ሰው ከፍቅር ውጪ ሲመላለስ በውስጡ ያለውን የእምነት ንጥረ ነገር ያዳክማል። እኛ ከፍቅር ውጪ በእምነት ልንመላለስ አንችልም። እኛ ከፍቅር ሕይወት ውጪ እየኖርን የእምነት ሕይወት ልንኖር አንችልም።

እኔ ይህንን በራሴ መንፈስ ውስጥ ጥርት እንዲል ለማድረግ ረጅም ጊዜ ወስዶብኛል ነገር ግን አሁን አውቄዋለሁ። ያለመጨናነቅ የሆነው እምነታችን በምናደርገው የፍቅር ጉዞ ይመዘናል። እኛ እምነታችንን ሳናዳክም ከፍቅር ውጪ ልንናገር ከፍቅር ውጪም ተግባራዊ ልንሆን አንችልም። አንደኛ ቆሮንቶስ 13 ፍቅር "የራሱንም አይፈልግም" ይላል። በአብ ላይ የሆነ እምነትና ራስ ወዳድነት አይቀላቀሉም። እኛ በእምነት ስንመላለስ እኛ ከሁኔታዎች በላይ እንሆናለን። እኛ በፍቅር ስንኖር በአብ ወይም በአባታችን ጥበቃ ዓለም ውስጥ በመሆን በእርሱ ጥበብ እንመላለሳለን።

አባታችን ፍቅርና ብርሃን ነው። እርሱ ኢየሱስን ለእኛ ጥበባችን አድርጎታል። እኛ ከእርሱ ጋር በኅብረት ስንመላለስ ጥበብ አለን ደግሞም የእርሱ ብቃት አለን። ውኃ ለዓሣ መኖር ተፈጥሮአዊ ባሕሪ እንደ ሆነለት ሁሉ እምነትም የእኛ ባሕሪ ይሆናል። እርሱ የማንነታችን አንዱ ክፍል ነው። እግዚአብሔር የእኛ ኃይል የእኛ ሕይወት የእኛ ብቃት ነው።

## በደዌና በበሽታ ሕልውና ውስጥ የጽድቅ ተጽእኖ

እኛ ኢየሱስ ስለ ምን በሰይጣን ሥራዎችና አቋም ፊት ፈጽሞ ደፋር ሊሆን እንደ ቻለ እንገረማለን። እርሱ በአልአዛር መቃብር በሞት ፊት በድፍረት በመታመን ሆኖ እናየዋለን ይህም እኛን ያስፈነጥዘናል። ይህ የሆነው ስለምንድን ነው? ምክንያቱ እርሱ ጻድቅ ስለ ነበር ነው። ኃጢአት ሰዎችን ፈሪ ያደርጋቸዋል። በኅሊናችን ውስጥ የተቀመጠ የኃጢአት እውቅና ወይም ኩነኔ እኛን አስሮ ይይዘናል።

እኛ ከእግዚአብሔር እንደ ሆንን እናውቃለን ከዚያም በላይ እግዚአብሔር በእኛ ውስጥ እንዳለ እናውቃለን። ስለዚህ እኛም ልክ እንደ ኢየሱስ በሰይጣን ሥራና አቋም ፊት በድፍረት መቆም እንችላለን። የእኛን "ሁለቱ የጽድቅ ዓይነቶች" የተሰኘውን መጽሐፍ ያንብቡ። በእውነት ጽድቅ እኮ እግዚአብሔር እኛን የራሱ አድርጎ የወሰደበት ብቃት ነው። እኛ አዲስ ፍጥረት መሆናችንን ከማወቃችን የተነሳ በእርሱ ሕልውና ፊት ያለ ምንም ፍርሃት መቆም እንችላለን። እኛኮ ዳግም የተፈጠርነው በእግዚአብሔር በራሱ ነው ደግሞም ኢየሱስ በስሙ የመጠቀም ሙሉ ውክልና ሰጥቶናል።

እርሱ "በስሜ አጋንንትን ታወጣላችሁ::" አለ:: እኛ አጋንንትን ማውጣት ከቻልን ሰይጣን የሠራውን ሁሉ መደምሰስ እንችላለን ማለት ነው:: እኛ ሰይጣን ጉብ ባለበት በየትኛውም ቦታ ኃይሉን መስበር እንችላለን:: እኛ የሰይጣንን ምሽግ ያለምንም ፍርሃት ማፈራረስና መደምሰስ እንችላለን ይህ የእርሱ መደምሰስ ደግሞ ለእኛ ድላችን ነው:: እንግዲህ አሁን ሰይጣን እንደተሸነፈ አውቀናልና እኛ ባርያ በነበርንበት ስፍራ ጌቶች ሆነናል:: እኛ ደካሞች በነበርንበት ክልል ኃያላን ሆነናል::

እኛ ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ስለሆንን ያለፍራቻ በእርሱ ስፍራ ሆነን ልክ ኢየሱስ በምድር ላይ በሥጋ በነበረ ጊዜ እንዳደረገው ማድረግ እንችላለን:: ከጌታ አንደበት "እውነት እውነት እላችኋለሁ በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል እኔ ወደ አብ እሄዳለሁና አብም ስለ ወልድ እንዲከበር በስሜ የምትጠይቁትን ሁሉ አደርገዋለሁ:: ማናቸውንም ነገር በስሜ ብትጠይቁ እኔ አደርገዋለሁ::" በማለት ያወጣው ቃል ትርጉም የለሽ አልነበረም::

እኛ ይህ ጸሎት እንዳልሆነ አብን ማናገር እንዳልሆነ ሆኖም አጋንንትን ማናገር እንደሆነ አውቀናል:: እኛ ፍርሐት የለሽ ድፍረት ተላብሰን ጠላትን ማሸነፍ እንችላለን:: ኢየሱስ "ከእርሱ ውጣ::" ብሏልና:: ስለዚህ እኛም "በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ከእርሱ ውጣ:: ወደ ተገባህ ወደ ጥልቁ ስፍራ ግባ ፈጽመህም ተመልሰህ እንዳትመጣ እንደገናም ይህንን ሰው እንዳታስጨንቀው::" እንላለን::

እኛ ከእርሱ በተካፈልነው ጽድቅ በእርሱ ፋንታ እርሱን ተክተን እየሠራን ነው:: እኛ ከኢየሱስ የተካፈልነው ጽድቅ በእርሱ ፋንታ እርሱን ተክተን እንድንሠራ ብቃትን ሰጥቶናል:: ይህ ለመለኮታዊ ሕይወት አዲስ ቀን ነው:: ይህ በሰዎች ግዛት ውስጥ አዲስ ሥርዓት ነው:: ሰይጣን ባለፈው አሮጌ ሥርዓት ነግሶ ነበር:: እኛንም የኃጢአት ኩነኔ ጨቁኖን ነበር::

እኛ አዲሱ ፍጥረት የእግዚአብሔር ጽድቅ መሆኑን ወደ ማወቅ መጥተናል:: እኛ ይህ ጽድቅ ስነ መለኮታዊ ትንታኔ ወይም ፍልስፍና እንዳልሆነ ነገር ግን እውነተኛ ጽድቅ እንደ ሆነ አውቀናል:: ሆኖም የእኛን የኃጢአተኝነት ኅሊናዊ እውቅና ወይም ኩነኔን ወደ ጽድቅ ኅሊናዊ እውቅና የለወጠው እግዚአብሔር ነው::

እኛ በውስጣዊ አስተሳሰባችን እግዚአብሔርን እስክንመስል ድረስና በሥራችን ረቂቅና ልበ ሙሉ እንድንሆን ቃሉን በውስጣችን እየገነባና እየሠራ ያለው እግዚአብሔር ነው:: እኛ ድንጉጥና ፈሪ መሆናችን አልፏል:: እኛ በተሸነፈው ጠላት ፊት እንደ እግዚአብሔር ልጅነታችን እንቆማለን::

በአንደኛ ቆሮንቶስ 2፥6 ላይ ስለ ተሻሩ የዓለም ገዢዎች ይናገራል:: እኛ እነርሱ እንደ ተሻሩ ተገንዝበናል:: እኛ ደግሞ እንደ ነገስን ተረድተናል:: እግዚአብሔር ደግሞ በእኛ

ውስጥ ነግሷል፡፡ እኛ የሰውን ዘር ያጠፉ በነበሩ የጨለማ ኃይላት ላይ ጌቶች ሆነናል፡፡ እኛ ተገቢ ስፍራችንን ይዘን ድርሻችንን እንጫወታለን፡፡

## ጽድቅ ከእምነት ጋር ያለው ግንኙነት

እምነት ከአባት ጋር ካለን ቀጣይ ኅብረት ውስጥ ያድጋል፡፡ ጽድቅ በአብ ሕልውና ፊት ከጥፋተኝነትና የበታችነት ስሜት ነጻ ሆኖ የመቆም ብቃት ነው፡፡ የተፈጸመ የክርስቶስ ሥራ ውጤትና በአዲስ ፍጥረትነት የተደመደመ ጉዳይ ነው፡፡

አብ የማይወድደውን ነገሮቻችንን ሁሉ ወስዶ የራሱን ሕይወትና ባሕሪ በስፍራው በመተካት በራሱ ባሕሪ እንደገና እንደፈጠረን ስናውቅና እርሱ የራሱ መኖሪያ ወይም ማደሪያ ሊያደርገው በመቻሉ በአዲስ ፍጥረት እንደረካ ደግሞም እርሱ በእኛ ውስጥ እንዳደረ ስንረዳ እኛ ለእርሱ ምን ያህል እጅግ ውድ እንደሆንንና ሊገመት የማይችል ዋጋ እንዳለን ተገንዝበናል ማለት ነው፡፡

እርሱ ወንዶችና ሴቶች ልጆች ካሉትና ከእነርሱም ጋር በእኩልነት ላይ በተመሰረተ መልኩ ኅብረት ማድረግ የማይችል ከሆነ በእዚህ ውስጥ ምንም ዓይነት እርካታ የሚባል ነገር የለም በክርስቶስም ያስተካከለው ነገር በሙሉ ፉርሽ ሆኗል ማለት ነው፡፡

እኛ መጀመሪያ ላይ ሰው ከአብ ጋር ፍጹም የሆነ ኅብረት እንደ ነበረው እርግጠኞች ነን ሰው በኃጢአት ምክንያት በወደቀ ጊዜ ግን ያ ኅብረት ተቋረጠ፡፡ ስለሆነም ፍጹም የሆነ መዋጀት ያንን የጠፋውን ኅብረት የግድ ማደስ አለበት፡፡ ጉዳዩም የግዴታ በሕጋዊ መሰረት መታደስ መቻል አለበት፡፡ ስለዚህ የተዋጀ ሰው በአባቱ ሕልውና ፊት ፍጹም የሆነ መብት እንዳለው ማወቅ አለበት፡፡ እግዚአብሔር ፍጹም የሆነ የፍቅር ሕይወት ለመገንባት መሰረት መጣል አለበት፡፡ ከዚህ ፍጹም ከሆነ የፍቅር ሕይወት ውስጥ የእምነት ሕይወት ያድጋል፡፡

እምነት በፍቅር ይሠራል፡፡ እምነትና ፍቅር የማይነጣጠሉ ናቸው፡፡ ፍቅር እምነትን ወለደ እምነትም ደግሞ ለፍቅር ብርታት ሰጠው፡፡ አንድ ሰው እግዚአብሔር ዳግም እንደ ፈጠረውና አዲስ ፍጥረት እንዳደረገው ይህም አዲስ ፍጥረትነት የአብ ባሕሪ ተካፋይነት እንደ ሆነ ሲያውቅ ያን ጊዜ ጤናማ ስፍራው በአብ ሕልውና ውስጥ መሆኑን አወቀ ማለት ነው፡፡ ኢየሱስ "እኔ የወይን ግንድ ነኝ እናንተም ቅርንጫፎቼ ናችሁ፡፡" አለ፡፡ ይህ ምሳሌም አንድ ሰው ቅርንጫፉና የወይኑ ግንድ ፍጹም አንድ እንደ ሆኑ እንዲረዳ ግድ ይለዋል፡፡

ይህ በአማኙ ውስጥ እምነትን ይገነባል፡፡ እኛም ያለማቋረጥ በክርስቶስ የእግዚአብሔር ጽድቅ መሆናችንን እናስረግጣለን፡፡ እኛ ይህ እውነታ የጎሊናችን አንዱ ክፍል እስኪሆን ድረስ ደግመን ደጋግመን እንናገረው፡፡ እኛ አራትና አራት ስምንት መሆኑን ወይም እሳት

ሙቀትን እንደሚሰጥ ወይም ፀሐይ ደግሞ ብርሃን እንደምትለግስ የምናውቀውን ያህል በጎሊናችን ንቁ እንሆናለን፡፡

እኛ እግዚአብሔር ያለንን ያንኑ እንደ ሆንን አውቀናል፡፡ እኛ እርሱ ያደረገንን ለመሆን አንጥርም አንሞክርም፡፡ እኛ በክርስቶስ ውስጥ የሆነውን ሐብትና ብልጽግና እንደሰትበታለን፡፡ እግዚአብሔር በኢየሱስ ለሚያምን ሰው እርሱ ራሱ ጽድቁ እንደ ሆነ ስለ ተናገረ እኛም ኢየሱስ አዳኝና ጌታ በመሆኑ ላይ እምነት ስላለን እግዚአብሔር የእኛ ጽድቅ እንደ ሆነልን አውቀናል፡፡

እኛም የእርሱ ጽድቅ እንደ ሆንን አውቀናል፡፡ ሰው ሰው ለመሆን እንደማይጥር ሁሉ እኛም ጽድቅ ለመሆን አንሞክርም አንጥርም፡፡ ምናልባት እርሱ ጥሩ ሰው ለመሆን ይሞክር ይጥር ይሆናል ነገር ግን ምንም ይሁን ምንም እርሱ ተፈጥሮ ያደረገውን ያንኑ ነው፡፡ እኛም እግዚአብሔር የእርሱ ጽድቅ እንዳደረገን ያንኑ ነን፡፡

መንፈስ ቅዱስ በጳውሎስ በኩል እግዚአብሔር ኢየሱስን የእኛ ጥበብ እንዳደረገው ተናገረ፡፡ ስለዚህ እኛ ኢየሱስ ጥበባችን መሆኑን አውቀናል፡፡ እርሱ ማለትም ኢየሱስ ቅድስናችን እንደ ሆነ ሲናገር እኛ በእርሱ ቅድስና እንደ ተቀደስን ተረድተናል፡፡ ኢየሱስ የእኛ ቤዛና መዋጀት እንደ ሆነ ሲያውጅ እኛ እንደ ተዋጀን እርሱም የእኛ ተቤዢያችን እንደ ሆነ ተገንዝበናል፡፡

ይህን ተከትሎ መዋጀታችን እውን ሆኗል፡፡ በተመሳሳይ መንገድ እርሱ የእኛ ጽድቅ መሆኑን አውጇል፡፡ እርሱ የእኛ ጽድቅ ከሆነ እንግዲያውስ ልክ እንደ እርሱ በአብ ፊት የመቆም መብታችን እኩልና አንድ ዓይነት ነው፡፡ ይህም በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ላለን እምነት እውነተኛ መነሻ ነው፡፡ የማርቆስ ፲፩፥22 (አውቶራይዝድ እትም) "የእግዚአብሔር እምነት ይኑራችሁ" ሲል (ሪቫይዝድ ትርጉም) ደግሞ "በእግዚአብሔር እመኑ" ይላል፡፡ እኛ ግን ሁለቱም አለን፡፡

እኛ በውስጣችን ከመለኮታዊ ባሕሪው የተካፈልነው በቃሉ አማካኝነት የተፈጠረ የእግዚአብሔር እምነት አለን፡፡ እኛ በእግዚአብሔር ላይ እምነት አለን ምክንያቱም ልጅ በቤተሰቡ ላይ መታመኑ ጤናማና ያለ ነገር ነውና፡፡ እኛ ጠላት በውስጣችን ያለውን የእግዚአብሔርን ዓላማ ለማጨናገፍ ከሚሞክረው ይልቅ በሕይወት የሚያጋጥሙንን ችግሮች ለማሸነፍ ከምንም ነገር በላይ እንዳስቀምጠን በእግዚአብሔር ብቃትና ችሎታ ላይ መጠን አልባ እምነት አለን፡፡

በሌላ አባባል ከጠላት ችሎታ ይልቅ በእግዚአብሔር ብቃት ላይ የላቀ እምነት አለን ማለት ነው፡፡እኛ ተጽእኖ ሊያደርግብን ከሚፈልግ ሁኔታ ወይም በቀንበር ስር ሊያሳድረን ከሚፈታተነን አካባቢ ይልቅ በእግዚአብሔር ቃል ላይ ወሰን የለሽ እምነት አለን፡፡

ለእኛ እግዚአብሔር በዓለም ካሉት ነገሮች ሁሉ በላይ እጅግ ታላቅ ነው። እኛ በዙሪያችን ከከበቡንና አስፈሪ ናቸው ብለን ከምንላቸው ሁኔታዎች በላይ በእኛ ውስጥ ያለው እርሱ በርግጥ ታላቅ መሆኑን አውቀናል። እኛ ከአሸናፊዎች እንደምንበልጥ ከውድቀት ዓለም ወጥተንና አልፈን ወደ ስኬትና ድል ዓለም እንደ ገባን ተረድተናል።

## ለኃጢአት እውቅናን መስጠት በእምነት ላይ ያለው ተጽእኖ

እምነት በኩነኔ ከባቢ አየር ውስጥ ሊያድግ አይችልም። እኛ ራሳችንን በኃጢአት እውቅና ወይም ኩነኔ ሥር እስካሳደርን ድረስ እምነታችን ደካማና ውጤት አልባ ይሆናል። እኛ ያለማቋረጥ ስለ ኃጢአት የሚሰበክበት ቤተ ክርስቲያን የምንካፈል ከሆነ በውስጣችን የኃጢአት እውቅና ወይም ኩነኔ እንዲነሰብት በማድረግ የእምነታችንን ብርታት ያዳፍነዋል።

እምነት ልክ እንደ ፍቅር የማያቋርጥ አዋጅን ይሻል። እኛ ሳናሰልስ ውዶቻችን ለሆኑት ፍቅራችንን ካላረጋገጥንላቸው ፍቅር ቀስ በቀስ እየቀዘቀዘ አጥጋቢ ተጽእኖውን ያጣል። ስለዚህ ምንጊዜም  የማያቋርጥ የፍቅራችን ማረጋገጫ የሆነ መግለጫያ ያስፈልጋል። አንዳቸው ለአንዳቸው ያላቸውን ፍቅር የማይገልጹ ባልና ሚስት ይዋል ይደር እንጂ ቀስ በቀስ እርስ በእርስ የነበራቸው ንቁ ጎብረት መላላቱ አይቀርም። ይህ ለእምነትም አንድና ተመሳሳይ ነው። እኛ ግን በቋሚነት በእምነት መታመናችንን እናረጋግጣለን እርሱም ያድጋል።

## ልናደርጋቸው የሚገቡ ጥቂት ማረጋገጫዎች

"ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ።" "የእግዚአብሔር ብቃትና ችሎታ በእኔ ውስጥ አለ።" "በእኔ ውስጥ ለዘላለም የሚኖር የእግዚአብሔር ሕይወት አለ።" "እኔ የእርሱ ጥበብ አለኝ።" "እኔ ጥበብን መጠየቅ የለብኝም ምክንያቱም ጥበብ የእኔ ነው።" "እኔ ስለ እምነት መጸለይ የለብኝም ምክንያቱም የእርሱ የተሰፋ ቃሎች አይሻሩምና። የትኛውም የእግዚአብሔር ቃል ኃይል አልባ አይደሉም።" "እኔ ወደ ዙፋኑ ክፍል በድፍረት እንድቀርብና እንድቆም እንዲሁም በአባቴ ሕልውና ውስጥ እንድቀመጥ ተጋብዣለሁ።" "እኔ የመለኮታዊ በሕርዩ ተካፋይ ነኝ።" "እኔ ሁልጊዜ የእርሱ ሕልውና በውስጤ ለማደሩ ንቁ ነኝ።" "በእኔ ውስጥ ያለው በዚህ ዓለም ካለው ይልቅ እጅግ ታላቅ ነው።" "እኔ በውስጤ ለዘላለም የሚኖር የእርሱ የፍቅር ሕይወት አለኝ።"

እነዚህ የእምነት ማረጋገጫ አዋጆች ኃይል በአማኙ ውስጥ ጤንነትና ሕይወትን ይገነባሉ። እነዚህ ማረጋገጫዎች ባለ ሙሉ ሥልጣን ቃል ናቸው ወይም ቃሉን መሰረት ያደረጉ ናቸው። ይሁን እንጂ እነዚህ የስሜት እውቀት ማረጋገጫዎች አይደሉም።

ምእራፍ አስራ ስምንት

የእኔ ደረሰኝ

አንደ ቀን በኩላሊት ችግር ከተጠቁ በእድሜ ከገፉ አዛውንት ቅዱስ ሴት ጋር እየተነጋገርኩ ሳለ የእርሳቸውን ደዌ እግዚአብሔር በኢየሱስ ላይ ወደ ማድረጉ እውነት ትኩረታቸውን ወሰድኩት፡፡ "በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ ሕመማችንንም ተሸከሞአል፡፡" የሚለውን ኢሳይያስ 53፥4ን አነበብኩላቸው፡፡

እርሳቸውም "አዎን እውነት ነው፡፡" አሉ፡፡ እኔም "እናቴ ይህ የእግዚአብሔር ቃል ለፍጹም ጤንነት ደረሰኝዎ መሆኑ አይታይዎትምን? እርስዎ ሊከፍሉት የማይችሉት እዳ ነበረብዎትና አንዱ መጥቶ እዳዎ ሙሉ ለሙሉ የተከፈለበትን ደረሰኝ ሰጠዎት፡፡ እርስዎም ደረሰኙን አዩና ሙሉ ለሙሉ እንደ ተከፈለ አወቁ፡፡" አልኳቸው፡፡

"እርስዎ ከእዳ ሙሉ ለሙሉ ነጻ በመውጣትዎ ሐሴት ያድርጉ፡፡" "አብ እዳዎን እንደ ከፈለ እንዲያውቁ ይፈልጋል፡፡ የእርስዎን ደዌ ኢየሱስን አሸክሞታል በእርስዎ ሕመም ኢየሱስ እንዲታመም አድርጓል፡፡ 'እግዚአብሔርም በደዌ ያደቅቀው ዘንድ ፈቀደ፡፡' ኢሳይያስ 53፥10፡፡ "እናንተ ደዌ ሊኖርባችሁ ወይም ስለ ደዌ ታስቡ ዘንድ አይገባችሁም፡፡ ይህ ቃል ለዚያ ደዌ ፍጹም ጤንነት ወቅታዊ ሙሉ ደረሰኛችሁ ነው፡፡ አሁን እንደ ቃሉ በመገረፉ ቁስል ተፈውሳችኋል፡፡"

"እናንተ የእርሱን ቃል ለሚቃረን አሳብ ስፍራ ለመስጠት አሻፈረኝ ማለት አለባችሁ፡፡ የስሜቶቻችሁን ምስክርነት አልቀበልም ማለት ይጠበቅባችኋል፡፡ በሽታው የነበረበት ስፍራ ላይ ሕመሙ ሊሰማችሁ ይችላል ነገር ግን እናንተ ላለመፈወሳችሁ እንደ መረጃ አድርጋችሁ ለመቀበል አሻፈረኝ ማለት አለባችሁ፡፡"

እናንተ የሚጠበቅባችሁ በጸጥታና "በመታመን አባት ሆይ የእኔን የኩላሊት ችግር ኢየሱስ ስለ ተሸከመው እርሱም በዚያ ደዌ ስለ ታመመና እኔም በመገረፉ ቁስል ስለ ተፈወስኩ አመሰግንሃለሁ፡፡" ማለት ብቻ ነው፡፡ "ምንም ዓይነት ስጋት ምንም ዓይነት ፍርሃት የለባችሁም ምክንያቱም ኢየሱስ የእናንተን ደዌ በሥጋው በእንጨት ላይ ተሸክሟልና፡፡

እርሱ በእግዚአብሔር በተመታ በቆሰለና በተቀሰፈ ጊዜ ይህን ሁሉ የተቀበለው ስለ እናንተ ደዌ ነው፡፡ "እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቆሰለ ስለ በደላችንም ደቀቀ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ በእርሱም ቁስል እኛ ተፈወስን፡፡" ኢሳይያስ 53፥10፡፡ "እናንተም ከጠላት ጭቆና አርነት ወጣችሁ፡፡ እናንተ ነጻ ናችሁ፡፡"

## የኃጢአትና የበሽታ ችግር ተፈትቷል

አንድ ጊዜ ኢየሱስ ከሙታን ተለይቶ በርግጥ እንደ ተነሣ ወደ ሰማይ እንዳረገ በርግጥም የገዛ ደሙን በሰማያዊ ስፍራ በቅድስተ ቅዱሳን እንዳቀረበና ፍትሕ እንደ ተቀበለው ለማረጋገጥ ተቸግሬ ነበር፡፡ እኔ ይህ በርግጥ እውነት መሆኑን ለማወቅ እጅግ ጓጉቼ ነበር፡፡ ይህ እውነት ከሆነ እንግዲያውስ የኃጢአትና የበሽታ ችግር ተፈትቷል ስለዚህ ሰይጣን በእኔ ላይ ያለው የበላይነት አብቅቷል፡፡

ኢየሱስ በሰማያት በእግዚአብሔር በግርማው ቀኝ ከተቀመጠ እንግዲያውስ ደቄ በእኔ መንፈስ ነፍስ ወይም ሰውነት ላይ ባለቤትነት የለውም፡፡ "ክርስቶስ አሁን ስላሉት መልካም ነገሮች ሊቀ ካህናት ሆኖ በመጣ ጊዜ በሰው እጅ ወዳልተሠራችው ከዚህ ፍጥረት ወዳልሆነችው ታላቅና ፍጹም ድንኳን ገባ፡፡ የገባውም የፍየልንና የጥጃዎችን ደም ይዞ አይደለም ነገር ግን የዘላለም ቤዛነት ሊያስገኝ የራሱን ደም ይዞ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ገባ፡፡" ዕብራውያን 9፥11-12 (አመት)፡፡

ይህ የእኔን ጥያቄ መለሰልኝ፡፡ እርሱ ለእኔ መንፈስ ነፍስና ሰውነት ዘላለማዊ ቤዛነትን አግኝቶልኛል፡፡ ክርስቶስ ሕመሜን ተቀብሏል ደዌዬን ተሸክሟልና በእርሱ ቁስል ተፈውሻለሁ፡፡ ኢየሱስ በሰማያት በእግዚአብሔር በግርማው ቀኝ ከተቀመጠ ያ ማስረጃ ለኃጢአት ለበሽታና ደዌ ችግሮች የተሟላ የክፍያ ደረሰኝ ነው፡፡ ይህንን ለማረጋገጥ እንዴት በጉጉት ቃሉን እንደፈተሸኩ ልነግራችሁ አልችልም፡፡ "ተቀመጠ" የሚለውን ቃል አስራ ዘጠኝ ጊዜ ወይም ከዚያ በላይ እንደሚያውጅ አገኘሁ፡፡

እርሱ በእግዚአብሔር በግርማው ቀኝ የተቀመጠበት ምክንያት እኔን ነጻ ስላወጣ የፍትሕንም የይገባኛል ጥያቄ ስላረካ ነው፡፡ እርሱ የጠላትን ኃይል ሰብሯል ደምስሷል፡፡ "ራሱን በመሰዋት ኃጢአትን ሊሸር አንድ ጊዜ (ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ) ተገልተጦአል፡፡" ዕብራውያን 9፥26 በቅንፍ ውስጥ ያለው (አመት) ነው፡፡ እርሱ ጽድቅን አስገኝቷል፡፡ (ሁለተኛ ቆሮንቶስ 5፥21) እርሱ የዘላለም ሕይወትን እርግጠኛ አድርጓል፡፡ (አንደኛ ዮሐንስ 5፥1-3)፡፡

እንግዲህ እንዲህ ከሆነ በአዲስ ኪዳን ያለ ማንኛውም ቃል ሁሉ በኢየሱስ ጸንቷል ማለት ነው፡፡ ከኢየሱስ በስተጀርባ ደግሞ ቃሉን ለማጽናት የእግዚአብሔር ዙፋን ወይም ሥልጣን አለ፡፡ ከዙፋኑ በስተጀርባ ደግሞ ለተመሳሳይ ሥራ ራሱ እግዚአብሔር አለ፡፡

"እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ፡፡" አንደኛ ጴጥሮስ 2፥24፡፡ ይህ የኃጢአት ችግር መፍትሔ ብቻ አይደለም ነገር ግን የኃጢአቶች ችግር ሁሉ መፍትሔ ነው፡፡ የኃጢአት ችግር እኛ የሆንነውና የነበርነው ሲሆን ኃጢአቶች ደግሞ የፈጸምናቸው ድርጊቶች ናቸው፡፡ እርሱ ኃጢአትን አስወገደና ወይም ሻረና ኃጢአቶቻችንን ደመሰሰልን ወይም ይቅር አለን፡፡

"ይኸውም ለጽድቅ እንድንኖር ነው፡፡" እንዲህ ያደረገውም እኛ በጽድቅ ዓለም ውስጥ እንድንኖር ነው፡፡ አንግዲህ እኛ ልክ እንደ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በአብ ሕልውና ውስጥ ያለ ምንም ኩነኔና የበታችነት ስሜት ቆመናል ማለት ነው፡፡ እኛ እንደ ሁሉን ቻይ እግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆችነታችን እንደ እርሱ ቤተሰብነታችን ከልጁም ጋር አብረን ወራሽ የመሆን ስፍራችንን ወስደናል፡፡

እኛ ስፍራችንን እስካልያዝን ወይም እስካልወሰድን ድረስ የደሙን ፍቱንነት የእርሱን መስዋእትነትና የኢየሱስን የመቤዠት ሃቀኛነት እውነታ ክደናል ማለት ነው፡፡ እኛ

ስፍራችንን ስንይዝ እግዚአብሔርን አከበርን ማለት ነው፡፡ ልጁንም አከበርን ማለት ነው፡፡ በክርስቶስ የሆነውን አዲስ ፍጥረትነት አከበርን ማለት ነው፡፡ እኛ ስፍራችንን አከበርን ማለት ነው፡፡ የዚህን ቁም ነገር ምንነትና አስፈላጊነቱን መጨበጥ ምንኛ ታላቅ ነገር ነው፡፡

"እናንተ በመገረፉ ቁስል ተፈወሳችሁ፡፡" ይህ የነገሮቹ ወይም የጉዳዮቹ ሁሉ መቋጪያና መደምደሚያ ነው፡፡ ኃጢአት ተወግዷል፡፡ ጽድቅ እውን ሆኖአል፡፡ ደዌ ያለፈ ጊዜ ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ የእግዚአብሔር ቃልና በጳውሎስ በተገለጠው የተፈጸመ የክርስቶስ ሥራ መሰረት እኛ በጭራሽ በፍጹም በድጋሚ በጠላት ቀንበር ስር ልንሆን አይገባም፡፡

እኛ የማናሳፍር ክርስቲያኖች ሆነን በቤተሰቡ ውስጥ ያለ ምንም ኩነኔ ስፍራችንን በመያዝ ራሳችንን ለእግዚአብሔር ልናቀርብ ቃሉን ለማጥናት መትጋት አለብን፡፡ "ታዲያ እንዴት ልንሞት እንችላለን?" ሲል አንዱ ጠየቀ፡፡ አኛ የእግዚአብሔርን አሳብ ጨርሰን ካገለገልን በኋላ ያለ ምንም ሕመም ጌታችንን ከሚያዋርድ አስጠሊታ ደዌ ውጪ እናንቀላፋለን፡፡

እኛ ያለን እንዴት ድንቅ የሆነ ግሩም ዓይነት ጎብረት ግሩም ዓይነት ሕይወት ግሩም ዓይነት መዋጀት ነው!!

ምእራፍ አስራ ዘጠኝ

ኢየሱስ ስለ እምነት የተናገረው

መጀመሪያ ኢየሱስ ከአይሁዶች ለምን እምነት እንደ ፈለገ ግራ ገብቶኝ ነበር በኋላ ግን ለምን እንደሆነ አየሁ፡፡ እርሱ ከያህዌ ጋር እምነትን የተካፈሉ የእግዚአብሔር የኪዳን ሕዝቦችን እየተናገረ ነበር፡፡ ሁለቱ ዓይነ ስውራን ለመፈወስ በመጡ ጊዜ እርሱ "ይህን ማድረግ እንድችል ታምናላችሁን? አላቸው፡፡ አዎን ጌታ ሆይ አሉት፡፡ በዚያን ጊዜ ፡- እንደ እምነታችሁ ይሁንላችሁ ብሎ ዓይኖቻቸውን ዳሰሰ፡፡ ዓይኖቻቸውም ተከፈቱ፡፡" ማቴዎስ 9፥28-30

እርሱ ለማርታ "ብታምኚስ ኖሮ" የእግዚአብሔርን ክብር ባየሽ ነበር አላት፡፡ እንደገና "ለሚያምን ሁሉ ይቻለዋል፡፡" አለ፡፡ እንግዲያስ ማመን የነበረባቸው ምንድን ነበር ... ስለ ኃጢአታቸው እንደሞተላቸውና እነርሱንም ለማጽደቅ ከሞት እንደ ተነሣ እርሱ የእነርሱ ምትክ ሆኖ ኃጢአትን እንዳስወገደ እነርሱ እርሱን እንደ ግል አዳኛቸው አድርገው ቢመሰክሩ (ቢናዘዙ ቢያውጁ) የዘላለም ሕይወትን እንደሚቀበሉ እንዲያምኑ አይደለም፡፡

ታዲያ ምን ዓይነት እምነት እየፈለገባቸው ነበር? እኛ እንደ ተረዳነው ከእነርሱ የፈለገው የድነት እምነትን አይደለም፡፡ "ኢየሱስ ጌታ እንደ ሆነ በአፍህ ብትመሰክር እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳነሳው በልብህ ብታምን ትድናለህና" ሮሜ ፲፥9፡፡ እርሱ በፍጹም አንዳቸውም እርሱን እንደ አዳኝ ለሰዎችም የዘላለምን ሕይወት እንደሚሰጥ እንዲያምኑት አልጠየቀም፡፡ እርሱ የጠየቃቸው ነገር ቢኖር እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ ፈዋሹ መሲህ እንደ ሆነ ብቻ እንዲያምኑት ነው፡፡

እርሱ እኛ እርሱን ምትክ መስዋእት ወይም መለኮታዊ ልውውጥ ብለን የምንጠራውን እነርሱ እንዲያምኑ አልጠየቃቸውም፡፡ ይህንን በፍጹም አልጠቀሰም፡፡ እርሱ ሞቶ አልተነሳም ነበርና በትንሣኤው እንዲያምኑም አልጠየቃቸውም፡፡

ማርቆስ ፲፥24 ይህንን ይገልጣል፡፡ እነርሱ የበለሷ ዛፍ ከስሯ ደርቀው አዩ፡፡ ጴጥሮስም ትዝ አለውና "እነሆ የረገምሃት በለስ ደርቃለች አለው፡፡ ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው ፦ በእግዚአብሔር እመኑ፡፡" ከዚያም "እውነት እላችኋለሁ ማንም ያለው ነገር እንዲደረግለት ቢያምን በልቡ ሳይጠራጠር ይህን ተራራ ፦ ተነቅለህ ወደ ባሕር ተወርወር ቢል ይሆንለታል፡፡ ስለዚህ እላችኋለሁ የጸለያችሁትን የጠየቃችሁትንም እንዳገኛችሁት እመኑ ይሆንላችሁማል" አለ፡፡

እርሱ በወቅቱ ለቤተክርስቲያን እየተናገረ አልነበረም፡፡ እየተናገረ ያለው በቀደመው ኪዳን ስር ለነበሩ አይሁዶች ነበር ሆኖም በተዘዋዋሪ መንገድ እኛንም ይመለከታል፡፡ ኢየሱስ እነርሱ በእርሱ እንዲያምኑ አበክሮ እየጠየቀ ነው፡፡ እንደ ሰው ሊያዩት ችለዋል፡፡ በእርሱም የተከናወነውን ተአምራት አይተዋል፡፡ ብዙ ሕዝብን መግቧል ውኃን ወደ ወይን ጠጅ ለውጧል በባሕር ላይ ሄዷል እርሱ ነፋሳትንና ማእበልን ገስጿል እርሱ ሙታንን አስነስቷል፡፡ በዮሐንስ 6፥30 ላይ አይሁዶች " እንኪያ አይተን እንድናምንህ ምን ምልክት ታደርጋለህ?" አሉት፡፡ እነርሱ የነበራቸው የስሜት እውቀት እምነት ነበር፡፡ እነርሱ ባዩት ወይም በሰሙት አምነው ነበር፡፡

ዮሐንስ 20፥24-29 የቶማስ አለማመን ታሪክ ነው፡፡ እርሱም "የችንካሩን ምልክት በእጆቹ ካላየሁ ጣቴንም በችንካሩ ምልክት ካላገባሁ አላምንም፡፡" አላቸው፡፡ ከስምንት ቀን በኋላ ኢየሱስ ድንገት ተገለጠና ቶማስን "ጣትህን ወደዚህ አምጣና እጆቼን እይ እጅህንም አምጣና በጎኔ አግባው ያመንህ እንጂ ያላመንህ አትሁን" አለው፡፡ ኢየሱስ ቶማስን እርሱ ከሙታን እንደ ተነሣና ኃጢአቱን እንዳስወገደለት እንዲያምን እየጠየቀው አልነበረም፡፡ ኢየሱስ ቶማስ በርግጥ በእርሱ እንዲያምን የስሜት እውቀት እምነቱን መገዳደሩ ብቻ ነበር፡፡ ምክንያቱም የቶማስ እምነት የተመሰረተው በሚያየው በሚዳስሰውና በሚሰማው በአምስቱ የስሜት ሕዋሳቶቹ ላይ ነበርና፡፡

በወቅቱ ከኢየሱስ ጋር ይመላለሱ የነበሩት አንዳቸውም ጳውሎስ በሮሜ ላይ የነገረንን ዓይነት እምነት እንዳልነበራቸው መረዳት ትችላላችሁ፡፡ ኢየሱስ ከእነርሱ ማንንም እርሱ አዳኝ እንደ ሆነና እነርሱንም ለማጽደቅ ከሙታን ተለይቶ እንደሚነሣ እንዲያምኑ አልጠየቀም፡፡

በዮሐንስ ፲፥27 ላይ ማርታ ኢየሱስን "አዎን ጌታ ሆይ አንተ ወደ ዓለም የሚመጣው ክርስቶስ የእግዝአብሔር ልጅ አንደ ሆነህ አምናለሁ" አለችው፡፡ ይህ የድነት አዋጅ ምስክርነት ወይም ኑዛዜ አይደለም፡፡ ማርታ ከኃጢአት የመዳንን ምስክርነት አውጃ ቢሆን

ኖሮ "አዎን ጌታ ሆይ አንተ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆንክ አምኛለሁ ደግሞም ስለ እኔ ኃጢአት እንደምትሞት እኔንም ለማጽደቅ እንደምትነሣ አምናለሁ::" ባለች ነበር::

ዮሐንስ 20፥9 "ከሙታን ይነሣ ዘንድ እንዲገባው የሚለውን የመጽሐፉን ቃል አላወቁምና::" ይላል:: ከሙታን ተለይቶ ከተነሣም በኋላ ማንም እርሱን ከኃጢአት አዳኝ የዘላለም ሕይወት ሰጪ የአዲስ ውልደት አመንጪ አድርጎ የገለጸው አንድም የለም:: በርግጥ እነርሱ ከሞት እንደተነሣ ግን አምነዋል::

የክርስቶስ ምትክነት መለኮታዊ ልውውጥ ሥራ እውቀትና የአዲስ ፍጥረትነት ግንዛቤ መታወቅ ከመቻሉ በፊት ጳውሎሳዊው መገለጥ መምጣት ነበረበት:: ኢየሱስ "ግን እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል የሚሰማውን ሁሉ ይናገራል እንጂ ከራሱ አይነግርምና የሚመጣውንም ይነግራችኋል::" አለ:: ዮሐንስ 16፥13:: ይህ ኢየሱስ በምድር በተመላለሰበት ጊዜ ካስተማረው ጎን ለጎን የኢየሱስና የአብ መገለጥ እንደሚኖር ያመላከተ ነበር:: ያም መገለጥ በሐዋርያው ጳውሎስ በኩል መጣ::

መሰረታዊ መርሆዎቹም በመጀመሪያዎቹ የሮሜ አስር ምእራፎች ውስጥ ይገኛሉ:: በዚያ ውስጥም ለእኛ በኢየሱስ ለሚያምን ሰው የእግዚአብሔር ጽድቅ መገለጡ ተገልጿል:: ጽድቅ ማለት ኢየሱስ በምድር ሲመላለስ በነበረበት ጊዜ እንዳደረገው በእግዚአብሔር ሕልውና ውስጥ ያለምንም የኃጢአተኝነት ስሜት መቆም መቻል ማለት ነው:: ኢየሱስ በምድር ላይ በሥጋ በተመላለሰበት ጊዜ በክርስቶስ ትምሕርት ውስጥ የዚህ ፍንጭ የለም::

## የሐዋርያው ጳውሎስ ትምሕርት

የእስራኤል እምነት ሁሉ የወደፊት ወይም የመጪ ጊዜ ነበር:: የእኛ እምነት ሥሩን የሚመዘው ቀደም ሲል እግዚአብሔር በክርስቶስ ሠርቶ ከፈጸመው ሥራ ነው:: አብርሃም ወደ ተስፋው ተመለከተ ሆኖም ምንም ዓይነት ጥያቄ አላነሳም ወይም አልተገዳደረም:: እኛ የመዋጀታችንን ርግጠኝነት ፈውሳችንን አብ ለእኛ ያለውን እንክብካቤ አዲስ ኪዳንን እየተመለከትን እንደ አብርሃም በብርታት ለእግዚአብሔር ክብርን እንሰጣለን::

እኛ እንደ እግዚአብሔር ልጅነታችን ልንተገብራቸው የሚገቡ ጥቂት ቀላል መረጃዎች እኒሁላችሁ:: "በክርስቶስ በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ የባረከን የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ::" ኤፌሶን 1፥3:: ይህ የሚያሳየን እኛ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛችንና ጌታችን አድርገን በተቀበልንና በመሰከርን ጊዜ እግዚአብሔር በክርስቶስ ያመጣው ማንኛውም ነገር ሁሉ የእኛ መሆኑን ነው:: እርሱ የእኛ ሆኗል::

ዛሬ ኢየሱስ ለዓለም ሁሉ እንደተገባው እግዚአብሔር በዮሐንስ 3፥16 ላይ "እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና::" ብሎ እንደተናገረው ማለት

ነው፡፡ እግዚአብሔር ኢየሱስን ለዓለም ሰጥቷል፡፡ ያልዳነው ሰው ኢየሱስን እንደ አዳኝ መጠየቅ አያስፈልገውም፡፡ ኢየሱስ ላልዳነው ሰው ተሰጥቶታል ተገብቶታልም፡፡ አብ ይህንን ስጦታ በፍጹም መልሶ አልወሰደም፡፡ ይህ ስጦታ ዛሬም ለተሰጣቸው ሕዝቦች ክፍት ነው፡፡

ይህንን ስጦታ ስትቀበሉ ክርስቶስ የሠራው ነገሮች ሁሉ የእናንተ ሆኗል፡፡ በአእምሮ መንፈስ ካለመታደሳችን የተነሳ ይህን ለመቀበል እኛን ያስቸግረናል፡፡ ይሁን እንጂ እነርሱ በሙሉ የእኛ ናቸው፡፡ መንፈስ ቅዱስ ለቤተ ክርስቲያን ተሰጥቷል፡፡ "እንኪያስ እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታ መስጠት ካወቃችሁ በሰማይ ያለው አባት ለሚጠይቁት እንዴት አብልጦ መንፈስ ቅዱስን ይሰጣቸው፡፡" ሉቃስ ፲፩፥23፡፡

ልክ ዳግም የተወለዳችሁ ቀን በዚያ ቅጽበት ለመጠየቅ የእናንተ ሆኗል፡፡ የዘላለም ሕይወት ለኃጢአተኛ ተሰጥቷል፡፡ ኃጢአተኛው ልክ ኢየሱስ ክርስቶስን በተቀበለ ጊዜ እርሱ የዘላለም ሕይወትን አግኝቷል፡፡ "ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም፡፡" አለ ስለዚህ እርሱ የጸጋ ስጦታ ነው፡፡

እኛ "በክርስቶስ ኢየሱስ የተፈጠርነው" መቼ ነው? በሦስቱ ቀናት ውስጥ እርሱ ከሙታን ከመነሣቱ በፊት ነው፡፡ እኛ ጽድቅ ተብለን ያታወጀልንስ መቼ ነው? "እርሱ ስለ መተላለፋችንና ስለ ኃጢአታችን አልፎ ተሰጠ እኛም በጸደቅን ጊዜ ተነሣ፡፡" ወይም ጽድቅ ታወጀ፡፡ ጽድቅ ስጦታ ነው፡፡ ድነት ስጦታ ነው፡፡ እኛ በጥረታችን እምናገኘው አይደለም፡፡

እግዚአብሔር ለጳውሎስ በሰጠው መገለጥ ኃጢአተኛው እግዚአብሔር በክርስቶስ ስለ ሠራለት ሥራ እምነት እንዲኖረው ጠይቋል፡፡ ኃጢአተኛው ኢየሱስ ስለ ኃጢአቱ እንደ ሞተለትና እንደገና ከሞት እንደ ተነሣ ማመን ያስፈልገዋል፡፡ የጳውሎስን መገለጥ ካመናችሁ በኋላ የእምነት ችግር እንደገና አይነሳም ሁሉ ነገር የእናንተ ሆኗልና፡፡ የራሳችሁ የሆነውን ለማግኘት እምነታችሁን መለማመድ አያስፈልጋችሁም፡፡ የሚያስፈልጋችሁ የእናንተ እንደሆነ ማወቅ ብቻ ነው፡፡

## ማጠቃለያ

አነበባችሁ አይደል ታዲያ ምላሻችሁ ምንድን ነው? አብዛኛው ለእናንተ አዲስ ነው፡፡ ከዚህም ውስጥ ጥቂት ነገሮች ግር አሰኝተዋችኋል አይደል! ይሁን እንጂ ልባችሁ ወይም መንፈሳችሁ እውነት መሆኑን አውቋል፡፡ ታዲያ በእርሱ ምን ለማድረግ አሰባችሁ?

ዛሬ ዛሬ ቤተ ክርስቲያን ተስፋ በሚያስቆርጥ ሁኔታ ውስጥ ነች፡፡ ማለትም በየትኛውም ስፍራ ባሉ አማኞች ዘንድ ያለው ንቁ ቀልጣፋና ሕያው እምነት እጅግ ጥቂት ነው፡፡ ታዲያ እናንተ ይህን አብንና ኢየሱስን መንፈሱንና ቃሉን እውን የሚያደርገውን የከበረ እውነት

ለማሰራጨት አትረዱንምን? ጥቂትም ቢሆኑ ጓደኞቻችሁን ጋብዙና ይህቺን መጽሐፍ በማንበብ ተወያዩ።

በማኅበረሰቦቻችሁ መካከል ያሉ መጋቢዎቻችሁና መጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪዎቻችሁ እያንዳንዳቸው ይህ መጽሐፍ እንዲኖራቸው አድርጉ።

## አስተያየት

እናንተ በስሜት እምነትና በቃሉ ላይ የተመሰረተ እምነት መካከል ያለውን ልዩነት አይታችኋል። እንግዲህ በስሜት እምነት እየኖሩ ሆኖም ከቃሉ ከሚገኝ እምነት ብቻ ሊመጣ የሚችለውን ውጤት በስሜት እውቀት እምነት ለማግኘት የሚታገሉትን ለመታደግ የእናንተ ኃላፊነት ምንድን ነው?

"ነገር ግን" እናንተ "እንዴት አድርጌ ልረዳቸው እችላለሁ?" ትላላችሁ። ይህንን መጽሐፍ በማሰራጨት በማኅበረሰቡ መካከል የንባብ ቡድን በማደራጀትና በዚህ መጽሐፍ አማካኝነት እግዚአብሔር ምን ሊያደርግላቸው እንደሚችል በመንገር ልትረዷቸው ትችላላችሁ።

የንባብ ቡድን ማቋቋም ባይቻላችሁ እንኳ እነኚህን መጻሕፍት ብታሰራጩ ጌታ አይደሰትምን? እኛም ይህንን አንብበው በተጠቀሙና ለሌሎች በሚያደርሱ እንኮራለን። እናንተ በዚህ አገልግሎት ድርሻ ሊኖራችሁ እንደምትፈልጉ የታወቀ ነው። ጌታ ይባርካችሁ!

በተከታታይ የእኚህን ታላቅ የእግዚአብሔር ሰው መጽሐፍ እንደማቀርብላችሁ ርግጠኛ ነኝ። ለሕትመት ከተዘጋጁት መካከል “ሁለቱ የጽድቅ ዓይነቶች” ና “ፈዋሹ ኢየሱስ” ይገኙበታል።

# ሁለቱ የጽድቅ ዓይነቶችና ፈዋሹ ኢየሱስ ይገኙበታል፡ለማሰራጨት በሚረዱ

ያልተመለሱ ጸሎቶች በአማኝ ግለሰብና በአማኙ እምነት ሕይወት መካከል ቆሟል። ጥቂቶች ጭርሱኑ እምነታቸውን አጥተዋል። አብዛኛዎቹም የጸሎት ሕይወታቸው ፉርሽ ከመሆኑ የተነሳ ወደ ፍልስፍናና ሜታፊዚካል አምልኮ ዞረዋል።

ነገር ግን ለእምነት መሰረት የሆነ አንድ ነገር ብቻ አለ እርሱም ሕያው ቃሉ ነው። እኛ ከቃሉ ጋር በተግባር አንድ ስንሆን ያን ጊዜ እምነት ሳንጨናነቅ የምንኖረው እውነታ ይሆናል። ያኔ ስለ እምነታችሁ አታስቡም ይልቁንስ ስለ ፍላጎታችሁና እርሱም ፍላጎታችሁን ሊያሟላ ብቃት እንዳለው ብቻ ታስባላችሁ።

ይህቺ መጽሐፍ በትክክለኛ እምነት በአእምሮ ስምምነትና ተስፋ መካከል ያለውን ልዩነት አሳይታችኋለች። ተስፋ ሁል ጊዜ የወደፊቱን ወይም የመጪውን ጊዜ አማላካች ስለሆነ ተስፋ ያደረጋችሁትን ማንኛውንም ነገር መቀበል አያስችላችሁም። እምነት አሁን ነውና!

ትክክለኛ እምነት ከስሜት መረጃ ባሻገር በቃሉ ላይ መቆም ነው። ይህቺ መጽሐፍ ለእናንተ በትክክለኛ እምነትና የስሜት እውቀት እምነት መካከል ያለውን ልዩነት ገልጻ ታሳያችኋለች። የስሜት እውቀት እምነት አውነተኛውን እምነት ከቤተ ክርስቲያን ጨርሶ ወደ ማጥፋት ተቃርቧል። "ማመን" በእውነቱ "ቃሉን ተግባራዊ ማድረግ ነው" እናም እምነት የተግባር ውጤት ነው።

ከመጽሐፉቱ የተወሰደ

ራሳቸውን እግዚአብሔርን መምሰል ያስለመዱ ሰዎች ስነ መለኮታዊ ትንታኔ ብቻ ከሚሰጡና ስለ እግዚአብሔር አስተያየት ከሚያቀርቡ ነገር ግን ምንም ዓይነት ድንቅ ምልክትና ተአምራት ከማይከተላቸው ምሕረት ስር አይወድቁምና የእነዚህን የእግዚአብሔር አርበኞች መጻሕፍት ማንበብ እነርሱ እዚያ ለመድረስ የወጡት የወረዱትን ጊዜ የፈጁትን ጉልበት ሳንወጣና ሳንወርድ እነርሱ በደከሙበት ልንገባ ያስችለናል። (ዮሐንስ 4÷38)። ከዚያም ባሻገር የኑሮአቸውን ፍሬ ተመልክተን በእምነታቸው ልንመስላቸው ዕድልን ይሰጠናል። ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ለዘላለም ያው ነውና። (ዕብራውያን 13÷7-8)።

"እምነት" ከአብ ለእያንዳንዳችን የተሰጠ የጸጋ ስጦታ ሲሆን "ማመን" ደግሞ እኛ ስለ ተሰጠን ስጦታ የምንሰጠው ምላሽ ነው።  ማንም ጨዋ ሰው ስለተቀበለው ስጦታ አመሰግናለሁ እንደሚለው ማለት ነው። "ማመን" ክርስቶስ የከፈለውን ዋጋ ባልተከፈለና በማያወላውል ልብ በእሺታ መንፈስ መቀበልና በምስጋና ውጤቱን ጭምር የራስ በማድረግ ባለቤትነትን ማረጋገጥ ነው።

የእግዚአብሔር ልጅ እስክንድር ሐዲስ